አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፤ የቋንቋ ጥናት፤ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል፤የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ በአራት ትምህርት ቤቶች የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ

በ

ሰለሞን ገብሩ

ነሐሴ 2010 ዓ.ም

# በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ በአራት ትምህርት ቤቶች የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ


አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፤ የቋንቋ ጥናት፤ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል፤የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር


ለተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

ሰለሞን ገብሩ



ነሐሴ 2010 ዓ.ም

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ


## የሂዩማኒቲስ፤ የቋንቋ ጥናት፤ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል፤የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር


# በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ በአራት ትምህርት ቤቶች የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ


በ

ሰለሞን ገብሩ


## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| ስም | ፊርማ |
| --- | --- |
| ______________________ | ____________ |
| አማካሪ | |
| ______________________ | ____________ |
| ፈታኝ | |
| ______________________ | ____________ |
| ፈታኝ | |

ነሐሴ 2010 ዓ.ም

# ምስጋና

ውድ ግዜአቸውን ሰውተው በየግዜው የማቀርብላቸውን ጽሁፍ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በጥልቅ በማየት ገንቢ አስተያየታቸውን ፣ የጥናታዊ ጽሁፍን ምንነትና የአሰራር ስርዓትን እንድገነዘብ ለረዱኝ አማካሪዬ ለዶክተር ሙሉሰው አስራቴ ላቅ ያለ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

በጥናቱ አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ ላደረጉልኝ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች፣ ጽሁፍን በመተየብና ሙያዊ ምክር ለሰጡኝ ለመስከረም ታደሰ፣ማህደር ግርማ ፣ ፍቃዱ ፋንታዬ፣ ዘላለም ቅጣው ፣ አዜብ አስተራይ፣ ሸዋሰገድ ሀ/ጊዮርጊስ፣ ግርማ መንግስቴ ፣ ውባየሁ ደነቀው፣እመቤት አበራ፣እስክንድር ተስፋሁን፣ የለም 2ኛ ደረጃ ት/ቤት አመራሮችና የቢሮ ፀሀፊዎች እንዲሁም ለባለቤነና ለሁለቱ ሴት ልጆቼ እንዲሁም ስማቸውን ለልጠቀስኳቸው በሀሳብ ለረዱኝ ጓደኞቼ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

ትምህርቱን እንድማር እድሉን ላመቻቹልኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ እና ትምህርቱን ለሰጡኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋ መምህራኖቼ በሙሉ ክፍ ያለ ምስጋና ይድረሳቸው፡፡

# ማውጫ


- ምስጋና ---------------------------------------------------------------------------------------------------- I
- ማወጫ-------------------------------------------------------------------------------------------------------- II
- የሰንጠረዥ ማውጫ--------------------------------------------------------------------------------------- III
- አጠቃሎ-------------------------------------------------------------------------------------------------- IV


## ምእራፍ አንድ

## መግቢያ


1.1. የጥናት ዳራ ------------------------------------------------------------------------------------------ 1

1.2. የጥናቱ መነሻ ----------------------------------------------------------------------------------------3

1.3. የጥናት አላማ ------------------------------------------------------------------------------------------ 3

1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት ------------------------------------------------------------------------------------3

1.5. የጥናቱ ወሰን -------------------------------------------------------------------------------------------4


## ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ፅሑፍ ቅኝት


2.1. የመናገር ክሂል ፅንስ ሀሳብ ------------------------------------------------------------------------- 5

2.2. የመናገር ክሂል የማስተማር አላማ ----------------------------------------------------------------- 6

2.3. የመናገር ክሂል መማር ------------------------------------------------------------------------------- 9

2.4. የመናገር ክሂልን ትምህርት አቀራረብ ---------------------------------------------------------------9

2.5. የመናገር ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት ------------------------------------------------ 11

2.5.1 መዋታ -----------------------------------------------------------------------------------------14

2.5.2 ችግሮችን አፍልቆ መፍትሔ መሻት-------------------------------------------------------14

2.5.3 ታሪክ መናገር ---------------------------------------------------------------------------------15

2.5.4 ሚና ጨዋታ ------------------------------------------------------------------------------------16

2.5.5 ጭውውት -------------------------------------------------------------------------------------17

2.5.6 ቃላዊ ሪፖርት --------------------------------------------------------------------------------17

2.5.7 ውይይት ---------------------------------------------------------------------------------------18

2.6. የመናገር ክሂል ሲተገበር የሚያጋጥሙ ችግሮች ------------------------------------------------------20

2.7. የመናገር ክሂል ሲተገበር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለሚያስወገድ የሚጠቅሙ ተግባራት-------21

2.8. በመናገር ክሂል በትምህርት አቀራረብ የመምህሩ ሚና -------------------------------------------22

2.9. የቀደምት ስራዎች ቅኝት ---------------------------------------------------------------------------25

## ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

3.1. የጥናቱ ክንዋኔ -----------------------------------------------------------------------------------------27

3.2. የተጠኚዎች ናሙና አመራረጥ -------------------------------------------------------------------27

3.2.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ---------------------------------------------27

3.2.2 የመማሪያ ክፍል ናሙና አመራረጥ -----------------------------------------------28

3.2.3 የመምህራንና ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ --------------------------------------28

3.2.3.1 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ------------------------------------------------------28

3.2.3.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ -------------------------------------------------------29

3.3 መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ---------------------------------------------------------------------29

3.3.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ -----------------------------------------------------------------29

3.3.2 የጽሑፍ መጠይቅ ----------------------------------------------------------------------------30

3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ ---------------------------------------------------------------------------------30

## ምዕራፍ አራት

## የመረጃዎች ትንተና

4.1 ከጽሁፍ መጠይቅና በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ----------------------------------------31

4.1.1 መምህራን የመናገር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ በአቀራረብ ደረጃ ምን ያህል እንደሚተገብሯቸው መፈተሽ -----------------------------------------------------31

4.1.2 መምህራን የመናገር ክሂል ትምህርት ሲተገብሩ የልምምዱን ሂደት መመርመር-----------------------------------------------------------------------------------------------39

4.1.3 የመናገር ክሂል ትምህርትን ሲተገበር በአፍልቆት ወቅት የሚታየውን ውጤት መፈተሽ --------------------------------------------------------------------------------49

4.2 የመረጃዎች ትንተና ማብራሪያ ----------------------------------------------------------------------57

4.2.1 የመናገርን ክሂል ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች ክንውኖች ---------------------------57

4.2.2 የክፍል ውስጥ የመናገርን ክሂል ትምህርት ትግበራ --------------------------------57

## ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳብ

5.1 ማጠቃለያ -----------------------------------------------------------------------------------------59

5.2 አስተያየት-----------------------------------------------------------------------------------------60

ዋቢ መጽሀፍት ------------------------------------------------------------------------------------62

አባሪ

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1- በጥናቱ የተካተቱ ትምህርት ቤቶች፣የተማሪዎችና የመምህራን ብዛት
ናሙና መጠን እና የምልከታ ጊዜ መግለጫ ………………………….27

ሠንጠረዥ 2- የተተኳሪ መምህራን ዳራዊ መግለጫ ….…………………………..28

ሠንጠረዥ 3፡- መምህሩ የእለቱን ትምህርት የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል
ትምህርት ተግባራትን አቀራረብ አስመልክቶ ከምልክታ የተገኘ
ውጤት የሚያሳይ መግልጫ----------------------------------------------32

ሠንጠረዥ 4፡- የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ
ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ መግለጫ--------------------------------35

ሠንጠረዥ 5፡- የመናገር ክሂል ተግባራት አቀራረብን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ
መግለጫ--------------------------------------------------------------- 37

ሠንጠረዥ 6፡- የመናገር ክሂል ትምህርት የልምምድ ተግባርን የሚያሳይ ከምልክታ
የተገኘ መግለጫ---------------------------------------------------------39

ሠንጠረዥ 7፡- የመናገር ክሂል ትምህርት የልምምዱን ተግባር የሚያሳይ መግለጫ-41

ሠንጠረዥ 8፡- የተማሪዎች የመናገር ክሂል የልምምዱን ተግባር ከመምህሩ መጠይቅ
የተገኘ መግለጫ---------------------------------------------------------44

ሠንጠረዥ 9፡- የመናገር ክሂል ትምህርት የልምምድ ሂደትን በተመለከተ ከተማሪዎች
ምላሽ የተገኘ መግለጫ-----------------------------------------------47

ሠንጠረዥ 10 ፡- ተማሪዎች በአፍልቆት ወቅት ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገለፁ
መምህሩ ያመቻችበት ሁኔታ መግለጫ---------------------------49

ሠንጠረዥ 11፡- ተማሪዎች ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲገለፅ በማድረግ ከመምህሩ ምላሽ
የተገኘ መግለጫ-------------------------------------------------------52

ሠንጠረዥ 12፡- የአፍልቆት ደረጃ የመናገር ክሂል አቀራረብ በሚመለከት
የተማሪዎችን ምላሽ የሚያሳይ መግለጫ------------------------------55

# *አጠቃሎ*

*የቋንቋ ክሂሎች የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን በተገቢው መንገድ የሚተገበር ከሆነ የቋንቋውን ትምህርት ዓላማ ለማሳካትና በተማሪዎች ላይ የተፈለገውን ለውጥ ለማምጣት ያለው አስተዋፅኦ አሌ የማይባል ነው። የዚህም ጥናት ዓላማም የመናገር ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርን መመርመር ነው። በዚህ መሰረት በዋናነት በመምህራን ላይ ትኩረት ያደረገ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ምልከታ ተከናውነዋል። በተጨማሪም መምህራንና ተማሪዎችም የጽሑፍ መጠየቅ እንዲሞሉ የተደርጓል። በቦሌ ክፍለ ከተማ ከሚገኙ ስድስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አራት በመምረጥና ከአራቱ ትምህርት ቤቶች አራት የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአላማዊ ናሙና አማካይነት ተመርጠዋል። የአራቱ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ከየትምህርት ቤቱ የተመረጡ 120 የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል። ከመልክታና ከጽሑፍ መጠይቅ ከተገኙት መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው ጥቂት መምህራን በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት በጥንድ ወይም በቡድን ሥራ እንዲታገዝ አለመሞከራቸውን፣ በቋንቋው ተጠቅመው በንግግር  ሀሳባቸውን በነፃ የሚገልጹበትን ሁኔታ አለማመቻቸታውን፣ የመናገር ማስተማሪያ ደረጃዎችን በተገቢው መንገድ አለማከናወናቸውን፣ በተጨማሪም ከመማሪያ መጽሐፉ ጎን ለጎን የተማሪዎችን ፍላጎት ሊያነሳሳ የሚችል ተግባር በጥንቃቄ አለመመረጡ፣ የዕለቱን የመናገር ክሂል ትምህርት ርእሰ ጉዳይ ግልጽ በሆነና በማይረሳ መልኩ አለመቅረቡ፣ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል አለመስጠቱ እና ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን ለማበረታታት የተሻለ ሙከራ አለመደረጉ፤ በመጨረሻም በመማር ማስተማሩ ሂደት የመናገር ክሂሉን ለማዳበር ያሉበትን ችግሮች ለማቃለል የመናገር ክሂል ተግባር ከመከናወኑ በፊት የትምህርት ዓላማ በዝርዝር እንዲቀርብ ቢደረግ፣ተማሪዎች ወደዋናው የመናገር ክሂል ትምህርት ከመግባታቸው በፊት የማነቃቂያ ትምህርት ቢሰጣቸው፣ የመናገር ክሂልን ለማሳደግ የቀረቡትን ተግባራት ለማለማመድ የሚሰጠው ጊዜ ከመልመጃዎቹ ስፋት ጋር መታየት እናዳለበት የመፍትሄ ሃሳብ ቀርቧል።*

# ምዕራፍ አንድ

# መ ግ ቢ ያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የአንድ የቋንቋ መምህር ዋናው ትኩረቱ ተማሪዎች ስለቋንቋው መዋቅራዊ ክፍሎች እንዲያውቁ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በቋንቋው ክሂሎች እንዲካኑና ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲፈፅሙ ተገቢ የሆነ ሰልቶችን በመጠቀም ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ መርዳት እንዳለበት Byrne (1976:1)ይገልፃሉ፡፡

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማ ተማሪዎች ታላሚውን የቋንቋ ስርዓትና አጠቃቀም ወይም እዉቀትና ክህሎት አወቀው መግባባት እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ ግቡም በታላሚዉ ቋንቋ የማዳመጥ፣የመናገር፤የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ማዳበር እንዲሁም የስነ-ልሳንና የስነጹሑፍ መሰረታዊ እዉቀትን ማስጨበጥ ነዉ፡፡

መናገር ሀሳብን በቃል መግለፅ እንደሆነ የመስኩ ባለሞያዎች አረጋግጠዎል፡፡ ሀሳብ በንግግር በሚገለፅበት ወቅት መታየት የሚገባቸዉና ከንግግር ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህም ሀሳብን በትክክለኛ አረፍተ ነገር አሰካክ መግለፅና የሚገለፀዉ ሀሳብ በንግግሩ ወቅት ከሚታየዉ አካላዊ እንቅስቃሴ ጋራ የተደጋገፈና የተመጣጠነ መሆን አለበት በማለት Widdowson (1992፡59-60) ያስቀምጣሉ፡፡

የንግግርን ክሂል በክፍል ዉስጥ አተገባበር በሚመለከት ከመምህር-መር የመማር ማስተማር ዘዴ ይልቅ ቡድኖችን በተለያየ መልክ በማደራጀት እያንዳንዱ ተማሪ የተለያዩ ሀሳቦችን በማፍለቅ እርስ በርስ የተሻለ እንዲነጋገሩ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎቹ ብዙዉን ጊዜ የሚያጠፉት ሀሳብን ለመረዳት በሚያደርጉት ጥረት ተጠምደዉ ነው በማለት Bygate (1987፡96) ይገልፃሉ፡፡

ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ወትሮም ቢሆን የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች በቋንቋ ትምህርት ክፍል ዉስጥ ትኩረት ያላገኙበትን ምክንያት Sesnan (1997፡105) ሲገልፁ ትምህርት ቤቶች አብዛኛዉን ጊዜ ትኩረት የሚያደርጉት በማንበብና በመፃፍ ክሂሎች ነዉ፡፡ ለዚህም ዋናዉ ምክንያት የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን በፈተና መመዘን አስቸጋሪ ነዉ

ከሚል እምነት የመነጨ ነዉ። ነገርግን አንድ ቋንቋ በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ዉጪ ለመገልገል አራቱም ክሂሎች በክፍል ዉስጥና ከክፍል ዉጪ መለማመድና መገልገል በጣም አስፈላጊ እንደሆነና ከነዚህ ክሂሎች ዉስጥ ለአንዱ ወይም ለሁለቱ ብቻ ትኩረት ሰጥቶ ሌሎቹን ክሂሎች ችላ ማለት ከቋንቋ ትምህርት አላማ አኳያ የሚጠበቀዉን የባህሪ ለዉጥ ማምጣት እንደማይቻል ይገልፃሉ። በተጨማሪም Harmer (1995) በበኩላቸዉ የክፍል ዉስጥ የንግግር ተግባራት ተማሪዎች ራሳቸዉን በመግለፅ ችሎታቸዉን የሚያሳድጉበት ስለሆነ የቋንቋዉን ትምህርት ዋነኛ አካል በመሆኑ በተገቢዉ መንገድ ሊሰጥ እንደሚገባ ይገልፃሉ። ስለዚህ የንግግር ክሂል የማስተማር ሰነ ዘዴ በክፍል ዉስጥ ያለዉ ሂደት በተለይ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የሚያዳብሩበት ሁኔታ ትኩረት የሚሰጠዉ ጉዳይ ነዉ።

የንግግር ልዉዉጥ በህግ የሚመራ የሚከናወንበት የራሱ ሥርዓት ያለዉ ነዉ። በህግ የሚመራ ነው ሲባል ተሳታፊዎቹ ተራ ጠብቀዉ ይናገራሉ፤ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይጠቁማሉ፤ለችግሩም መፍትሄ ይሰጣሉ፤የንግግርን ግጥምጥምነት ይጠብቃሉ፤ ወዘተ ለምሳሌ;- የስነ-ልቦና ችግር ያለበት ሰዉ ትክክለኛዉን የንግግር ልዉዉጥ ህግ በመጣስ መስተጋብሩን ትቶ ለብቻዉ ያወራል፤ለተጠየቀዉም ጥያቄ ትክክለኛዉን ምላሽ አይሰጥም፤ ከርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት የሌለዉ ነገርም ይናገራል። ቀደም ብሎ እንደተገለፀዉ ጤነኞቹ ሰዎች በዚህ መልኩ የንግግር ልዉዉጡን አለማድረጋቸዉ ደግሞ ለህጉ መኖር አስረጂ ይሆናሉ። በመሆኑም መምህሩ የንግግር ማስተማር ዘዴዉን በክፍል ዉስጥ ለመተግበር ሲያስብ ህጎችን በጠበቀ መልኩ መሆኑን ተገንዝቦና የተማሪዎችንም ቅድመ ዳራ መዳሰስ እንደሚገባዉ ጠንቅቆ ማወቅ ይኖርበታል Cook (1989) በማለት ይገልፀዋል።

ከላይ በተለያዩ የመስኩ ምሁራን እንደተገለፀዉ የመናገር ክሂል ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለመመስረትና አዎንታዊ ተግባሮቻችንን ለማከናወን ጉልህ ድርሻ የሚያበረክት ቢሆንም ክሂሉን ለማዳበር የሚረዱ ተግባራትን በማስተማሪያ መሳሪያዎች በማካተትም ሆነ በክፍል ዉስጥ አተገባበሩን በሚመለከት በተለይ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዉስጥ ምን እንደሚመስል መፈተሹ፤ ችግሮች ካሉ ሊሻሻል የሚችልበትን ሁኒታ መጠቆም ይገባል።

በመሆኑም ይህ ጥናት መምህራን የመናገር ክሂልን የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት ( ያለምንም ፍርሃት ) መግለጽ እንዲችሉ፣ አንደበተ ርዕቱ ተናጋሪዎች እንዲሆኑ፣ በውይይት እራሳቸውን አጉልተው እንዲያሳዩ ፣ የራሳቸው ቋንቋ ከሌሎች

ቋንቋዎችጋር ያለውን ልዩነት መፈተሽ እንዲችሉ እና በተስማሩበት የስራ መስክ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል እንደሆነ ይመረምራል፡፡

## 1.2 የጥናቱ መነሻ

የጥናቱ አቅራቢ ለዚህ ጥናት መነሻ የሆነዉ በስራዉ አለም ባካበተዉ ልምድ ለመገንዘብ እንደቻለው ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት በንግግር ክሂል ከሚያሳዩት ደካማ ግብረ መልስ በመነሳት እና መምህራኑ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የመናገር ክሂል መልመጃዎች በአግባቡ መተግበር ወይም አለመተግበራቸውን በተደረገው የዳሰሳ ጥናት መሰረት በማድረግ ነዉ፡፡ ጥናቱ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂላቸው አተገባበር ምን ያህል ነዉ? የመምህር ተማሪ ተራክቦዉ ቅርፅ ምን ይመስላል የሚሉትን ጥያቄዎች መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑን አጥኚዉ ስላመነበት ነዉ፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ምን እንደሚመስል መመርመር ነዉ፡፡ ይህ አብይ አላማም የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት እነሱም፡-

1. መምህራን የመናገር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ በአቀራረብ ደረጃ ምን ያህል እንደሚተገብሯቸው መፈተሽ ፧
2. መምህራን የመናገር ክሂል ትምህርትን ሲተገብሩ የልምምዱን ሂደት መመርመር፧
3. የመናገር ክሂል ትምህርት ሲተገብር በአፍልቆት ወቅት የሚታየውን ውጤት መፈተሽ፧

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

መምህራን የመናገር ክሂልን የክፍል ውስጥ አተገባበር ተገንዝበው ለትምህርቱ መቃናት አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያርጉ ይህ ጥናት ያበረታታል ፡፡ ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሚታዎች ይኖሩታል የሚል ግምት አለ፡-

- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂልን ሲተገብሩ የራሳቸዉን ዕዉቀት በመጨመር ለተማሪዎቻቸዉ ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥቆማ ይሰጣል፡፡
- ለወደፊቱ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ ስለ አተገባበሩ ለመማሪያ መሣሪያ አዘጋጆች መርጃ በመስጠት ድጋፍ እንዲሆን ይረዳል፡፡
- በዚህ ጥናት ዙሪያ ምርምር ለሚያከናዉኑ መነሻ ሃሳብ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚካሄደዉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ በሚገኙ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስር በለም 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤ በበሻሌ 2ኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት ፤ በዶክተር ሀዲስ አለማየሁ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በቦሌ ህብረተሰብ 2ኛ ደረጃ ትምህር ቤት ነዉ። ጥናቱም የሚያተኩረዉ በ 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር ላይ ሲሆን የዚህ ክፍል መምህራንና ተማሪዎች የጥናቱ ተተኳሪ ይሆናሉ።

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

## 2.1. የመናገር ክሂል ጽንሰ ሀሳብ

ንግግር የሰው ልጅ ፍላጎቱን ስሜቱንና አመለካከቱን ለሌላ ሁለተኛ አካል የሚያስተላልፍበት መስተጋብራዊ ሂደት ነው፡፡ ስለሆነም የመናገር ክሂል የማዳመጥን ምላሽ የሚፈልግ በመሆኑ ከማዳመጥ ክሂል ጋር በጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ንግግርን ለማጎልበት የሚያስችሉ ተግባራት በአብዛኛው ተማሪው ላይ የሚያተኩሩ መሆን አለባቸው፡፡ Pressley ( 2007:236) ንግግር ማስተማር የሚቻለው አስተማሪው ብቻ እየተናገረ ሳይሆን አብዛኛውን የንግግር ጊዜ በመጠቀም ተማሪዎች እየተናገሩ ከንግግራቸው መማር ሲችሉ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

ንግግር ከአራቱ በቋንቋ ክሂሎች ማለትም ከማዳመጥ፣ ከመናገር፣ ከማንበብና ከመጻፍ ውስጥ አንደኛውና በጣም አስፈላጊ ክሂል ነው፡፡ በመሆኑም የንግግር ክሂል ልምዱ የሚጀምረው ከቤተሰብና ከማህበረሰቡ ጋር በሚደረግ ግንኙነት እንዲሁም በትምህርት የሚዳብር ነው፡፡ Ur(1996፡120) ንግግር አእምሯዊ ወይም አካላዊ ችግር ከሌለ በስተቀር የማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር መግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡ ይህም ከሌሎች ክሂሎች ማለትም ከማንበብና ከመጻፍ የሚለይ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ Lewis and Sick (1993:9) ይህንኑ ሀሳብ ሲያጠናክሩ ንግግር ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ከፍተኛውን ቦታ የሚይዝ ነው፡፡ አንድ ሰው ቋንቋውን አወቀው የሚባለው መናገር ሲችልና በቋንቋው ሀሳቡን መግለጽ ሲችል ነው ይላሉ፡፡

ንግግር እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ የመግባቢያ መንገድ ነው፡፡ በመሆኑም ሰዎች ከቢጤያቸው ጋር በሚያደርጉት የመግባባት ሂደት መልእክታቸውን በሚያስተላልፉበት ጊዜ ስርዓቱን ጠብቀው በብቃትና በጥራት ሊገለገሉበት ይገባል ይህንን አስመልክተው ተስፋዬ (1981፡61) ሲገልጹ ንግግር ሲባል  እንደመጣ መቀባጠር ወይም መለፍለፍ አይደለም፡፡  ስሜት ያፈለቀውን ፣አይን የተመለከተውን፣ በንባብ የተገኘውን ፣ ውይይትና ጨዋታ የወለደውን ጉዳይ መነሻ በማድረግ ሀሳብን ለሌላው ማህበረሰብ ክፍል ወግና ስርአት ባለው ዘዴ ለማስደመጥ መሞከር ነው፡፡ አንድ ሰው አፉ ላይ የመጣለትን ሁሉ መናገር የለበትም ካልን ደግሞ ከመናገሩ በፊት ምንድን ነው የምናገረው? መቼ ነው የምናገረው? እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በማሰብ ዝግጅት እንዲያደርግ ግድ ይለዋል፡፡

በድሉ(2007፡85) ንግግር በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚከናወን የሁለትዮሽ ሂደት ነው፡፡ ማቀበያ ክሂል የሆነው የንግግር ክሂል ይዳብር ዘንድ መቀበያ የሆነው የማዳመጥ ክሂል መዳበር አለበት፡ የሁለቱ ክሂሎች መዳበር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ በመሆኑም የንግግር ክሂል ስናከናውን የማዳመጥ ክሂልንም በተዘዋዋሪ ይከናወናል ማለት ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

Bygate (1987:11) አንድ ሰው ንግግር ይችላል የሚባለው ከአንደበቱ ቅላፄና ምት ያለው ቃላትን ማውጣት በመቻሉ ሳይሆን በተነሳበት ጉዳይ የሚውሉና ሀሳቡን በትክክል ሊያስተላልፉለት የሚችሉ ቃላት መምረጥ ሲችል ነው፡ ቃላትን በሚመርጥበት ጊዜ ይህ ቃል በዚህ ሰአት ብናገረው የአድማጭን ስሜት ሊይዝልኝ ይችላል ወይ? የተነሳሁበትን አላማ ሳያደፈርስ አጥርቶ ሊያስተላልፍልኝ የሚችል ቃል ነው ወይ? የሚሉትን ማሰብ ይኖርበታል በማለት ገልጸዋል፡፡ Bygate ( 1987:108) በተጨማሪም ሲያብራሩ በአራቱ የክሂል ዘርፎች መካከል ጥብቅ ግንኙነት አለ የምንልበት ምክንያት አንዱን ክሂል በምናስተምርበት ጊዜ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ሁሉንም ክሂሎች ለማስተማር ስለምንገደድ ነው፡፡ እንዲሁም የንግግር ክሂል ከሌሎች ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ቢኖረውም የራሱ የሆነ መለያ ባህሪም አለው፡፡ አንድ የንግግር አቅራቢ ስለ አንድ ጉዳይ በሚናገርበት ጊዜ የሚጠቀምባቸው ዓረፍተ ነገሮች ባብዛኛው አጫጭር ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ የቃላት አመራረጡና የሰዋሰው አጠቃቀሙ ባመዛኙ ይሳኩለታል፡፡ መልእክቱም በሚገባ ሊተላለፍ ይችላል በማለት ገልጸዋል፡፡

## 2.2. የመናገር ክሂልን የማስተማር አላማ

Bygate (1987:3) የቋንቋ መዋቅርን ማወቅና በቋንቋው ለመገልገል የሚያበቃ ክሂል መኖር ንግግርን የመማር አላማን ለማሳካት ጠቃሚ ነው፡፡ የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ ከማስተማር አላማዎች አንዱ ተማሪዎች በተለያዩ አቅጣጫ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ ነው፡፡ የተማሪዎች የቋንቋ እውቀታቸው የሚመዘነው በታላሚው ቋንቋ ለመማር፣ ለመናገርና ሀሳብ ለመለዋወጥ ያላቸውን ብቃት በተሳትፎ ሊያሳድጉ ሲችሉ ነው፡፡ ተማሪዎች በቋንቋ ክፍለ ጊዜ ንግግር እንዲማሩ ሁኔታዎች ካልተመቻቸላቸው ለትምህርት ያላቸው ፍላጎት ከመቀነሱም በላይ ንቁ ተሳታፊ አይሆኑም፡፡ በመሆኑም መምህራን ንግግር የሚያስተምሩበትን ምክንያት ለይተው ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ የንግግርን ዓላማ ለማስተማር ምክንያት ከሚሆኑት ነጥቦች መካከል ተማሪዎች፡-

- የንግግር ድምጾችንና የድምጽ ቅንብሮችን መፍጠር እንዲችሉ፤
- የቃላትንና የዓረፍተ ነገር ጥብቀትና ቃናን በቋንቋ ውስጥ መጠቀም እንዲችሉ፤
- ተገቢ ቃላትንና ዓረፍተ ነገሮችን በተገቢው አውድ እና የመነጋገሪያ ርዕስ ዙሪያ በማድረግ መገልገል እንዲችሉ፤
- ሀሳብን በተጠየቃዊ ቅደም ተከተልና ትርጉማዊ በሆነ መንገድ ማቀናበር እንዲችሉ፤
- ቋንቋን በፍጥነትና በራስ መተማመን እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ነው በማለት ገልጸዋል።

Paul Nation (1990) ተማሪዎች በድግግሞሽ አንድን የተጠና ንግግር ሲለማመዱ እንዴት ክሂላቸውን እንደሚያሻሽሉ ማወቅ ይገባቸዋል። በዚህም ልምምድ ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ክህሎትን ከድግግሞሽ የንግግር ልምምድ ሊያሻሽሉ መቻላቸውን ይገልጻሉ። የንግግር ልምምድ በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ብዙ ግቦች አሉት። እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡-

- የትምህርቱን ፍሬ ነገር መማር
- ከሌሎች ተሳታፊዎች ስለ ቋንቋ አይነት መረዳት
- አንደበት ርዕቱነትን ማዳበር
- ተግባቦታዊ ዘዴዎችን መማር
- የንግግር ክህሎትን ማዳበር ናቸው።

Harmer (2007:123) የመናገር ክሂል ትምህርት ሲተገበር ተማሪዎችም በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ የምንፈልግባቸውን ሶስት ምክንያቶች እንደሚከተለው ጠቅሰዋል።

- የመናገር ክሂል ተግባራት የልምምድ እድሎችን ማለትም በእውኑ ዓለም ንግግር የሚያገለግል የልምምድ እድል በክፍል ውስጥ ስለሚሰጡ፤
- ተማሪዎች የሚገለገሉባቸው የመናገር ክሂል ተግባራት ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ሁሉም ምን ያህል ጥሩ እንደሰሩ፣ ምን ያህል ስኬታማ እንደሆኑና ምን አይነት የቋንቋ ችግር እንዳጋጠማቸው ስለሚለዩበት፤
- ተማሪዎች በአእምሯቸው ያከማቿቸውን የቋንቋ ቅርፆችን የመገልገል ችሎታቸው ስለሚጨምር ይህም ቃላትና ሀረጋትን ያለምንም ጭንቀት በጥሩ ሁኔታ መገልገል ስለሚያስችላቸው ነው።

በድሉ (2007:87) በሀገራችን አብዛኞቹ ተማሪዎች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁት ጥሩ ንግግር ችሎታ ሳያዳብሩ እንደሆነ ይገልጻሉ። በመሆኑም ከትምህርት ቤት

በኋላ ባለው ህይወታቸው ያለምንም ችግር ሀሳባቸውን በንግግር ለመግለጽ ይቸገራሉ፡፡ በራስ ያለመተማመን (አይናፋርነት)፣ መልእክትን በምክንያትና ውጤት አቀናጅቶ ያለማቅረብና የቋንቋውን ስርአት ያለመጠበቅ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ የማስተማር ዋና አላማም እነዚህን ንዑሳን ክሂሎች በማዳበር ተማሪዎች ጥሩ የመናገር ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡

የአፍልቆት ክሂል የሆነውን የመናገር ክሂልን የማስተማር ዋና አላማ የቋንቋ ፍሰትን ወደሚፈልገው ደረጃ ማድረስ እና የስኬታማ ቃላዊ ተግባቦት ክሂሎች ማሳደግ መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ በተጨማሪም አፈ-ፈት ተናጋሪዎች ቋንቋቸውን በአግባቡ እንዲችሉ የንበት፣ የሰዋሰው፣ የቃላት፣ የዲስኩር ወዘተ. እውቀት ( እነዚህ ችሎታዎች የአፈ-ፈት ተናጋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው) ሊኖራቸው ይገባል፡፡

አፈ-ፈት ወይም ብቃት ያላቸው የቋንቋ ተናጋሪዎች ቃላትን ማንበብ ማወቅ አለባቸው፡፡ ይህ እውቀት የድምጽ፣ የጥብቀት እና የቅላጼ ዘርፍን የሚሸፍን ሲሆን የቋንቋው ተናጋሪዎች ድምጾችን ማፍለቅ፣ ቃላትን የሚጠብቁበትን ቦታ መለየትና የተለያዩ ቅላፄዎችን ድምፀት ምንነት መረዳትና መጠቀም መቻልን ማወቅ ያካትታል፡፡ አንድ አፈ-ፈት ተናጋሪ ከንበት በተጨማሪ የቋንቋውን ሰዋስው ማወቅ አለበት በከፊል ንቁ የሆነ የሰዋሰው ህግ እውቀት ተናጋሪ ስፍር ቁጥር የሌላቸው አረፍተ ነገሮች እንዲያፈልቅ ያደርጉታል፡፡ ይህ በከፊል ንቁ የሆነ የቋንቋ ህግ እውቀት አፈ-ፈት ተናጋሪ ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ያላቸው አረፍተ ነገሮችን ማፍለቅ እንዲችል ይረዳዋል ማለት ነው፡፡ አፈ-ፈት ተናጋሪዎች የቃላት እውቀት ሊኖራቸው ይገባል፤ የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ማወቅ ለአንድ ብቃት ያለው የቋንቋ ተናጋሪ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ አፈ-ፈት ተናጋሪዎች ቃላትን በጥሬ ፍቺያቸው ብቻ ሳይሆን በሚስጢራዊ ፍቻቸውም የሚሉትን ነገር መረዳት እንዳለባቸው Nunan (1991:32) ገልፀዋል፡፡

የመናገር ክሂል ማስተማርን Harmer (1995:15) ሊገልጹ ተማሪዎች በቋንቋ ተጠቅመው ሀሳባቸውን መግለጽ እንዲችሉ ዘመናዊ በሆነ የክፍል ውስጥ የማስተማር ዘዴ ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በዚህም በቋንቋው የመጠቀም ችሎታቸውን ያዳብሩ ዘንድ አስፈላጊው ሁሉ ሊደረግ ይገባል፡፡ በመሆኑም የሚከተሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል፡-

- ተገቢ ቃላትን በተገቢው ቦታ መጠቀም እንዲችሉ፤
- አስተያየቶቻቸውን በማስረጃ አስደግፈው ማቅረብ እንዲችሉ፤
- ግላዊ አመለካከቶቻቸውን በንግግር ነጻ ሆነው እንዲገልጹ፤

- ኢ-መደበኛ የአነጋገር ስልት አስወግደው መደበኛ የአነጋገር ስልት እንዲጠቀሙ ይረዳቸዋል በማለት ገልጸዋል፡፡

## 2.3. የመናገር ክሂልን መማር

Harmer (1995:15) የንግግር ክሂል ስንማር ሀሳባችንን ለመግለጽ ፣ ለማስተላለፍ፣ ለማብራራት የምንጠቀምበት ክሂል ሲሆን፣ ከማዳመጥ ክሂል ቀጥሎ አብዛኛውን ጊዜያችን የምናጠፋው በዚሁ ክሂል መሆኑ ይገልጻሉ፡፡ሰዎች ሁለተኛ ቋንቋቸውን ሲማሩ ማወቅና ይበልጥ መገልገል የሚፈልጉት በንግግር ነው፡፡ በመሆኑም በማንኛውም እንቅስቃሴያቸው ውስጥ ሰፊ ቦታ የሚሰጠው ሲሆን በተገቢው መንገድና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ማስተማር ተገቢ ነው፡፡ እንዲሁም የንግግር ክሂል የተለያዩ ማህበራዊና ትምህርታዊ ፋይዳዎች እንዳሉት ይጠቅሳሉ ከነዚህም ውስጥ፡-

- በርካታ የቋንቋ እውቀት ለመቅሰም ያስችላል፤
- በንባብና ጽህፈት ክሂሎች እድገት አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያመጣል፤
- ተማሪው የሚማረውን ቋንቋ ንበት፣ ሚና፣ የድምጾችን አወጣጥ ለማወቅ እና
- ከተሻለ ማህበራዊ ደረጃ ላይ ለመድረስ ፋይዳዎች አሉት፡፡

Brum Fate (1984) ተማሪዎች የንግግር ክሂልን ሲለማመዱ አንደበት ርዕቱነታቸውን በአግባቡ እያሻሻሉ ይሄዳሉ፡፡ በልምምዱ ወቅትም በየመሀሉ ምን ልናገር ብሎ አያቆምም ወይም እንዴት ራሱን መግለጽ እንዳለበት አይቸገርም፡፡ ይህ አንደበተ ርዕቱነት መሰረት የሚያደርገው የቋንቋውን የቃላት አገባብ ዘዴዎችን በደንብ በመጠቀም በቋንቋው መግባባት መቻልን ያስችላል፡፡ እንዲሁም የአንድ ተማሪ እንደበተርዕቱነት የሚለካው ቋንቋን ቶሎ በመናገር እና የቋንቋው የቃላት አሰካክ፣ የቋንቋውን ሂደት የመቆጣጠር ብቃት እና የቋንቋ ሰዋስዋዊ አገባብን በአግባቡ መጠቀም ሲችል ነው፡፡ እንዲሁም መምህሩም እንደበተርእቱነትን ለማሳደግ በልምምድ ወቅት የተለያዩ መልመጃዎን በትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል በማለት ገልጸዋል፡፡

## 2.4. የመናገር ክሂልን የማስተማር አቀራረብ

ተግባቦታዊ አቀራረብ ተማሪዎች በቋንቋው ተጠቅመው በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ውስጥ ሀሳባቸውን ለመግለጽና አከባቢያቸውን ለመመርመር ያስችላቸው ዘንድ በቂ ልምምድ የሚሰጥ ነው በማለት Richards (1994:2) ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የተማሪው መስተጋብር እንዲጨምር

በማድረግ በተጨባጭ ያለውን ሁኔታ በክፍል ውስጥ በማምጣት ተነሳሽነታቸውንና ፍላጎታቸውን ባገናዘበ መንገድ ተማሪዎች እንዲናገሩ በመርዳት ተግባቦታዊ ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎ የሚከናወኑበት ሂደት ነው ብለዋል፡፡

በተግባቦታዊ አቀራረብ የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ አብዛኛውን ጊዜ ግልጋሎታዊውም ሆነ ስነልሳናዊ አላማው ከተማሪው ፍላጎት ችሎታ አኳያ የተለያዩ ተግባራትን ይቀርጻል፡፡ ብዙውን ጊዜ ስራው የሚከናወነው በቡድን ወይም በጥንድ ሀሳብ መረዳት እንዲችሉ፣ እንዲከራከሩ፣ እንዲወያዩ ወዘተ... የሚያግዝ ልውውጥ በተገቢው ሁኔታ መካሄድን ነው፡፡ ይህም የንግግር ክሂልን ለማስተማር በከፍተኛ ደረጃ ሁኔታዎችን ያመቻቻል በማለት Richards (1994:71) ያስገነዝባሉ፡፡ እኚሁ ምሁር ተግባቦታዊ አቀራረብን የመናገር ክሂል ከማዳበር አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ሲገልጹ፡-

- ጥሩ አድማጭ መሆን ጥሩ ተናጋሪ መሆንን፤
- ከሰዎች ጋር ሀሳብ በሀሳብ መለዋወጥን፤
- ሰዎች ሲጠይቁ አገናዝቦ መመለስን፤
- ተረቶችን፣ አፈታሪኮችን፣ ዘዴዎችን፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን፣ መናገርና በንግግርም ጣልቃ ማስገባትን፤
- ጭውውቶችን ማራኪ በሆነ መንገድ ማቅረብን፤
- በክርክር፣ በውይይት፣ በተለያዩ ምርምሮች ላይ በተወሰነ ርዕስ ላይ የመናገርን፤
- መልእክት አስተላላፊውን ሰው በጥንቃቄ በመከታተል መስማማቱን ወይም መቃወሙን ወይም ሌሎች መረጃዎችን መጨመርን ወዘተ... ያካተተ ጠቀሜታ አለው ብለዋል፡፡ በአጠቃላይ ተግባቦታዊ አቀራረብ “ቋንቋ መግባቢያ ነው” የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ በውስጡ የያዘ በመሆኑ ተማሪዎች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚደረገውን እንቅስቃሴ፣ ባህል፣ ወግና ልማድ ተንተርሰው ሀሳባቸውን እንዲገልጹ የሚያበረታታ ነው፡፡

አንድ የቋንቋ መምህር ንግግርን ከማህበራዊና ተግባራዊ ማነቃቂያ ጋር አያይዞ ማስተማር ሌላው ጉዳይ ነው፡፡ ተግባራዊ ንግግር ስናስተምር ተማሪዎች የመረጃ ልውውጥ እንዲያደርጉ ወይም እዚያው ክፍል ውስጥ ሊተገበሩ የሚችሉ ስራዎችን ማከናወን ይችላል፡፡ ሌላው ተማሪዎች ማህበራዊ ግንኙነታቸውን እንዴት አድርገው እንደሚመሰረቱ እና በክፍል ውስጥም በምንመልኩ እንደሚተገብሩት ማስተማርና ከክፍል ውጪም ባለው ሕይወታቸው ጠቃሚ መሆኑን ማስተማር፤ ይህም ሲሆን ከጓደኞቻቸው ጋር ከቤተሰብ አባላት ጋር በውይይት መልክ እንዲተገብሩት ማድረግ ነው በማለት Brown & Yule (1983) ገልጸዋል፡፡ ይህንኑ ጉዳይ

አብራርተው ሲገልጹ መምህራኖች የእነዚህን ልዩነትና ጠቀሜታ ለተማሪዎች እንዲለዩ መስጠትና ለይተው እንዲያብራሩ ማድረግ ግድ ይላል፡፡

ቋንቋ በማስተማር ሂደት ውስጥ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በመግለጽ እንዲሁም የመምህሩ ተግባር እንደ መረጃ አቀባይ መሆን ነው፡፡ መምህሩ የተለያዩ አዳዲስ መረጃ መሳሪያዎችን በመጠቀምና በተቻለ መጠን በታላሚው ቋንቋ የሚቀርበውን ተግባር ግልጽና በማይረሳ መልኩ ማቅረብ አለበት፣ በዚህ ሁኔታ ከሆነ ተማሪዎ አዳምጠው መገንዘብ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን መምህሩ የሚቀርበውን ነገር አሳምራለሁ በማለት ብዙ ጊዜውን በዚህ ደረጃ ማጥፋት የለበትም፡፡

Byrne (1987፡ 34) እንደሚያስረዱት በዚህ ደረጃ የንግግር ትምህርት በምንባብ መልክ ወይም በምልልስ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ለምሳሌ መምህሩ ውይይትን በማስተማሪያነት ለመጠቀም ከፈለገ በቅድሚያ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ወይም ሌሎች ሰዎች ሲወያዩ የሚያሳይ ይዘት ማቅረበ ወይም ከዕለቱ ምንባብ ርዕስ ጋር የተያያዙ አጫጭር ምንባቦችን በማምጣት ወይም በምልልስ ሊያቀርባቸው ይገባል፡፡ መምህሩ በዚህ ደረጃ የሚያቀርበው አዲስ የንግግር ትምህርት ከሁለት መመዘኛ አንፃር ሊመለከተው ይገባል፡፡ የመጀመሪያው በዚህ ደረጃ ብዙ ጊዜ ማጥፋት የማያስፈልግ መሆኑን፣ ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎች ቀጣይ የሚቀርበውን የትምህርት ይዘት ክንዋኔዎች እንዲፈጽሙ የሚያስችላቸው ነውን? የሚለውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም በምልልስ መልክ የሚቀርበው ነገር:-

- የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ሊያሳድግ የሚችል አግባብነት ያለው ቋንቋ መጠቀም፣
- አጭር መልስ የሚፈልግ ተስማሚ የሆነ ሀሳብ፣
- በእውነታው ዓለም ሊደረግ የሚችል መሆን፣ ለምሳሌ፣ ከተማሪዎች እድሜ እና የክፍል ደረጃ ጋር ተመጣጣኝነት ያለው የንግግር ተግባር፣
- በዚህ ደረጃ ብዙ ጊዜ መጥፋት ስለሌለበት ምልልሱ ያልረዘመ ተግባር እና
- ምልልሱ ተማሪዎችን ሊስብ እና ወደ ልምምድ ተግባር ሊመራ የሚችል መሆን ይገባዋል፡

## 2.5 የመናገር ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት

ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ የሆነውን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ሊያሳትፉ የሚችሉ ተግባራትን መቅረፅ ያስፈልጋል፡፡ Harmer (2007: 55) እንደሚሉት ጥሩ የመናገር ክሂል ተግባራት ሲዘጋጅ ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ በትምህርቱ እንዲሳተፉ ዕድል

የሚሰጡና ከልምምዱ በኋላ የመምህሩ ምጋቤ ምላሽ ግምት ውስጥ የሚያስገቡ ከሆኑ ተማሪዎች በትምህርቱ እርካታ ያገኛሉ፡፡ ይህም ተማሪዎች የታለመውን አላማ በቀላሉ እንዲደርሱበት ይረዳል፡፡ ተግባራቱ ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፉ ከሆነ ክፍሉ ያለምንም ችግር ተግባቦቱ የሰመረይሆናል ይህ ደግሞ ተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜት ከፍ በማድረግ በንግግር ሀሳብን መግለፅ የቋንቋ ትምህርት ክፍል ባህል እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ የመናገር ክሂልን እንደክሂል ተማሪዎች እንዲያዳብሩት የሚረዱ ተግባራት በተለያዩ ምሁራን ስራዎች ውስጥ የተጠቀሱ ሲሆን Harmer (2007:129) ሲገልፁ የመረጃ ክፍተት ተግባራት አቅጣጫን ማሳየት፣ የነገሮችን (የስዕሎችን) ልዩነት መግለፅ፣ በሰንጠረዥ መልክ የቀረቡ መረጃዎችን ማሟላት ላይ ስለሚመሰረቱ ተግባራቱ የውስብስብነት ባህሪ አይታይባቸውም፡፡ ይህም ባህሪያቸው ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቀላሉ እንዲገልፁ ይረዳቸዋል፡፡ ተረታተረቶች (ታሪኮች) ደግሞ የልጆችን ባህሪ ከመቅረፅ ባሻገር የልጆችን ስሜት የማነሳሳት ኃይላቸው ከፍተኛ ስለሆነ በዝቅተኛ ክፍሎች መጠቀሙ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም በድሉ ዋቅጅራ (2007፣ 92-93) ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የንግግር ተግባር ላይ ከመሳተፋቸው አስቀድሞ ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ቅድመ ንግግር ተግባራት አሉ ይላሉ፡፡ እነዚህ የቅድመ ንግግር ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ንግግር የሚደረግበትን ርዕሰ ጉዳይ መወሰን ወይም መምረጥ፣
- በተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ መረጃዎችን መሰብሰብ፣
- ንግግር የሚደረግበትን ዓላማ ማወቅ
- አድማጭን መወሰን
- ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ማስፈር

እንዲሁም የቅድመ ተግባራትን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ንግግር ተግባር ይገባሉ፡፡ የሚከተሉት ተግባራት ተማሪዎች በንግግር ሂደት ላይ እያሉ ትኩረት ሊያደርጉባቸው የሚገቡ ናቸው፡፡

- በንግግሩ መጀመሪያ ርዕሱን ለአድማጭ በሚገባ ማስተዋወቅ፣
- የንግግሩን ዓላማ ባጭሩ ማስተዋወቅ፣
- የአድማጭን ስሜትና ፍላጐት መጠበቅ፣
- አድማጭን በዓይን መቃኘት፣
- የስሙኝ ልንገራችሁ ዓይነት አቀራረብን በማስወገድ የአድማጮችን ምላሽ መቀበል፣
- መረጃ መሣሪያ ካስፈለገን መጠቀም፣

- ንግግርን ሳቢ አድርጐ ማቅረበ (በድምፅ አወራረድ እና በአካል እንቅስቃሴ አድማጭን ለመሳብ ጥረት ማድረግ)፣
- ከአድማጭ የሚመጡ ጥያቄዎችን በቅደም ተከተል በማስታወሻ መያዝ፣
- ለተጠየቁ ጥያቄዎች ገለፃ መስጠት እና ማጠቃለል፣
- በንግግሩ መጨረሻ ምስጋና ማቅረብ፣

የድህረ ንግግር ተግባር ተናጋሪዎች አድማጮቻቸው ምን ያህል መልዕክቱን እንደተረዱ የሚገመግሙበት ነው፡፡ ይህ የተወሰኑትን አድማጮች በዘፈቀደ በመምረጥ የንግግሩን ፍሬ ሃሳብ አስመልክቶ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ለማድረግ ሊካሄድ ይችላል በድሉ (2007:93)፡፡

ንግግር በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚደረግ የሁለትዮሽ ሂደት ሲሆን ይህንን ክሂል ለማዳበር የሚዘጋጁ መልመጃዎች የመማር ማስተማሩን ሂደት ከመምህር መር አቀራረብ በማላቀቅ የተማሪዎችን መስተጋብራዊ ግንኙነት የሚያበረታቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ስለሆነም ተግባራቱ ተማሪዎችን በጥንድ፣ በሶስትዮሽና በቡድን የሚያሳትፉና በራስ የመተማመን ስሜት በማዳበር ሀሳባቸውን እንዲገልፁ የሚያግዙ ሊሆኑ ይገባል፡፡ Ur (1996: 120) የመናገር ክሂል ተግባራት እንደሚከተለው አስቀምጠዋል፡፡

1. ብዙውን ጊዜ ተማሪዎች እንዲናገሩ ማድረግ፦ በተቻለ መጠን ለንግግር ተግባር የተሰጠው ጊዜ በተማሪዎች ንግግር መሸፈን ይኖርበታል፣ ጉዳዩ ግልፅ ሆኖ እያለ ግን የክፍል ውስጥ ክንውን አብዛኛውን ጊዜ በመምህሩ ይሸፈናል፡፡ ስለዚህ የመምህሩን ሚና በመቀነስ የተማሪዎች መስተጋብራዊ ግንኙነት ጐልቶ እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
2. ሁሉን ያማከለ ተሳትፎ፦ የክፍል ውስጥ ክንውን ጥቂት ቁጥር ባለቸው ተማሪዎች ተፅእኖ ብቻ መውደቅ የለበትም ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች የመናገር እድል ሊሰጣቸው እና ተሳትፎዋቸው የተመጣጠነ ሊሆን ይገባል፡፡
3. ከፍተኛ ተነሳሽነት፦ ተማሪዎች ለመናገር የሚነሳሱት በተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ከፍተኛ ፍላጐት ሲኖራቸው እና ስለ ርዕሰ ጉዳዩ የሚናገሩት አዲስ ሐሳብ ስለሚያጥርባቸው ነው፡፡ ወይም ደግሞ በሂደቱ ተሳትፎ በማድረግ ለንግግር ተግባር አላማ መሳካት አስተዋጽኦ ለማበርከት ነው፡፡ ስለዚህ ተግባራቱ የተማሪዎችን ተነሻሽነት የሚያሳድጉ ሊሆኑ ይገባል፡፡
4. የቋንቋ ቅቡልነት ደረጃ፦ ተማሪዎች ሀሳቦቻውን በንግግር ማለትም ተገቢነት ባለው መንገድ እርስ በርሳቸው መግባባት መቻላቸውንና ተቀባይነቱ ከፍ ባለ የቋንቋ ብቃት የመግለፅ አቅም ያላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ መምህራን ከላይ

የተጠቀሱትን የስኬታማ የንግግር ክሂል ባህሪያት እና በቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ ክንውን ወቅት መተግበር ከቻሉ ተማሪዎች የመናገር ክሂልን በቀላሉ ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡

ከላይ በምሁራኑ እንደተጠቀሰው የንግግር ተግባር ሲከናወን መምህራኑ ለተማሪዎቹ ግልጽ የሆነ መመሪያ በመስጠት ክፍለ ጊዜውን ተማሪዎቹ በአግባቡ እብዲጠቀሙበት በማድረግ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡

## 2.5.1 ጨዋታዎች

Sesnan (1997:116) "ጨዋታዎች ደስታ እየፈጠሩ የልጆችን የቋንቋ ችሎታ ለማሻሻል ይረዳሉ" ይላሉ፡፡ ጨዋታዎች በባህሪያቸው የየራሳቸው ህግና ደንብ የሚኖራቸው ውድድርን እና ትብብርን የሚጠይቁ ሁለቱንም አካተው የሚይዙ ናቸው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎችን በቡድን ማደራጀት፣ ለጨዋታው ግልፅ ህግ ማዘጋጀት፣የጨዋታው አሸናፊዎች እስከሚታወቁበት የመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ድረስ ሂደቱ ሁሉንም የቡድኑን አባላት የሚያሳትፍ መሆኑን ማወቅ፤ ተሸናፊዎች ከጨዋታው ውጭ ከሆኑ በኋላ እንደገና ወደጨዋታው የሚመለሱበት ህግ መኖሩን ማረጋገጥ፣ ወይም ጨዋታውን አሳጥሮ ቶሎ እንዲያልቅ ማድረግ ከጨዋታው በፊት የሚታሰብባቸቸው ጉዳዮች እንደሆኑ አስገንዝበዋል፡፡ ስለዚህ ልጆች ጨዋታዎችን እየተጫወቱ እግረ መንገዳቸውን የቋንቋ ችሎታቸውን ማሳደግ ይችሉ ዘንድ የመለማመጃ ተግባራቱ እንዴት እንደሚከናወኑ ዝርዝር መመሪያዎችን መምህሩ በቅድሚያ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

ጨዋታዎች በተለይ ለታዳጊዎች ጠቃሚዎች ሲሆኑ በሁለም የዕድሜ ክልል ባሉ ተማሪዎች ተወዳጅ ናቸው፡፡ የተለያዩ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል ውስጥ ጨዋታዎች ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም የተወሰኑ ተማሪዎች ጨዋታውን ሲችሉ ሌሎች ደግሞ ጨዋታውን ፈፅሞ ሰምተውት የማያውቁት ሊሆንባቸው ይችላል፡፡ ይህም የጨዋታዎች ውስንነት መሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም መምህሩ ጨዋታዎችን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ሲያስብ የተማሪዎችን የዕድሜ፣ የባህል እና የቅድመ እውቀታቸውን በመረዳት ችግሩን መፍታት ይጠበበታል፡፡

## 2.5.2 ችግሮችን አፍልቆ መፍትሔ መሻት

ተማሪዎች አንድን ሚና ተክተው የሚጫወቱት ተግባር ሳይሆን ችግሮችን በሀሳባቸው አፍልቀው የችግሮቹን አስገዳጅ ሁኔታዎች በቡድን የሚመረምሩበት ነው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች የተወሰኑ ችግሮችን በማንሳት ለችግሮቹ መፍትሄ ወይም ውሳኔ ለመስጠት የሚሞክሩበት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ተማሪዎች እራሳቸው ማህበራዊ ሚና እንዳላቸው በመቁጠር

በህብረተሰቡ ዘንድ ያሉ ችግሮችን በማንሳት የወደፊቱን እንዲተነብዩ፣ የሚያመጣውን ችግር እንዲያስቀምጡ፣ እርስ በርስ እንዲወያዩ፣ አንድ ሃሳብ ላይ እንዲደርሱ ያደርጋቸዋል። በተጨማሪም አንድን ችግር ለመፍታት የሚደረግ ህዝባዊ ውይይት ማካሄድ ለዚህ ተግባር ጥሩ ምሳሌዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ምሁሩ ጠቅሰዋል። ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የዚህ ተግባር ዋና አላማ ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ችግሮች ከመፍታት ባለፈ ሳይታወቃቸው እርስ በርስ በሚያደርጉት ተራክቦ የመናገር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ሲሆን ለመለማመጃ የሚቀርቡት ተግባራትም ለመምራት የተማሪዎችን ችሎታ ማገናዘብ ይኖርባቸዋል። ከላይ የቀረበውን ተግባር ለማከናውን ሦስት ደረጃዎችን መከተል አስፈላጊ እንደሆነ Beygate (1987:81) ይጠቅሳሉ። የመጀመሪያው አስፈላጊውን መረጃ የመስጫ ጊዜ ሲሆን ሁለተኛው ችግሩን ለመፍታት የሚከናወን ውይይት ነው የመጨረሻው ደረጃ ደግሞ የመምህሩ ክትትል ነው።

ይህንንም ለማየት እንደሞከረው እንደነዚህ አይነት መለማመጃዎች የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ከማዳበራቸውም በላይ የተማሪዎችን የችግር ፈቺነት አቅም ለማሳደግ ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ የክፍል ደረጃውን ያገናዘቡ መልመጃዎችን መርጦ በመስጠት እንዲለማመዱ ማድረግ ከመምህሩ ይጠበቃል።

## 2.5.3 ታሪክ መናገር

Harmer (2007: 129) ስለራሳችንና ስለሌሎች ሰዎች ታሪኮችን በመተረክ አብዛኛውን ጊዜአችንን እናጠፋለን። ስለሆነም ተማሪዎች በቋንቋቸው ታሪክ መናገር መለማመድ አለባቸው በማለት ሂደቱን እንደሚከተለው አቅርበዋል።
ተማሪዎች በቡድን በቡድን ይቀመጣሉ። ለእያንዳንዱ ቡድን ተከታታይነት ያላቸው መልዕክት አዘል ስዕሎች ይሰጣል ቡድኖቹ ስዕሎቹን ከተመለከቷቸው በኋላ ይሰበሰባሉ፣ ከዚያም ከመጀመሪያዎቹ ቡድኖች አንዳንድ አባል የያዙ ሌሎች አዳዲስ ቡድኖች ይደራጃሉ። አዲሶቹ ቡድኖችም ቀደም ሲል ያዩት ስዕላዊ መግለጫ ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፍ ይናገራሉ። በመጨረሻም እያንዳንዱ ቡድን የቀረበው ታሪክ ተመሳሳይ ሀሳብ የያዘ መሆኑን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ቡድኖች የየራሳቸውን ታሪክ ለክፍል ያቀርባሉ።

በሌላ በኩል ተማሪዎች ታሪክ እንዲናገሩ ለማለማመድ በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ተግባራት ለተገልጋዮች ህይወት ቅርበት ያላቸው መሆን እንደሚገባቸው Harmer (2007:130) እንዲህ ሲሉ ይገልፃሉ። "የተማሪዎችን የመተረክ ችሎታ ለማሳደግ የየራሳቸውን ሁኔታ ለምሳሌ

በሰውነታቸው ላይ ስላለ ጠባሳ፣ ስለፀጉራቸው፣ ስለጌጦቻቸው፣ ስለየትምህርት መሳሪያዎቻቸው፣ ስዕሎቻቸው ወይም ደግሞ ቀደም ሲል ስላሳለፉት በጎ ወይም መጥፎ ገጠመኝ ወዘተ እንዲተርኩ የሚያነሳሱ ጥያቄዎችን መምህሩ እንደ መነሻ ቢጠቀም ውጤቱ በጣም የተሻለ ይሆናል" ይላሉ፡፡ Sasnan (1997:116) ልጆች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ታሪክ እንዲናገሩ ማበረታታት አስፈላጊ መሆኑን በመጥቀስ የሚከተሉት አይነት ታሪኮችን እንዲናገሩ ማድረግ ጠቃሚነት እንዳለው ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ በፊት የሰሟቸውን ታሪኮች ደግመው እንዲናገሩ ማድረግ፣ የየራሳቸውን ታሪኮች ፈጥረው እንዲናገሩ ማበረታታት እና ስላዩአቸው ወይም ስለአከናወኗቸው ነገሮች ለክፍሉ እንዲናገሩ እድል መስጠት የልጆችን ችሎታ ለማሳዳግ ይረዳል፡፡ስለዚህ መምህራን በየቋንቋው በቃል የሚተረኩ ወይም በፅሑፍ የቀረቡ ታሪኮች የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ ያላቸውን ፋይዳ ተገንዝበው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚያቀርቡት ንግግር ታሪኮቹን በግብአትነት እንዲገለገሉባቸው በማድረግ የመናገር ክሂል አቀራረቡን ቀና እንደሚያደርገው በውል ሊገነዘቡት ይገባል፡፡

## 2.5.4 ሚና ጨዋታ

ተማሪዎች የአንድን ግለሰብ ሚና (ለምሳሌ የሱቅ ሻጭና ገዥ፣ የአንድን መምህርን የተማሪን ባህሪ ወዘተ) ተክተው የሚያከናውኑት ተግባር ሲሆን ሚና ጨዋታ ተማሪዎች ወክለው የተወኑትን ተግባር እንዲያስተውሉና ከአዳዲስ የቋንቋ አገላለፆች ጋር እንዲተዋወቁ ከመርዳቱም በላይ ተማሪዎች የቋንቋ ፍሰት ብቃታቸውን ማሻሻል እንዲችሉ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ መምህሩም የማሪዎችን ጥንካሬና ድክመት በመለየት መፍትሄ እንዲፈለግ ይረዳዋል፡፡ Gower R. Phllipes, D, and Walters, S. (1995: 105) የሚና ጨዋታን ፋይዳ ጠቅሰዋል፡፡ ቀለል ያሉ ሚና ጨዋታዎች (ለምሳሌ ሸቀጣሸቀጦችን ከሱቅ መግዛት፣ አቅጣጫን ማሳየት የመሳሰሉት በዝቅተኛ ደረጃ ላሉ ተማዎች በጣም ጠቃሚ ተግባራት ሲሆኑ ውስብስብ የሆኑ ሚና ጨዋታዎች ለምሳሌ በአንድ ታሪክ ወስጥ የተካተቱ ገፀ ባህሪያትን ወክሎ መጫወት) የከፍል ደረጃቸውን ከፍ ላሉ ተማሪዎች ተስማሚ እንዲሆኑ እኚሁ ምሁር አክለው ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ ለተማሪዎች የክፍል ደረጃ ተገቢነት ያላቸውን መልመጃዎች መርጦ በክፍል ውስጥ ማቅረብ የመምህራን ግዴታ ነው፡፡

መምህራን ሚናን ከተለያዩ ተግባራት ማለትም ከቀላል ምልልስ እስከ ውስብስብ ውክልናን ከተለያዩ ደረጃዎች ጋር በማያያዝ መተገበር ይችላሉ አንድን ሚና ወስዶ ተግባራዊ ማድረግ ለቋንቋ ንግግር ለዛ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡ ይህም ተግባር በጥንድ ወይም በቡድኖች

ማከናወን የተሻለ ውጤት ይታይበታል።ይህም የብዙ ተማሪዎች ተሳትፎ እንዲኖር ያበረታታል። የሚና ተግባራት በእውነተኛ ህይወት ላይ የተመሰረተ ሁኔታ ከሆነ ልምምዱ በጣም ጠቃሚ ነው አንዳንድ ተማሪዎች ሚናን መጫወት ለነፃ ውይይት ቀላል ሆኖ ያገኙታል። ምክንያቱም ተማሪዎች የዕውቀት እንቅፋት ስለ ማይገጥባቸው አንዳንድ ተማሪዎች ሌላውን ሰው መስለው ሲጫወቱ ይደሰታሉ። ግልፅ ግብ ያለው ሚና መጫወት ለነፃ ውይይት ዓላማና አቅጣጫ ያሳያሉ። የሚና ጨዋታ ውድድርና መተጋገዝን ያካትታል። ይህም ሳቢ ያደርገዋል። በተጨማሪም ተማሪዎች የተለያዩ ሚናዎችን በኘሮግራም ሲጫወቱ ቋንቋቸውን በተኀደኝ ይለማመዱሉ፤ያሻሽላሉ። የሚና ጨዋታ ሲቀርብ በተቻለ መጠን ለምሳሌ ማሳመን፣አለመስማማት፣ ቅሬታ ማቅረብ፣ መጋበዝ ወዘተ ቢሆን ለንግግር ክሂል መሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል Tricia Hedge. (1996: 278-280) በማለት ጠቅሰዋል።

## 2.5.5 ጭውውት

ጭውውት የንግግር ክሂልን ለማዳበር አንጻራዊ ተመራጭነት ያለው ዘዴ ነው። ተማሪዎች እንደየክፍል ደረጃቸው አግባብነት የተመረጡ ቅንጫቢዎችና በመጠቀም የሚያካሂዱት የጭውውት ተግባር እውነተኛ የንግግር ዓውድን ይፈጥራል። ለጭውውት የሚመረጠው ርዕሰ ጉዳይ አግባብነት የሚመዘነው ከርዕስ ጉዳይ ቅለትና ክብደት እንዲሁም ከተማሪዎች ዳራዊ እውቀት አንፃር ነው።

ከተማሪዎች ደረጃ ጋር ሲነጻጸር ቀላል የሆነ ርዕሰ ጉዳይ የተመረጠ እንደሆነ፤ ተማሪዎች ጭውውቱን የሚያካሂዱት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው፤ ስለጉዳዩ ያላቸውን ዕውቀትና አመለካከት ለመግለጽ ሳይሆን፤ በመምህሩ ስለታዘዙ ብቻ ይሆናል። በሌላ በኩል የተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ከተማሪዎች ደረጃ በላይ (ከባድ) ከሆነ ደግሞ፤ ተማሪዎቹ ስለጉዳዩ የሚኖራቸው ዕውቀት አነስተኛ ስለሚሆን የሚናገሩት እጅግ የተወሰ ነገር ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች የሚናገሩት ነገር ላይ ጥርጣሬ እንዲኖራቸውና በራስ የመተማመን ደረጃቸው ዝቅ እንዲል ያደርጋል በድሉ ዋቅጅራ(2007:94) በማለት ገልጸዋል።

## 2.5.6 ቃላዊ ሪፖርት

ይህ ዘዴ ተማሪዎች ያነበቡትንና ያዳመጡትን ጉዳይ በራሳቸው የቃላት አጠቃቀምና የአገላለጽ ችሎታ በንግግር የማያቀርቡበት ነው። ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ቃላዊ ሪፖርት በሚያቀርቡበት ጊዜ አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር መምህራን የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይኖርባቸዋል።

- ከክፍለ ጊዜው አስቀድሞ ተማሪዎች በቂ ዝግጅት ማድረጋቸውን ማረጋገጥ፤

- ለሪፖርቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን (የሰው እና የቦታ ስሞችን፤ ቁጥሮች፤ ቀንና ስዓቶችን)ብቻ በማስታወሻ እንዲይዙና ሌላውን ጉዳይ በቃል ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ፤
- ሪፖርቱ ከቀረበ በኋላ አድማጮች ያልገቧቸውን ጉዳይ እንዲጠይቁ ማድረግ፤
- አቅራቢው ለተጠየቁ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥ ማድረግ፤ በድሉ ዋቅጅራ (2007:95) በማለት ገልጸዋል፡፡

## 2.5.7 ውይይት

ውይይት ከፍተኛ ዝግጅትን የሚጠይቅ ሲሆን በክፍል ውስጥ ከተማሪዎች ጋር የሚደረግ ውይይት ውጤታማ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉትን ነጥቦች ማረጋገጥ ሲቻል እንደሆነ Gower R. Phllipes, D, and Walters, S(1995:107-108) አስረድተዋል፡፡

- የተማሪዎች በሚወያዩበት ርዕሰ ጉዳይ ሊቀሰቀሱና የሚናገሩት ሀሳብ ሲኖራቸው
- ተግባሩ በአደረጃጀቱ የመናገር ፍላጐት ለመፍጠር በቂ የሆነ የማነሳሳት አቅም ሲኖረው፣
- ተማሪዎች ለውይይት የቀረበውን ጉዳይ መግለፅ የሚያስችል የቋንቋ ችሎታ ሲኖራቸው
- ተማሪዎቹ ለውይይቱ ዝጉጁነትና ሀሳባቸውን ለማደራጀት የሚሰጠው ጊዜ ታሳቢነት
- የተግባሩ በሚፈለገው አግባብ መሄድ ማለትም ውይይቱ በተወሰኑ ተማሪዎች ተፅዕኖ አለመዋል

በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ውይይቶች ተማሪዎችን በማነሳሳት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድግ ከእድሜያቸውና ከችሎታቸው ጋር የሚጣጣሙ የመወያያ ይዘቶችን ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ Gower R. Phllipes, D, and Walters, S. (1995. 108-109) ውይይቶችን ለማነሳሳት ጠቃሚ መንገዶች ናቸው ብለው ከጠቀሷቸው ይዘቶች ውስጥ ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ሲመጥኑ የሚችሉ ይዘቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- አባባሎችን ማሻሻል፡- ለተማሪዎች በአንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ አከራካሪ አባባሎችን ዝርዝር በመስጠት በቡድን ተወያያተው ማሻሻያ እንዲያደርጉ ማድረግ ለምሳሌ፣ ወላጆች ወንድ ልጆቻቸውን የምግብ አዘገጃጀት፣ ሴት ልጆቻቸውን ደግሞ የመኪና አጠጋገን ማስተማር አለባቸው፡፡

- አባባሎችን መቃወም፡- የተለያዩ አከራካራ አባባሎች ለተማሪዎች በቁራጭ ወረቀት ላይ ፅፎ በመስጠት የመቃወሚያ ሀሳብ እንዲያዘጋጁ ጊዜ መስጠት ከዚያም ከመካከላቸው አወያይ መምረጥና እያንዳንዱ ተማሪ የመቃወሚያ ሀሳብ በየተራ እንዲያቀርብ ማድረግ ከላይ የመናገር ክሂልን ለማለማመድ ይረዳሉ ተብለው ከቀረቡት ተግባራት በተጨማሪ Harmer (2007:129-130) ይህንኑ በማጠናከር የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ማለማመድ የሚችሉ ተግባራትን ሲገልፁ፡-
- ተማሪዎች የሚፈልጉትን ርዕስ በመምረጥ እርስ በርስ ቃለ መጠይቅ እንዲደራረጉ ማድረግ
- ተማሪዎች የተለያዩ መረጃዎችን ሰብስበው በማደራጀትና በመለማመድ በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ማድረግ ወይም በቤታቸው ያነበቡትን  ቅንጫቢ ወይም ሙሉ ስራ በንግግር እንዲያቀርቡ ማድረግ፣
- ተማሪዎችን በቡድን በመመደብ ከሚደግፉት ሀሳብ አንፃር ወግነው እንዲከራከሩ ማድረግ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማዳበር ጥሩ የክፍል ውስጥ ተግባር ሲሆን ከንግግር ችሎታ በተጨማሪ የነገሮችን ተጠየቃዊ ግንኙነት የመመርመር ችሎታም ያዳብራሉ፡፡

ከላይ በተለያዩ ምሁራን የቀረቡት ነጥቦች እንደሚያመለክቱት በነጥብነት የቀረቡት ተግባራት የመናገር ክሂልን ለማለማመድ ተገቢነት አላቸው ወይስ የላቸውም ከሚለው ላይ መሆኑ እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የትኞቹ ተግባራት ለየትኞቹ የክፍል ደረጃ ይዋሉ የሚለውን ነው፡፡ ስለዚህ ከላይ የቀረቡትን የመናገር ክሂል መለማመጃዎች ከተማሪዎች ዕድሜ፣ የክፍል ደረጃ፣ አካባቢ ወዘተ ጋር በማጣጣም ተግባራቱን መጠቀም እንደሚቻል መምህራን በውል ሊገነዘቡት ይገባል፡፡

በተጨማሪም ነፃ ውይይት የንግግር ለዛን ለማዳበር መልካም አጋጣሚዎችን መፍጠር ይችላል፡፡ በተለያዩ ጊዜ በነፃ ውይይት ተማሪዎች እንዲሳተፉ በማድረግ በርካታ ርዕስ ላይ ለምሳሌ በፍላጎታቸው፣ ሐሳቦች፣ ታሪኮች እና ልምዶቻቸው የንግግር ችሎታቸውን ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡

እንዲሁም ቁሳቁሶችንም ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡ እዚህም ላይ ተማሪዎች የሚስማሙባቸውን እና የማይስማሙባቸውን ሐሳቦችን፣ ምርጫቸውን እና  ንጽጽር እንዲያደርጉ እድል ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ነፃ ውይይት በተጨማሪ ተማሪዎች ለምልልስ አስፈላጊ የሆነ ቋንቋ እንዲጠቀሙ ያበረታታል በሌላኛው ተናጋሪ ላይ በተወሰነ ጊዜ ምስል እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ በርግጥም ነፃ ውይይት ከሌሎች ተግባራት የበላይነትን ይይዛል፡፡ ይኸም ለተማሪዎች የርስ በርስ ግንኙነት

አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡ መምህራን ብዙን ጊዜ በቡድን ያልተዋቀሩ የንግግር ብቃትን የሚያሻሽሉ ተግባራት ያስጨንቃቸዋል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በተግባራቱ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ሊቸገሩ ይችላሉ በማለት Tericia Hedge (1996:277) ገልጸዋል፡፡

ከላይ የተገለፁት ተግባራት አንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህር የመናገርን ክሂል በክፍል ውስጥ ሊተገብር ሲያስብ ሊያከናውናቸው የሚገቡ በመሆናቸው እነዚህንም ተግባራት በመጠቀም መምህሩ ተማሪዎቹን በመሚገባ ማለማመድ ይጠበቅበታል፡፡

## 2.6. የመናገር ክሂል ሲተገበር የሚያጋጥሙ ችግሮች

በመምህሩም ሆነ በተማሪው የመማር ማስተማሩ ሂደት በሚከናወንበት ወቅት ተግባሩን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡ ከመምህሩ አኳያ የማስተማር ችሎት የብቃት ማነስ፣ የዝግጅት ማነስ፣ የክፍል አመራር ችሎታ ማጣት ወዘተ… ሊጠቀሱ ሲችሎ፣ በተማሪዎች በኩል ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል ደግሞ ዋና ዋናዎቹ መታቀብ፣ የሚናገሩት ነገር ማጣትና ዝቅተኛ ወይም ሁሉን የላማከለ ተሳትፎ አለማከናወን ናቸው በማለት Ur (1996: 121) ገልፀዋል፡፡ ከተጠቀሱት ችግሮች ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት የሚከሰቱ ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሀ. መታቀብ፡- የሚናገረው ሰው ከሚያዳምጥ፣ ከሚያነብ ወይም ከሚፅፍ ሰው የበለጠ የሌሎችን ትኩረት ይስባል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ እንሳሳታለን በሚል የፍርሃት ስሜት ስለሚያድርባቸው ከመናገር ይቆጠባሉ፡፡ በተጨማሪም ትችትን በመፍራትና ንግግራችን የሌሎች ስሜት መሳብ አይችልም በሚል እምነት ሀሳባቸውን በውስጣቸው አምቀው የመያዝ ባህርይ ይታይባቸዋል፡፡ በዚህ የተነሳ በክፍል ውስጥ ለንግግር በሚዘጋጁ ተግባራት በፈቃደኝነት አይሳተፉም፡፡

ለ. የሚናገሩት ነገር ማጣት፡- ተማሪዎች የመናገር ፍላጐት እያላቸው አንዳንድ ጊዜ ለንግግር ለተመረጠው ጉዳይ በቂ መረጃ ስለማይኖራቸው ለመናገር አይደፍሩም፡፡ ተማሪዎቹ ለንግግር በተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በቂ ዳራዊ ዕውቀት ከሌላቸው ለመናገር ግላዊ ፍላጐትና ተነሳችነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡ ይህ አይነቱ ሁኔታ በተደጋጋሚ ከተከሰተ ተማሪዎች ለንግግር ስር የሰደደ ጥላቻ ሊያዳብሩ ይችላል፡፡

ሐ. ዝቅተኛ ወይም ሁሉን ያላማከለ ተሳትፎ አብዛኛውን ጊዜ የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባራት

በአንድ ጊዜ የሚያሳትፉት  አንድ ተማሪ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ በርካታ ተማሪዎች በንግግር  ተግባር ላይ ማሳተፍ ለቋንቋ ትምህርት ከተመደበው ጊዜ ጋር ሊጣጣም የማይችል ተግባር ነው፡፡ ይህም ሁኔታ የተወሰኑ ተማሪዎች የክፍል ወስጥ የንግግር ተግባርን በመቆጣጠር የሌሎች ተሳትፎ ውስጥ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## 2.7 የመናገር ክሂል ሲተገበር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማስወገድ የሚጠቅሙ ተግባራት

Ur (1996: 121) ንግግርን በማስተማር ሂደት ለሚያጋጥሙ ችግሮች የሚከተሉትን  ተግባራት በመፍትሄነት የጠቆሙ ሲሆን ተግባራቱም እንደሚተለው ቀርበዋል፡፡

ሀ. የቡድን ስራ መጠቀም፡- የክፍል  ውስጥ የንግግር ተግባራትን ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲያካሄዱ ማድረግ በልምምዱ የሚናገሩ ተማሪዎች ቁጥር ይጨምራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በክፍሉ ተማሪዎች ፊት ቆመው ለመናገር የሚፈሩና የሚያፍሩ ጭምት ተማሪዎች በአራትና በአምስት ተማሪዎች አድማጭነት ንግግር እንዲለማመዱ እድል ይሰጣል፡፡ ስለዚህ የሁሉንም ተማሪዎች ተሳትፎ ለማጎልበት መምህራን ትኩረት ሊሰጡት ይገባል፡፡

ለ. ተግባሩ በቀላል ቋንቋ እንዲቀርብ ማድረግ፡- አንዳንድ ጊዜ ተማሪዎች ጥሩ ይናገራሉ ብለው የሚገምቷቸውን ሰዎች ንግግር አስመስሎ ለመናገር የሚመከሩበት ሁኔታ አለ ሁኔታው ተማሪዎች ሲገልፁት በሚፈልጉት ጉዳይ ላይ ሙሉ ትኩረታቸውን እንዳያሳርፉ እንቅፋት ይሆናል፡፡ በሚናገሩት ሀሳብና በቋንቋ አጠቃቀማቸው መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዳይኖርም ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በራሳቸው የቃላት አጠቃቀምና የአገላለፅ ችሎታ ተጠቅመው እንዲያቀርቡ ማድረግ የንግግርን ተግባር ከባድ አድርገው እንዳያስቡት ያደርጋል፤ በራስ የመተማመን ደረጃቸውንም ከፍ ያደርጋል፡፡

ሐ. ፍላጐትን ለማነሳሳት ሳቢና አነቃቂ የመወያያ (ርዕስ) ተግባር መምረጥ፡- ለተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባር የሚመረጥ ርዕስ ወይም የሚዘጋጅ መልመጃ ግልፅ፣ ሳቢ፣ ተማሪዎችን ለንግግር የሚያነሳሳና ሊያነጋግር የሚችል ሰፊ ሀሳብ የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡ ርዕሱ የተመረጠው ወይም መልመጃው የተዘጋጀው የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት አድረጎ ከሆነ የተማሪዎች ተሳትፎ ይጨምራል፡፡ ስለዚህ የመናገር ክሂልን የክፍል ውስጥ ክንውን ውጤታማ ለማድግ በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተራክቦ ላይ ተፅዕኖ

የሚያሳድሩ ችግሮችን ለመቀነስ ከላይ  በመፍትሔነት የቀረቡትን ነጥቦች ተግባራዊ ማድረግ አሌ የማይባል ጉዳይ መሆኑን  መምህራን ሊገነዘቡት ይገባል።

በአጠቃላይ የመናገር ክሂል ሲተገበር አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በጓደኞቻቸው ፊት ቆመው ለመናገር ስለሚፈሩ መምህሩ ይሆናል የሚለውን ዘዴ በመጠቀም ወይም በቡድን በማደራጀት ተግባሩን እንዲሳተፉ ማድረግ ይጠበቅበታል። በተጨማሪም የሚመረጠው ርዕስ በተማሪው የህይወት ገጠመኝ ዙሪያ ቢሆን ይመረጣል።

## 2.8 በመናገር ክሂል ትምህርት አቀራረብ የመምህሩ ሚና

የአብዛኛው መምህራን አላማ ቋንቋውን በማስተማር ረገድ ትክክለኛውን ዘዴ መተግበር ነው። ስለሆነም መምህራን ከዘመኑ የንግግር ክሂል ማስተማር ጋር ይበልጥ ዝምድና ሊኖራቸው ይገባል። የንግግር ክሂልን ስለማስተማር Nunan (1995:5) መምህራን የመናገር ክሂል ከፅሑፍ ክሂል ጋር ያለውን ልዩነት እያነፃፀሩ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ትኩረት ስጥተው ማመልከት እንዳለባቸው ገልፀዋል፡-

- ተስማሚ የሆነውን የንግግር ቋንቋ የማስተማር ቅርፅ ወይም ሞዴል የትኛው ነው?
- የንግግርና የፅሑፍ ቋንቋ ልዩነቶች በግልጽ  ማስቀመጣቸው
- የንግግር ክሂልን ትምህርቱ ካከናወነ በኋላ ከተማሪዎች ሞጋቤ ምላሽ ለማግኘት የተለያዩ መጠይቆችን በማዘጋጀት ማስሞላት?
- ተማሪዎች በንግግር ትምህርት ሂደት ውስጥ ስህተት አንድ የመማሪያ መንገድ መሆኑን ተረድተው በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ነፃ ሆነው እንዲናገሩ ማበረታታት፣
- በቡድን ወይም በተናጠል ስራ ውስጥ መምህሩ እየዞረ በመከታተል ማበረታታት፣
- የተማሪዎች አቀማመጥ ለንግግር ተግባራት አመቺ እንዲሆን ማድረግ፣
- ለንግግሩ ተግባር የተማሪዎችን ትኩረት መሳብ የሚችል መግቢያ/ ፍንጭ መስጠት በማለት ያስቀምጣሉ።

Byrne (1976:1-2) የአንድ ቋንቋ መምህር ተግባር በክፍል ውስጥ የተሻለ የመማር ማስተማር ሁኔታዎችን መፍጠር ነው። ከዚህ አጠቃላይ ተግባር በተጨማሪ አንድ መምህር በመናገር ክሂል አተገባበር የተለያዩ ደረጃዎች የሚከተሉት ሚናዎች እንዳሉት ይገልፃሉ።

## ሀ. በአቀራረብ ደረጃ

በአቀራረብ ደረጃ መምህሩ የተማሪዎቹን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ተግባራት መምረጥና የተመረጡትን ይዘቶች ግልፅነትና አይረሴነት ባለው መንገድ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ ደረጃ ብዙ ጊዜ ማጥፋት ተማሪዎች እርስ በርሳቸው  ቋንቋውን የሚለማመዱበትን ጊዜ ስለሚያሳጣ ተገቢነት የለውም፡፡

Byrne (1976:34)እንደሚያስረዳው በዚህ ደረጃ የንግግር ትምህርቱ በምንባብ መልክ ወይም በምልልስ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ለምሳሌ መምህሩ ውይይቱን በማስተማሪያነተ ለመጠቀም ከፈለገ በቅድሚያ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ወይም ሌሎች ሰዎች ሲወያዩ የሚያሳይ ይዘት ማቅረብ ወይም ከዕለቱ ምንባብ ርዕስ ጋር የተያያዙ አጫጭር ምንባቦች በማምጣት ሊያቀርብ ይችላል፡፡ መምህሩ በዚህ ደረጃ የሚያቀርበው አዲስ የመናገር ትምህርት ከሁለት መመዘኛ አንፃር ሊመለከት ይገባል፡፡ የመጀመሪያው በዚህ ደረጃ ብዙ ጊዜ ማጥፋት የማያስፈልግ በመሆኑ ጊዜ መቆጠቡን፣ ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎች ቀጣይ የሚቀርበውን የትምህርት ይዘት ክንዋኔዎች እንዲፈጽሙ የሚያስችላቸው ነውን? የሚለውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## ለ.በልምምድ ደረጃ

ይህ ደረጃ ተማሪዎች አብዛኛውን የመናገር ተግባር የሚያከናውኑበት ነው፡፡ የመምህሩ ተግባር ልምምዶችን በተቻለ መጠን ማዘጋጀትና ማቅረብ ነው፡፡ ልምምዶቹም ትርጉም ያላቸውና አይረሴነት የሚፈጥሩ ሊሆኑ ይገባል፡፡ መምህሩ ብዙ ከመናገር በመቆጠብ ተማሪዎች በልምምዱ እንዲሳተፉ እድል መስጠትና አፈፃፀማቸው አጥጋቢ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል፤

Byrne (1976:39-43) በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በቀረበላቸው አውድ ላይ ተመርኩዘው የማስመሰል እና የመደጋገም ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም ጊዜ ተሰባስቦ መስራት (የህብረት ንግግር)፣ ከፍተኛ ልምምድ፣ ቀጣይነት ያለው ቃላዊ ተግባር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህ ዓላማ የሚያገለግሉ ተግባራት ድምፅን ከፍ አድርጐ ማንበብ፣ የተለያዩ መረጃዎችን እንዲያከናውኑ ማድረግ፣ የንግግር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማድረገ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን ክሂል የመለማመድ ተግባራትን ሲገልፁ፡-

- ገምተው እንዲናገሩ የሚያስችሉ መልመጃዎች፡- ለተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት መሰረት የሆኑት ቀለል ያሉ የመረጃ ክፍተት በተለይም ጨዋታዎች ለዚህ ተግባር ማሳኪያ ሊውሉ ይችላሉ፡፡

- መላምታዊ ሁነቶች፡- እንዲህ አይነቱ ነገር ቢያጋጥማችሁ ምን ታደርጋላችሁ? በማለት በጉዳዩ ላይ እንዲነጋገሩ ማድረግ፤ ለምሳሌ፡- ሎተሪ ቢደርሳችሁ ገንዘቡን ምን ታደርጉበታላችሁ?

- ክፍት መልሶች፡- ለተማሪዎች የመነሻ ሀሳቦችን ሰጥቶ ሀሳቡን በተለያየ መንገድ እንዲያሟሉ ማድረግ ወዘተ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡

## ሐ. በአፍልቆት ደረጃ

በዚህ ደረጃ የመናገር እድል ለተማሪዎች በመስጠት ቋንቋውን በራሳቸው እንዲጠቀሙና ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ መምህሩ ማድረግ ይገባዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ ጊዜ የተማሪዎችን ልምምድ የሚቆጣጠርበትና እንደ ተማሪዎቹ ፍላጐት እንደሚጠይቁት ጥያቄ ሁኔታ የተለያዩ እርዳታዎችን የሚያደርግበት እና ምክር የሚለግስበት ወቅት ነው፡፡ አብዛኛውን መምህራን በጥሩ ሁኔታ ካቀረቡና ተማሪዋችን ካለማመዱ በኋላ ሥራቸውን እንደጨረሱ አድርገው ይቆጥራሉ፡፡ ነገር ግን በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ነፃ ሆነው ሀሳባቸውን እንዲያንሸራሽሩ የሚያደርጉበትና ተማሪዎች ምን ያህል መሻሻል እንዳሳዩ የሚከታተሉበት መሆኑን መረዳት አለባቸው፤ በተጨማሪም ተማሪዎች የራሳቸውን የቃላት እና የስዋስው አውቀት በመጠቀም ሀሳብ አፍልቀው የሚገልጹበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም ውይቶችና ክርክሮችን  በማደራጀት በስዕሎች፣ በፎተግራፎች፣ በካርታዎች ወዘተ ላይ ተንተርሰው ሃሳባቸውን እንዲያነሸራሽሩ ማበረታታ ይኖርባቸዋል በማለት Byrne (1987:74-98) ገልፀዋል፡፡

በአፍልቆት ደረጃ ዋናው ትኩረት ተማሪዎች በቀላሉ እና በነፃነት የሚግባቡበትን አውድ መፍጠር እንዲሁም በጋራ የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸተ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ የክፍሉ ተማሪዎች በተወሰነ ቡድን መከፋፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ሲባል ግን የጥንድ ሥራ አላስፈላጊ ነው ማለት አይደለም፡፡ በተለይ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥራቸው የሚበዛ ከሆነ የቡድን ስራ ተመራጭነት ያለው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ደረጃ የቡድን ሥራ መጠቀም ተማሪዎች ሀሳብ ለሃሳበ ለመለዋወጥ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡ በአጠቃላይ አላማችን የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ማዳበር እስከሆነ ድረስ ሁል ጊዜ እነዚህን ሦስት ደረጃዎች መጠቀም  ይገባናል በማለት Byrne (1986:81-91) ይገልፃሉ፡፡

## 2.9 የቀደምት ስራዎች ቅኝት

የተማሪዎችን መናገር ክሂል ለማሳደግ ለክፍል ደረጃው ተገቢነት ያላቸው የመናገር ክሂል ተግባራትን በማቅረብ ተማሪዎች የቋንቋውን ስዋሰዋዊ ስርዓት በመጠቀም አሳባቸውን በንግግር እንዲገልጹ በክፍል ውስጥ መለማመድ ይኖርባቸዋል፡፡ የክፍል ውስጥ ልምምዱን ውጤታማ ለማድረግ ተማሪዎችን የመናገር ችሎታ ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ መምህራን የመለማመጃ ተግባራቱ የሚቀርቡበትን መንገድ ጠንቅቀው ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስለዚህ መምህራን በክፍል ውስጥ በሚደረገው ተግባቦታዊ ሂደት ብዙ ከመናገር በመቆጠብ ቀስቃሽና አጋዥ መሆን ይኖርባቸዋል እንጂ አዘውትረው ከተማሪዎች ጋራ መስተጋብር ማድረግ አይጠበቅባቸውም፡፡ ተማሪዎቹም የመማር ግዴታቸውን ለመወጣት በጥንድ እና በቡድን በመሆን የእርስ በእርስ መስተጋብር መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡

የዚህ የቀደምት ጥናት ዓላማ ከዚህ ትናት ጋራ ግንኙነት ያላቸውን የቀደምት ጥናት ስራዎች መቃኘት ነው፡፡ ከዚህ ጥናት ጋራ ግንኙነት ያላቸው 1ኛ. እጅጉ ይማም " በደብረ ብርሃን ከተማ በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂልአቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ በ2003 ዓ.ም ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ ያደረገውን ጥናት፣ 2ኛ አያልሰው ይታየው " ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ ትምህርት መጻህፍት ውስጥ በሚገኙ የልብ ወለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተና ግምገማ" በሚል ርዕስ በ2003 ዓ.ም ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ የተደረገ ጥናት ነው፡፡ አጥኚው( እጅጉ ይማም) የጥናቱ አቀራቢም በግኝቱ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ለማሳደግ በቡድን ውይይት፣ የግል፣ የጥንድ ወዘተ ማቅረቢያ ዘዴዎችን መምህራን መተግበር አለመቻላቸውን፣ የተማሪዎች ተራክቦ እኩል እንዳልሆነና የተማሪዎች የእርስ በእርስ ግንኙነት አቀራረብ ጉልህ ድርሻ የሌለው እንደሆነ፣ የመምህሩ የመናገር ክሂል አቀራረብ ሁሉም ተማሪዎችን አሳታፊ አለመሆኑ፣ የተማሪዎች የንባብ ባህል ባለመዳበሩ ምክንያት ተማሪዎች ሀሳብ የማፍለቅ ችግር እንደሚታይባቸው የጥናቱ መረጃ እንደሚጠቁም ገልጿል፡፡ ሁለተኛው የጥናት አቅራቢ በመጽሃፍት ውስጥ የሚገኙ የንግግር ክሂል መልመጃዎች ከተሰጠው ክፍለ ጊዜ ጋር ተመጣጣኝ ያለመሆኑ፣ ክሂሉን ከሌሎች ክሂሎች ጋራ የማያለማምድ መሆኑ፣ ንግግር ለማስተማር የተለያዩ ዘዴዎችን ማለትም ስዕሎችን፣ ቃለ መጠይቆችን፣ ክርክሮችን፣ ጭውውቶችን ወዘተ አለመጠቀም የመናገር ክሂል መልመጃዎችን አዘገጃጀት መርሆዎችን አለመከተል እንከን ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል በማለት አስቀምጠዋል፡፡

ስለሆነም ይህ ጥናት ከቀዳሚዎቹ ትናቶች ከቦታ በተጨማሪም በክፍል ደረጃ ይለያል፡፡የተጠኚዎች መለያየት ለጥናቱ ውጤት መለያየት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም የላይኞቹ ጥናቶች የትኩረት አቅጣጫ አፈ ፊት ተማሪዎችን ግምት ያስገባ ሲሆን ይህኛው ጥናት ግን ሁሉንም አፈ ፊትም ኢ አፈ ፊትንም ተማሪዎችን መነሻያደርጋል፡፡ እንዲሁም በመናገር ክሂል ልምምድ ወቅት ለመናገር ማይደፍሩ ተማሪዎችን መምህራን እንዴት ያስተናግዷቸዋል የሚለውንም በመፈተሽ አከናውኗል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናኑ ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ክንዋኔ

በምዕራፍ አንድ ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ የዚህ ጥናት ትኩረት የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂልን አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ የተከተለው አይነታዊ እና መጠናዊ ምርምር ዘዴን ሲሆን አቀራረቡም ገላጸዊ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጥናት ይዞ ከተነሳው ግብ አኳያ አሰራሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 3.2 የተጠኚዎች ናሙና አመራረጥ

ሰንጠረዥ 1. በጥናቱ የተካተቱ ትምህርት ቤቶች፣ የተማሪዎች እና የመምህራን ብዛት የናሙና መጠን እና የምልከታ ጊዜ መግለጫ

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት | | የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን | | የምልከታው ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በትምህርት ቤት | ናሙና | በትምህርት ቤት | የመጠይቅ ናሙና | |
| 1 | ለም 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 835 | 30 | 3 | 1 | 2 |
| 2 | በሻሌ 2ኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት | 803 | 30 | 3 | 1 | 2 |
| 3 | ዶክተር አዲስ አለማየሁ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 350 | 30 | 2 | 1 | 2 |
| 4 | ቦሌ ኅብረተሰብ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 405 | 30 | 2 | 1 | 2 |

### 3.2.1. የትምህርት ቤቶች የናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደዉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ነዉ፡፡ በክፍለ ከተማዉ ሰር ስድስት የመንግስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቸ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ስድስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ አራቱ በዕጣ ናሙና ተመርጠዋል፡፡

የተመረጡት ትምህርት ቤቶቹም ለም 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በሻሌ 2ኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ ዶክተር አዲስ አለማየሁ 2ኛ ደርጃ ትምህርት ቤት እና ቦሌ ህብረተሰብ 2ኛ ደረጃ ትምህረት ቤት ናቸዉ፡፡

## 3.2.2 የመማሪያ ክፍል ናሙና አመራረጥ

የክፍሎች አመራረጥን በተመለከተ ተተኳሪ መምህራን ከሚገቡባቸዉ ክፍሎች ዉስጥ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት አንድ አንድ ምድብ በድምሩ አራት ምድቦች በዕጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

## 3.2.3 የመምህራንና ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

### 3.2.3.1 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በነሲብ ናሙና በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቁጥራቸው አስር ሲሆን አራቱ የጥናቱ ተተኳሪ ሆነው ተመርጠዋል፡፡ በሂደቱም አራቱም መምህራን መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርገዋል፡፡ አመራረጡም በኢላማዊ ናሙና አማካኝነት ሲሆን ለጥናቱ ጠቃሚ የሆነ መረጃ ያስገኛሉ ተብለው የሚታሰቡ መምህራን በናሙናነት ተጠኚ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ ከየትምህርት ቤቱ አንድ አንድ ተጠኚ መምህራን ብቻ በጥናቱ እንዲታቀፉ ተደርገዋል፡፡

*ሰንጠረዥ2. የተተኳሪ መምህራን ዳራዊ መግለጫ*

| | የትምህርት ቤት ስም | ጾታ | የትምህርት ደረጃ | የትምህርት መስክ | | የማስተማር ልምድ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | አብይ | ንዑስ | |
| 1. | ለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ሴ | ቢኤ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 19 |
| 2. | በሻሌሁለተኛና መሰናዶ ት/ቤት | ወ | ቢኤ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 4 |
| 3. | ዶክተር ሀዲስ ዓለማየሁ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤ | ሴ | ቢኤ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 4 |
| 4. | ቦሌ ህብረተሰብ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | ወ | ቢኤ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | 3 |

ከሰኝጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው መረጃ እንዲሰጡ የተመረጡት መምህራን ከከፆታ እንጻር ሁለት ሴት እና ሁለት ወንድ ናቸው፡፡ ከትምርት ደረጃ አንጻርም ሁሉም የመጀመሪያ ዲግሪ

ያላቸውና በአማርኛ ትምህርት የሰለጠኑ ሲሆኑ ከ3 እስከ 19 ዓመታት ያህል ያገለገሉ ናቸው፡፡ ስለሆነም ተፈላጊው መረጃ ይገኛል ተብሎ ይገመታል፡፡

#### 3.2.3.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ከላይ ከተጠቀሱት አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተመረጡ አራት ክፍሎች ውስጥ በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ከ 50-65 ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ የመነሻ ቁጥር እጣ ከተለየ በኂላ አንድ አልፎ አንድ በመውሰድ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ሰላሳ በአጠቃላይ አንድ መቶ ሃያ ተማሪዎች ተመርጠው የጽሁፍመጠይቁን እንዲሞሉ ተደርገዋል፡፡ ተማሪዎቹ ጽሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታውን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ከተማሪዎቹ የሚሰበሰበው መረጃ በተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘውን መረጃ ያጠናክራል በሚል እሳቤ የተካሄደ ነው፡፡

## 3.3 መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የዚህ ጥናት ትኩረት የ10ኛ ክፍል መምህራን የክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል አተገባበርን መፈተሽ ነዉ፡፡ የጥናቱ አካባቢ፣ የትምህርት ቤቶቹ የመምህራን እና የተማሪዎቹ ናሙና ከተመረጡ በኂላ መረጃ የመሰብሰቡ ስራ ተከናውኗል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች አስተማማኝ ይሆኑ ዘንድም በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መጠቀም አስፈላጊ ሆኖተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ መረጃዎች ለማሰባሰብ ጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

### 3.3.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ

በተጠኚ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚስተዋለው ክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል የመማር ማስተማር ክንውን ለመታዘብ በቼክ ሊስት የተደገፈ ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያነት በጥቅም ላይ የዋለ ዋንኛው መሳሪያ ነው፡፡ ምልከታው በአራቱ ናሙና ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩትን መምህራን አካቷል ፡፡ የምልከታው መረጃ የተሰበሰበው ከየካቲት 13 እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2010 ዓ.ም ድረስ ነው፡፡ ምልከታው የተካሄደው በተጠኚ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ አራት የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ በመታዘብ ነው፡፡ ምልከታው በእያንዳንዱ ተጠኚ መምህራን ላይ ሁለት ሁለት ጊዜያት የተካሄደ ነው፡፡

## 3.3.2 የጽሑፍ መጠይቅ

የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር በሚመለከት ተጨማሪ መረጃዎችን ለማሰባሰብ እንዲቻል ለአራት መምህራን እና ለተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ቀርቧል፡፡ የጽሁፍ መጠይቅ መሰረታዊ ዓላማው በተከታታይ የክፍል ውሰጥ ምልከታዎች የተገኘውን መረጃ ለማገናዘብ እና ትክክለኝነቱን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህም መምህራን የክፍለ ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበራቸውን በተመለከተ ምን እንደሚመስል የሚጠይቁ ክፍሎች ያካተተ ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ለተመሳሳይ ዓላማ ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው፡፡ ለመምህራን የተዘጋጀው የጽሁፍ መጠይቅ ለተተኳሪዎቹ መምህራን ተበትኖ በቂ ጊዜ አግኝተው እንዲሞሉት ተደርጓል፡፡ለተማሪዎች የተዘጋጀው የጽሁፍ መጠይቅም አጥኚው በየትምህርት ቤቶቹ በመገኘት የተመረጡትን ተማሪዎች ለብቻቸው በመለየት እና ስለመጠይቁ አጠቃላይ ዓላማ እና አሞላል ማብራሪያ ከተሰጣቸው በኋላ በየግላቸው እንዲሞሉት ተደርጓል፡፡ የተበተኑት መጠይቆችም በሙሉ ተሞልተው ተመልሰዋል፡፡ በጽሁፍ መጠይቆቹ ውስጥ የሚገኙት ዝርዝር ጥያቄዎች በትንተናው ጊዜ በሰንጠረዥ መልክ ቀርበው ይገኛሉ፤፤

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት ከመምህራንና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ፣ ከምልከታ፣ ከተሰበሰቡት መረጃዎችና ውጤቶች በመነሳት በምዕራፍ አንድ ስር ለቀረቡት የዓላማ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ትንተና ተደርጓል፡፡ ትንተናው መረጃዎቹ በሚያነሱት ጉዳይ ተከፋፍለው በሰንጠረዥ ውስጥ በቁጥር እና በመቶኛ ቀርበዋል፡፡ ሌላው በመረጃ ትንተና የታየው ውጤት የተብራራበት ነው፡፡ ውጤቱንም ከሚቀርቡት ይዘቶችና ክንውኖች በመማር ማስተማሩ ሂደት ከሚሰራበት ስነዘዴ እና አተገባበር በተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ስር ከሰፈሩት ንድፈ ሃሳቦች ጋር መጣጣማቸውን ለመፈተሽ እና መምህራን ያላቸውን ግንዛቤ እንዲሁም ከስነ ዘዴው ውቴታማነት አንጻር ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃዎች ትንተና

የዚህ ምዕራፍ ዓላማ በ10ኛ ክፍል ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል አተገባበርን ለመፈተሽ፣ የትምህርት አቀራረባቸውን በተመለከተ ውጤታማ መሆናቸውን በመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በምዕራፍ ሦስት እንደተገለፀው የዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምልከታ እና የጽሑፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ በነዚህ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በዝርዝር እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 4.1. ከምልከታ እና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.1.1 መምህራን የመናገር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ በአቀራረብ ደረጃ ምን ያህል እንደሚተገብሯቸው መፈተሽ

በንግግር ትምህርት አቀራራብ ተማሪዎች ወደዋናው ተግባር ከመግባታቸው በፊት የማነቃቃት ስራ ታስቦ የሚከናወን ከሆነ የተፈለገውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ዓይነተኛ መሳሪያ መሆኑን የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ የተማሪዎችን ፍላጐት በማነሳሳት ተግባቦታዊ ችሎታቸውን የሚያሳድግ፣ ገጠመኞቻቸው ከእለት እለት ህይወታቸው ጋር አብረው የሚሄዱ ተግባራትን በመምረጥ እነሱን መሰረት በማድረግ ቀጣዩን ሥራቸው የሚያከናውኑበትን ሁኔታ በግልፅ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች የንግግር ተግባራቱን እንዴት ማቅረብ እንዳለባቸው ሞዴል በመስጠትና በነፃነት እንዲናገሩ ማድረግ የመምህሩ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ከርዕሱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የተለያዩ (ለምሳሌ የተለያዩ ስዕሎችን) በመቀጠም የዕለቱን ትምህርት ዓላማና ምን ምን ተግባራትን እንደሚሰሩ ማሳወቅ ስለሚያከናውኑት ተግባር ግልፅ መመሪያ መስጠት መመሪያውን መረዳታቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ለሚያከናውኑት ተግባር ተገቢነት ያለው አቀማመጥ መምረጥ ይጠበቅበታል፡፡

ከዚህ መሰረተ ሀሳብ በመነሳት የተደራጀ ምልከታ ቅፅ በቅድሚያ በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ ምልከታው ወቅት ተተኳሪ ነጥቦች መከናወን ወይም አለመከናወናቸውን መከታተል የተቻለ ሲሆን የእያንዳንዱ የመናገር ክሂል አቀራረብ ደረጃ ክንውን ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠየቅና ከመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ እየተመሳከረ የመረጃው ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 3. መምህሩ የዕለቱን የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት ተግባራትን አቀራረብ አስመልክቶ በምልከታ የተገኘ ውጤት የሚያሳይ መግለጫ፤

| ተራ ቁ | የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይ | |
| | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| 1 | የተወሰነ ግልፅ ዓላማ ለተማሪዎች ቀርቦ ነበር? | 4 | 50% | 4 | 50% |
| 2 | የትምህርቱ አቀራረብ የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ መሰረት ያደረገ ነበር? | 8 | 100% | ___ | ___ |
| 3 | በትምህርቱ አቀራረብ የፈጠራ ስራ እና የማስተማሪያ መሳሪያ ቀርቦ ነበር? | ___ | ___ | 8 | 100% |
| 4 | የትምህርቱ ይዘት የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ ነበር? | 6 | 75% | 2 | 25% |
| 5 | የመናገር ትምህርቱን በበቂ ሁኔታ ይለማመዱ ዘንድ ተማሪዎችን የማነቃቃት ተግባር ተከናውኗል? | ___ | ------ | 8 | 100% |
| 6 | የቀረቡት መመሪያዎች ለተማሪዎቹ ግልፅ ነበሩ? | 6 | 75% | 2 | 25% |

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ በተካሄዱት የክፍል ውስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት ተከታታይ ምልከታዎች ውስጥ የተማሪዎችን ችሎታ ለማዳበር የተለያዩ የመናገር ተግባራትን ወደ ክፍል በማምጣት የዕለቱን ትምህርት ከማቅረባቸው በፊት አላማውን በመዘርዘር ያቀረቡት በቁጥር 4 (50%) ሲሆኑ፤ አላማውን ሳይገልፁ ወደ ዕለቱ ትምህርት የገቡ 4 (50%) ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው የዕለቱን ትምህርት ከመቅረቡ በፊት ማንኛውም መምህር ስለሚያስተምረው ጉዳዩ አላማውን በዝርዝር ማሳወቅ ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪም ከተማሪዎቹ ዕድሜና ፍላጐት፣ ስነ ልቦና፣ ከትምህርት ደረጃ፣ ከተማሪዎቹ ማንነትና ይዘውት ከመጡት ባህል፣ ወግና ልማድ ጋር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ ለማዳበር ተማሪዎች የሚያነሳሱና የሚያሳትፉ እንዲሁም ለውይይትና ክርክር የሚጋብዙ ርዕሶችን በቂ ጊዜ ወስዶ መምረጥ ጠቀሜታው የጐላ ነው፡፡ ሆኖም ከዚህ ምልከታ ማየት የቻልነው የተወሰኑት አላማውን ሲገልፁ፣ የተወሰኑት መግለፅ አልቻሉም፡፡ በመሆኑም ግልፅ አላማን በማስገኘት ረገድ ያተኮረ የንግግር ተግባር ልምምድ በማቅረብ ረገድ የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን ያሳያል፡፡

እንዲሁም የዕለቱ ትምህርት ርዕስ የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ መሰረት የማድረጉ ሁኔታ 8(100%) የትምህርቱን መርሃ ትምህርት መከተላቸውን በአግባቡ ያሳየናል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዙ የክፍል ውስጥ መናገር ክሂል ትምህርት ሁሉም ተተኳሪ መምህራን ዋናውን ትምህርት (የዕለቱን) ሲያቀርቡ በፈጠራ ስራዎች ላይ የተመሰረተ አልነበረም፡፡ ይህ ደግሞ የተማሪዎች የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴዎች የህይወት ገጠመኝን ያላገናዘበ በመሆኑ ትምህርቱን ጉዶሎ ያደርገዋል፡፡

ይህንን ሀሣብ (Brown & Yule 1983) የመናገር ተግባራትን ስናስተምር ተማሪዎች ማህበራዊ ግንኙነታቸውን እንዴት አድርገው እንደሚመሰርቱ እና በክፍል ውስጥ በምን መልኩ እንደሚተገብሩ ማስተማርና ከክፍል ውጪም ባለው ህይወታቸው ጠቃሚ መሆኑን ማስተማር፣ ይህም ሲሆን ከጓደኛቸው ጋር ከቤተሰብ አባላት ጋር በውይይት መልክ እንዲተገብሩ ይረዳቸዋል በማለት ገልፀዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎች የመናገር ክሂልን ሲማሩ ከህይወት ገጠመኞቻቸው ጋር የተያያዘ ትምህርት መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ተግባራት በምን ዓይነት ደረጃ እንደሚቀርቡ በማያሻማ ሁኔታ አውቆ የተማሪዎቹን ፍላጎትና ስሜት እንዲሁም የትምህርት ደረጃ ሊመጥኑ የሚችሉ የተለያዩ ሞዴሎችን በማምጣጥ ወደ ዋናው ሥራ የማስገባት ሁኔታ ከማንኛውም የቋንቋ መምህር የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡ በዚህም መሠረት 6 (75%) ያቀረቡት ርዕሰ ጉዳይ የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ የሚመጥን ሲሆን 2(25%) የተማሪዎችን የትምህርትና የዕድሜ ደረጃ ያገናዘበ ነው ለማለት አያስችልም፡፡ ለተማሪዎቹ ልምምድ የተሰጣቸው ርዕስ *"ለሴት ልጆች የትዳር ጓደኛ ለመምረጥ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም"* በሚል ሲሆን፤ ይህ ርዕስ ተማሪዎቹ በሚያውቁበትና ባልሞከሩበት ተግባር በመሆኑ ይህ ሀሣብ ከተማሪዎቹ የትምህርት ደረጃ በላይ በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ግን አብላጫው ርዕስ የቀረበው መጣኝ በሆነ መልኩ በመሆኑ ትምህርቱ በዚህ ረገድ መልካም እንደነበር ያሳየናል፡፡

በሌላ በኩል በክፍል ምልከታው የተከናወነውን ተግባር ስንመለከት ተጠኚ መምህራን ተማሪዎች ወደ ዋናው ተግባር እንዲገቡ ለማነቃቃት ባለመሞከራቸው የተሠጣቸውን ሥራ ለመጀመር ብዙ ደቂቃዎችን ፈጅቶባቸዋል፡፡ ተግባሩ ይቀርብ የነበረው በክርክር መልክ በመሆኑ ወደ ክርክር ከመግባታቸው በፊት ማነቃቂያ ሳይሆን የክርክሩን ሂደት ነበር መምህርቷ ሲገልፁ የነበረው፡፡ በመሆኑም የክርክሩ ሂደት ሳቢና ማራኪ ባልሆነ መንገድ የቀረበ እና ተማሪዎች የርስ በርስ ያለመደማመጥ እና ሥርዓቱን ያልጠበቀ ክንውን እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ይህ

የሚያሣየን መምህራን የማነቃቃት ሥራ ባለመስራታቸው፣ ውይይትና ክርክር መድረክ ላይ እንዴት እንደሚያቀርቡ እና ምን ምን ነገሮች እንደሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ተግባራት ባለማቅረባቸው ተማሪዎቹ ቅደምተከተላቸውን ጠብቀው እንዳይናገሩ ሆነዋል፡፡

የሚቀርቡት መመሪያዎች ግልጽነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህም ሲባል ለተማሪዎቹ በትምህርት የሚቀርበው መመሪያ በሚገባ ተብላልተው ወደ ትምህርቱ ከመግባታቸው በፊት መምህራን ለተማሪዎቹ ግልጽና ሊተገብሩት በሚችሉበት ሁኔታ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም 6 (75%) በተማሪዎች ግልፅ በሆነ መልኩ የሚሰብ ሲሆን 2 (25%) የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃና እድሜ ያላገናዘበ በሆነ መልኩ ተሰርቷል፡፡

ከፍ ሲል ባየነው ሠንጠረዥ እንደተጠቀሰው በክፍል ውስጥ በተደረጉ ተከታታይ ምልከታዎች የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት አብዛኛዎቹ መምህራን የዕለቱን የመናገር ትምህርት አቀራረብ የፈጠራ ሥራዎችን እንዲሁም ወደ ዕለቱ ትምህርት ከመግባታቸው በፊት የማነቃቂያ ተግባር ያላከናወኑ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ነገር ግን ምልከታ በተደረገባቸው ጊዜያት ምንም ዓይነት የፈጠራ ሥራዎችንና የማነቃቂያ ተግባር አለማከናወናቸው ነው፡፡

*ሠንጠረዥ 4 የክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አቀራረብ በተመለከተ ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ መግለጫ*

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የመላሽ ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ 4 | | አብዛኛውን ጊዜ 3 | | አንዳንድ ጊዜ 2 | | ጨርሶ 1 | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | የመናገር ትምህርት ከማቅረቤ በፊት አላማዉን በግልፅ አብራራለሁ? | 3 | 75% | 1 | 25% | - | - | - | - |
| 2 | ወደ ዋናዉ የመናገር ተግባር ከመግባቴ በፊት የማነቃቂያ ስራ አከናዉናለሁ? | 1 | 25% | 2 | 50% | 1 | 25% | - | - |
| 3 | ከመናገር ትምሁርት በፊት ስለመናገር አቀራረብ ተማሪዎች እንዲያውቁ አደርጋለሁ? | 2 | 50% | 2 | 50% | - | - | - | - |
| 4 | ለመናገር ትምህርት የሚሆን ግብአቶችን በግል ተዘጋጅቼ በመምጣት አስተምራለሁ(አጋዥ መርጃ መሳሪያዎችን)? | 1 | 25% | 1 | 25% | 1 | 25% | 1 | 25% |
| 5 | ተማሪዎቹ በቀረበላቸው ሞዴል የመናገር ተግባር መሰረት የማስመሰልና የመደጋገም ስራዎችን እንዲያከናውኑ አደርጋለሁ? | - | - | - | - | 4 | 100% | - | - |

በሰንጠረዡ እንደተጠቀሰው ተተኳሪዎቹ መምህራን የመናገር ትምህርቱን ከመተግበራቸው በፊት አላማውን በግልጽ የሚያቀርቡ 3(75%)ቱ መምህራን ሁልግዜ እናቀርባለን ሲሉ አንድ (25%) መምህረርት ግን አብዛኛውን ጊዜ በማለት ገልፃለች ፡፡ እንደሚታወቀው አንድ መምህር የመማር ማስተማሩን ክንውን ለመተግበር ዓላማ ሊኖረው ይገባል፡፡ እንደ በድሉ ዋቅጅራ (2007፡87) የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ የማስተምር ዋና አላማዉ ተማሪዎች ሀሳባቸውን ያለምንም ችግር እንዲገልፁ በራስ የመተማመን፤ ሀሳብን በምክንያትና ዉጤት አቀናጅቶ ማቅረብ፤ የቋንቋን ስርዓት ጠብቀዉ እንዲናገሩ ያስችላቸዋል በማለት ገልፀዋል፡፡ ስለሆነም ከምልከታዉ መረጃ እንደተረዳነዉ ሶስቱ መምህራን ዓላማዉን መግለፃቸዉ ይጠቁመናል፡፡

በሌላ በኩል መምህራን ወደ ዋናዉ የክፍል ዉስጥ የመናገር ተግባር ከመግባታቸዉ በፊት የማነቃቃት ሥራ ማከናወናቸዉና አለማከናወናቸዉ ተጠይቀዉ ሲመልሱ አንድ መምህር "ሁል ጊዜ" አከናዉናለሁ ስትል 50%ቱ "አብዛኛዉን ጊዜ" እንደሚተገብሩ ገልፀዋል ፡፡ ነገር ግን የምልከታዉ መረጃ ጋር ሲነፃፀር ሁሉም መምህራኖች የማነቃቂያ ተግባር እንዳላከናወኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

እንደ Ur (1996፡50) አገላለፅ ተማሪዎች በራሳቸው ጥሩና መጥፎ ገጠመኝ ዙሪያ፤ በአካባቢያቸዉ ያላቸዉን ባህል፤ ልምድና እዉቀት መነሻ በማድረግ የተለያዩ ርዕስ ጉዳዩችን መርጠዉ የሀሳብ ልዉዉጥ ቢያደርጉ መልካም ዉጤት ሊገኝ ይችላል በማለት ገልፀዋል፡፡ መጠይቅ ከሞሉት መምህራን 50%ቱ "ሁል ጊዜ" ለክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል አቀራረብን አሳዉቃለሁ ሲሉ 50%ቱ ደግሞ "አብዛኛዉን ጊዜ" አንደሚተገብሩት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ለመናገር ክሂል ትምህርት የሚሆኑ ግብአቶች ከመጽሐፉ ጥያቄ ዉጪ አቀርባለሁ ያሉ ተተኳሪ መምህራን አንድ መምህር "ሁል ጊዜ"፣ አንድ መምህር "አብዛኝዉን ጊዜ"፣ አንድ መምህር አንዳንድ ጊዜ እና አንድ መምህር "ጨርሶ" በማለት መልሰዋል፡፡ ይህ የሚያሳየን የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ ለማዳበር በቂ ጊዜ ወሰዶ የሚያነቃቁ፤ የሚያሳትፉና ለዉይይት የሚጋብዙ ርዕስ ጉዳዩችን በመምረጥ ረገድ መምህራኑ ያላቸዉ ተነሳሽነት ከሁለቱ መምህራን በስተቀር ሌሎቹ ደካማ መሆኑን ነዉ፡፡

አብዛኛዎቹ ሙሁራን እንደሚገልፁት፤ በክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት ተማሪዎችን በማነቃቃት የተለያዩ ሞዴል ተግባራትን በመስጠት አጋዥ መርጃ መሳሪያዎችን ተጠቅሞ የማስመሰልና የመደጋገም ተግባራትን እንዲያከናዉኑ ማድረግ ጠቀሜታዉ የጎላ ነዉ፡፡ በሰንጠረዡ ላይ እንደሚታየዉ በክፍል ዉስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ ሁሉም መምህር ተግባሩን 100%ቱ "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚያከናዉኑ ገልፀዋል፡፡ ከምልከታዉ ጋርም ይህ ተግባር ተመሳሳይ መልስ ታይቶበታል፡፡ ከዚህ እንደምንረዳው በመናገር ክሂል አቀራረብ ወቅት መምህራን ከመጽሐፉ ከቀረቡት የመለማመጃ ጥያቄዎች ዉጪ የተለያዩ የመርጃ መሳሪያዎች በማቅረብ የመማር ማስተማርን ተግባር እንደማያከናዉኑ ነዉ፡፡

ሠንጠረዥ5. የመናገር ክሂል ተግባራት አቀራረብን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ መግለጫ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | መልሶች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን ያቅተኛል | | አልስማማም | | በፍፅም አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ % | በቁጥር | በመቶኛ % | በቁጥር | በመቶኛ % | በቁጥር | በመቶኛ % | በቁጥር | በመቶኛ % |
| 1 | የመናገር ትምህርት ክሂልን ተግባር ከማከናወናቸው በፊት አለማው ይገለፅላችኂል | 42 | 35 | 53 | 44.1 | 12 | 10 | 7 | 5.9 | 6 | 5 |
| 2 | የመናገር ክሂል ተግባር በክፍል ውስጥ ከመቅረቡ በፊት በተለያዩ መንገዶች ያነቃቃሉ | 31 | 25.8 | 41 | 34.2 | 22 | 18.3 | 17 | 14.2 | 9 | 7.5 |
| 3 | የመናገር ክሂል ተግባር ከመጀመራቸው በፊት አጭርና ግልፅ መመሪያ ይሰጡ ነበር | 32 | 26.6 | 37 | 30.9 | 21 | 17.5 | 19 | 15.8 | 11 | 9.2 |
| 4 | ዋናውን የመናገር ተግባር ተማሪዎች ከማከናወናቸው በፊተ ሞዴል (ምሳሌ የሚሆኑ) ተግባሮች ይቀርቡ ነበር | 23 | 19.2 | 39 | 32.5 | 22 | 18.3 | 14 | 11.6 | 22 | 18.3 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚታየው የመናገር ክሂል ትምህርት ከመከናወኑ በፊት ዓለማውን ተገልፆላቸው እንደነበር ተጠይቀው 97(79.1%) ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ በማለት ሲመልሱ፣ 12(10%) ተማሪዎች ለመወሰን ያቅተኛል፣13(10.9%) አልስማም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ በመሆነም ከተማሪዎች መልስ መረዳት እንደሚቻለው የዕለቱን ትምህርት ከመቅረቡ በፊት የትምህርቱ ዓላማ እንደሚገለፅላቸው በአወንታዊ መልስ መስጠታቸውን መረጃው ያሳየናል፡፡ ሆኖም ግን በተደረገው ተከታታይ ምልከታ መረጃ መሰረት ሁለቱ መምህራን ዓለማውን ያለመግለፃቸውን ነው የሚያሳየው፡፡

እንዲሁም ተማሪዎች ከሞሉት መጠይቅ ውስጥ መረዳት እንዳተቻለው የመናገር ክሂል ተግባራትን ከመቅረቡ በፊት በተለያዩ መንገዶች የማነቃቃቱ ሁኔታ ይተገበራል ወይ? ተብለው ሲጠየቁ 25.8% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 34.2% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 18.3% ተማሪዎች ለመወሰን ያቅተኛል፣ 14.2% ተማሪዎች አልስማማም፣ 7.5% ተማሪዎች ደግሞ በፍፁም አልስማማም በማለት ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ ከተማሪዎቹ መልስ መረዳት የሚቻለው የዕለቱ ትምህርት ከመቅረቡ በፊት መምህራን ተከታታይነት ባለው መንገድ የተማሪዎች የቅድመ ዕውቀት ከዕለቱ ትምህርት ጋር ለማዛመድ፣ የዕለቱ ትምህርት በምን ዙሪያ እንደሚያጠነጥን ፍንጭ ለመስጠት፣ የተማሪዎችን ትኩረት ወደ ዕለቱ ትምህርት ለመሳብ የሚያደርጉት ጥረት አወንታዊ መሆኑን ነው መረጃው የሚያሳየን፡፡

ሌላው የመምህራን የቅድመ መናገር ክሂል ተግባር ክንውን በሚመለከት ለተማሪዎች የቀረበው ጥያቄ የመምህራን የመመሪያ አስጣጥ የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህም ጥያቄ 26.6% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 30.9% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 17.5% ተማሪዎች ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 15.8% ተማሪዎች አልስማማም፣ 9.2% ተማሪዎች ደግሞ በፍፁም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ Ur (1996.18) የመምህራን ወደ ዕለቱ ትምህርት ከመግባታቸው በፊት መመሪያ የመስጠት ጠቀሜታ በሚመለከት “ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስለሚያከናውኑት ተግባር ግልፅና እጥር ምጥን ያለ መመሪያ መስጠት የተማሪዎች ግራ የመጋባት ችግር ተቀርፎ ክንውኑ በተሳካ ሁኔታ እንዲሄድ ይረዳል” ይላሉ ከዚህ አኳያ ሲታይ የመምህራኑ ግንዛቤና አፈፃፀም በተማሪዎች እይታ በመካከለኛ ደረጃ ላይ ነው በተከታታይ የተደረገው የክፍል ምልከታ መረጃ እንደሚያሳየው ሁሉም ተተኳሪ መምህራኖች ይህንን ተግባር ሲያከናውኑ አለመመልከቱ ነው፡፡

ተማሪዎች ወደ ዋናው የመናገር ተግባር ከመግባታቸው በፊት ሞዴል (ምሳሌ) የሚሆኑ ተግባሮች ይቀርቡ እንደነበር ተጠይቀው ሲመለሱ 19.2% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 32.5% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 18.3% ተማሪዎች ለመወሰን ያቅተኛል፣ 11.6% ተማሪዎች አልስማማም፣ 18.3% ደግሞ በፍፁም አልስማማም በማለት መልስ ሰተዋል ይህንን በተመለከተ Harmer (2007.129) የመናገር ክሂል ትምህርቱ ከመከናወኑ በፊት ተግባራቱን ስዕሎችን በማቅረብ ልዩነታቸውን መግለፅ እንዲችሉ ማድረግ፣ በሰንጠረዥ መልክ የቀረቡ መረጃዎችን ማሟላት እንዲችሉ ማድረግና የመሳሰሉት ሞዴሎች ቢቀርብላቸው ተግባራቱ የውስብስብነት ባህሪይ እንዳይኖራቸው ያደርጋል በማለት ጠቅሰዋል፡፡ በዚህም መሰረት አብዛኛው መምህራን ይህንን ተግባር ያከናወናሉ ብለው ተማሪዎች በተሰጣቸው መጠይቅ

ቢየመላክቱም በተደረገው ተከታታይ ምልከታ መረጃ መሰረት አንድም መምህር ይህንን ተግበር ሲተገብር አልተስተዋለም፡፡

ባጠቃላይ ሲታይ የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ በአቀራረብ ደረጃ ከሁሉም የጽሁፍ መጠይቅና ምልከታ ለመረዳት እንደተቻለው ወደ ዋናው ትምህርት ገመግባታቸው በፊት የማነቃቂያ ተግባር ሁሉም መምህራን ያለማከናወናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የእለቱን ትምህርት አላማ ከመግለጽ አንጻር የተወሰኑ መመህራን ሲያቀርቡ ተስተውሏል፡፡

### 4.1.2 መምህራን የመናገር ክሂል ትምህርት ሲተገብሩ የልምምዱን ሂደት መመርመር

*ሰንጠረዥ-6* የመናገር ክሂል ትምህርት የልምምድ ተግባርን የሚያሳይ ከምልከታ የተገኘ

*መግለጫ*

| ተ/ቁ | የማስተማር ዘዴው ትግበራ | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይ | |
| | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| 7 | በልምምድ ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ ጉልቶ ይታይ ነበር? | 4 | 50% | 4 | 50% |
| 8 | ተግባሩን ለማለማመድ የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ ተጠቅመዋል? | 4 | 50% | 4 | 50% |
| 9 | የመናገር ክሂልን ማለማመድ የሚያስችሉ ተግባራትን (ክርክር፣ በጭውውትና በውይይት መልክ) ተከናውኗል? | 6 | 75% | 2 | 25% |
| 10 | የመናገር ክሂል ልምምዱን ለማድረግ በግል፣ በጥንድ ወይም በ1 ለ5 የማስተማር ስነ-ዘዴ ተጠቅመው ነበር? | 8 | 100% | --- | ---- |

እንደ (Byrne 1986:34) አገላለጽ በልምምድ ወቅት የሚቀርቡ ይዘቶች ተማሪዎች በተሠጣቸው ሞዴል መሰረት ተለማምደው ቀጣዩ የመናገር ትምህርት ልምምዶች እንዲፈፅሙ አቀራረቡ ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር አብሮ የሚሔድ፣ ጊዜ የማይወስድ፣ አጭርና ግልጽ እንዲሁም ከተማሪዎች ነባራዊ ህይወት ጋር መሔድ ይኖርበታል ይላሉ፡፡ ነገር ግን የምልከታው መረጃ እንደሚጠቁመን 50%ቱ የቀረበውን የንግግር ክሂል ትምህርት ገለጻ ሲሰጡ የቀሩት 50%ቱ ግን ሳይሰጡ ወደ ልምምድ እንዲገቡ በማድረጋቸው ተማሪዎች የሚሰሩትን ስራ በአግባቡ ሳይረዱ በቀጥታ ወደ ልምምድ ተግባር የገቡበት ሁኔታ ታይቷል፡፡ ይህ በመሆኑ የተወሰኑት ተማሪዎች ተሳትፏቸው በከፊል እንደነበር መገንዘብ ይቻላል፡፡

መምህራኑ በትምህርት የተመደበውን ጊዜ ለማነቃቂያ፣ ለማስተዋወቂያ፣ ለማለማመጃ ለማጠናከሪያና ለመገምገሚያ ወይም ማጠቃለያ ከፋፍለው በዕለቱ ትምህርታቸው አሰጣጥ ላይ አልተስተዋለም፡፡ በሰንጠረዥ ላይ እንደተገለጸው ወይም ወደ ትምህርቱ ከመግባታቸው በፊት የማነቃቂያ ጊዜ ሁሉም መምህራን አለመስጠታቸው ተገልጿል፡፡ በመሆኑም በምልከታው እንደታየው ጊዜን በአግባብ ከፋፍሎ የመጠቀሙ ሁኔታ ሳይሆን በጥቅል ተግባሩ ሲከናወን ነው የታየው፡፡

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ ማስተዋል የሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራኖች ልምምዱን ለማድረግ የተጠቀሙት በክርክርና በውይይት መልክ 6(75%) ሲሆን 2(25%) የመማር ማተማር ተራክቦ በግል ነው፡፡ ልምምዱም የተከናወነው የተመረጡት ርዕሶች *"ሱስ ማቆም፣ ይቻላል ወይስ አይቻልም?" እና "ትዳር ጓደኛ ለመምረጥ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም"* በክርክር ልምምዱ ወቅት በምልከታ እንደታየው መምህሯ ለተማሪዎቹ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ገለጻ ከሰጡ በኋላ ተማሪዎች ቦታቸውን ያዙ፤ በመቀጠልም ድምፃቸው በማይሰማ ሁኔታ ዳኞች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለተማሪዎች ከገለፁ በኋላ የክርክር ልምምዱ ቀጠለ በዚህን ወቅት የክፍሉ ተማሪዎች ይረብሹ ስለነበር ተከራካሪዎቹ ምን እንደሚሉ በግልፅ አይሰማም ነበር፡፡

ሌላው በውይይት መልክ የቀረበው ልምምድ ነው፡: እንደ Tericia Hedge (1996:277) አገላለፅ ውይይት ተማሪዎች ለምልልስ አስፈላጊ የሆነ ቋንቋ እንዲጠቀሙ ያበረታታል፡፡ በሌላኛው ተናጋሪ ላይ በተወሰነ ጊዜ ምስል እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ በርግጥም ውይይት ከሌሎቹ ተግባራት የበላይነትን ይይዛል፡፡ ይኸውም ለተማሪዎች የርስ በርስ ግንኙነት አጋጣሚ ይፈጥራል በማለት ያስቀምጣሉ፡፡

ከምልከታው እንደተረዳነው አብዛኛው መምህራን የንግግር ልምምድ ተግባሩን ያከናወኑት 75% በክርክር፣ በውይይት እና በጭውውት ሲሆን፤ 25% በተናጠል በሚል እንደነበር ያመለክታል፡፡

Tricia Hadge (1996 278- 280) መምህራን ሚናን ከተለያዩ ተግባራት ማለትም ከቀላል ምልልስ እስከ ውስብስብ ውክልና ከተለያዩ ደረጃዎች ጋር በማያያዝ መተግበር ይችላሉ፡፡ የሚና ተግባር በእውነተኛ ህይወት ላይ የተመሰረተ ለነፃ ውይይት ቀላል ሆኖ ያገኙታል፡፡ ምክንያቱ ተማሪዎች ሌላውን ሰው መስለው ሲጫወቱ ይደሰታሉ፡፡ ግልፅ ግብ ያለው ሚና መጫወት ለነፃ ውይይት ዓላማና አቅጣጫ ያሳያል፡፡ የሚና ጨዋታ ውድድርና መተጋገዝን ያካትታል፡፡ ይህም ሳቢ ያሳድገዋል በማለት ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም መምህራን የመናገር ልምምዱን ተግባር በዚህ

መልክ ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡ ከምልከታው ማየት እንደተቻለው ሁሉም መምህራን በግል፣ በጥንድ፣ በ1 ለ 5 ተግባሩን አከናውነውታል፡፡ በመሆኑም 100% ተተግባሪ ሆኗል ማለት ይቻላል፡፡

*ሠንጠረዥ 7. የመናገር ክሂል ትምህርት የልምምዱን ተግባር የሚያሳይ መግለጫ*

| ተ.ቁ | ማስተማር ዘዴው ትግበራ | አመራሮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይ | |
| | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| 11 | በልምድ ጊዜ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሣተፉ ይደረግ ነበር? | 2 | 25% | 6 | 75% |
| 12 | ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎች እንዲለማመዱ ይበረታቱ ነበር? | - | - | 8 | 100% |
| 13 | ልምምድ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዙ የተለያዩ ዘዴዎች ይጠቀሙ ነበር? | 2 | 25% | 6 | 75% |
| 14 | በልምምድ ወቅት ተማሪዎች እርስ በርስ በመወያየት ልምምድ እንዲያደርጉ ይበረታቱ ነበር? | 6 | 75% | 2 | 25% |
| 15 | ተማሪዎቹ ያልገባቸውን ጥያቄዎች እንዲያቀርቡ ሰፋ ያለ ዕድል ተሰቷቸዋል? | - | - | 8 | 100% |
| 16 | በልምምድ ወቅት ተማሪዎች ሲሳሳቱ ለመርዳት ጥረት ተደርጎ ነበር? | - | - | 8 | 100% |

(Harmer 2007:55) የመናገር ክሂልን ለማሳደግ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ሊያሳትፉ የሚችሉ ተግባራት መቅረጽ ያስፈልጋል፡፡ የመናገር ክሂልን ተግባራት ሲዘጋጅ ተማሪዎቹ ሙሉ በሙሉ በትምህርቱ እንዲሣተፉ እድል የሚሰጡና ከልምምዱ በኃላ የመምህሩ ምጋቤ ምላሽ ግምት ውስጥ የሚያስገቡ ከሆነ ተማሪዎቹ በትምህርቱ እርካታ ያገኛሉ፡፡ ይህም ተማሪዎቹ የታለመውን አላማ በቀላሉ እንዲደርሱበት ይረዳል፡፡ ተግባራቱ ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፍ ከሆነ ክፍሉ ያለምንም ችግር ተግባቦቱ የሰመረ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎቹን በራስ የመተማመን ስሜት ከፍ በማድረግ በንግግር ሀሳብን መግለጽ የቋንቋ ትምህርት ክፍል ባህል እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፆኦ ያደርጋል በማለት ገልፀዋል፡፡ በዚህም መሠረት በክፍል

ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ የማድረጉ ፋንታ መምህሩ ለልምምዱ ይዞት የሚቀርበው የመለማመጃ ርዕስ ከፍተኛውን ሚና ይጫወታል፡፡ ከሠንጠረዡ ለመረዳት እንደተቻለው  አንድ መምህር ብቻ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ጥረት ሲያደርግ ነው የታየው፡፡ አብዛኞቹ መምህራኖች ልምምዱ ሲተገበር የነበረው በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ መሆኑን እንረዳለን፡፡ በምልከታውም የታየው የተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ መድረኩን ይዘው ልምምድ እንደተከናወነ ለማየት ተችሏል፡፡ ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን የማበረታታቱ ጉዳይ በሁሉም መምህራን አልታየም፡፡ ይህም በመሆኑ የመናገር ልምምዱ ተግባር ይከናወን የነበረ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡ በልምምድ ወቅት ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎች ችግር ur (1996፤121) ተማሪዎች የመናገር ችግር ከሚያጋጥማቸው መካከል ዋና ዋናዎቹ መታቀብ፤ የሚናገሩትን ነገር ማጣትና ዝቅተኛ ወይም ሁሉን ያለማከለ ተሳትፎ አለማከናወኑ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

በዚህም መሠረት ከምልከታው እንደተረዳነው 100%ቱ መምህራኖች እንዚህን ተማሪዎች መርዳት እንዳልቻሉና መማር ማስተማሩን ተግባር እንዳልተተገበረ ያመላክተናል፡፡ የትምህርቱ ተግባር ሲከናወን በተማሪዎች ዘንድ የተመጣጠነ ተሳትፎ ወይም ልምምድ መከናወን እንዳለበት እሙን ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ Byrne(1987:55)ሲገልፁ፤ *"በክፍል ውስጥ በሚደረገው የንግግር ትምህርት ተግባራት ተሳትፎ በተወሰኑ ተማሪዎች እንዳይያዝ መምህራን ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደርጉ ይገባል"* ይላሉ፡፡ በዚህም መሠረት በምልከታው እንደተመለከትነው አንድ መመህር ብቻ በልምምድ ወቅት ሁለት ተማሪዎች እየተፈራረቁ ሀሳባቸውን ሲገልፁ "እረአባካችሁ ተናገሩ ሀሳባችሁን በፈለጋችሁት መንገድ አቅርቡ ሁለት ልጅ ብቻ የማስተምር መሰለኝ" በማለት ሀሳባቸውን ሲያቀርቡ ተስተውሏል፡፡ የተቀሩት መምህራን በቀረቡት ሀሳቦች ብቻ ክፍለ ጊዜው ተጠናቋል፡፡ እንደውም አንዷ መምህር የክርክሩን ልምምድ ማጠቃለያ ሳይሰጡበት እና ምንም ሀሳብ ሳይናገሩ ተማሪዎቹ ብቻ ተለማምደው ክፍለ ጊዜው ተጠናቋል፡፡ ከዚህ መረዳት የምንችለው አብዛኛው መምህር ተግባሩን በአጥጋቢ ሁኔታ እንዳላከናወኑት እንመለከታለን፡፡

Harmer (2007: 129-130) የተማሪዎችን የመናገር ክሂል ማለማመድ የሚችሉ ተግባራትን ሲገልጹ ተማሪዎቹ የሚፈልጉትን ርዕስ በመምረጥ እርስ በርስ ቃለ መጠይቅ እንዲያደርጉ ማድረግ፤ የተለያዩ መረጃዎችን ሰብስበው በማደራጀትና በመለማመድ በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ማድረግ ወይም በቤታቸው ያነበቡትን ቅንጫቢ ወይም ሙሉ ሥራ በንግግር እንዲያቀርቡ ማድረግ፤ በቡድን በመመደብ ከሚደግፉት ሀሣብ አንፃር ወግነው እንዲከራከሩ ማድረግ

የተማሪዎቹን የመናገር ክሂል ለማዳበር ጥሩ መንገድ ነው በማለት ያብራራሉ፡፡ በዚህ መሠረት ተማሪዎቹን በቡድን በመሆን እርስ በርስ ውይይት ማድረግን በተመለከተ ከምልከታው እንደታዘብነው አብዛኛውን መምህራን የመናገር ልምድን ተግባር ያከናወኑ ሲሆን አንድ መምህር ብቻ አለማከናወኑን እንመለከታለን፡፡ ለተማሪዎቹ የቀረበው ርዕስ ጉዳይ ግልጽ መሆንና የነሱን ደረጃ የመጠነ መሆኑ እንዳለበት እሙን ነው፡፡ በመሆኑም ከምልከታው ለመገንዘብ እንደተቻለው ተማሪዎቹ የተለያዩ ሀሳቦችን በመሰንዘር ሀሳባቸውን ሲያብራሩ የልምምዱ ተግባር ይከናወን የነበረው በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ ነበር፡፡ በዚህም ወቅት ሁሉም መምህር ወይም 100%ቱ ለተማሪዎቹ ምንም ዓይነት የጥያቄ ዕድል ያልሰጡ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡

(Byrne1987:74) መምህሩ በተማሪዎች ልምምድ ወቅት ሀሣባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ ማድረግ አለበት፡፡ ልምምዱንም ሲቆጣጠር እንደ ተማሪዎቹ ፍላጎት፤ እንደሚጠየቁት ጥያቄ ሁኔታ የተለያዩ እርዳታዎችን የሚያደርግበትና ምክር የሚሰጥበት መሆን ይኖርበታል፡፡ አብዛኛውን መምህራን በጥሩ ሁኔታ ካቀረቡና ተማሪዎችን ካለማመዱ መጨረሻ ላይ ተማሪዎቹ ምን ያሕል መሻሻል እንዳሳዩ የሚመለከቱበት ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የራሳቸውን የቃላትና የሰዋሰው እውቀትን በመጠቀም ሀሳብ አፍልቀው የሚገልፁበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል በማለት ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በልምምድ ወቅት መደገፍ ማረቅ (ሲሳሳቱ) ማስተካከል ይኖርባቸዋል፡፡ ከምልከታው የተረዳነው ሁሉም መምህራኖች ተማሪዎቻቸው ሲሳሳቱ ዝም ብለው ሀሳባቸውን ከማዳመጥ በስተቀር ለማስተካከል የሞከረ አልነበረም፡፡ ስለዚህም የልምምዱ ተግባር በአግባቡ አለመከናወኑን ያመለከተናል፡፡

ሠንጠረዥ 8:-ተማሪዎች የመናገር ተግባራትን እንዲለማመዱ ከመምህሩ መጠይቅ የተገኘ

መግለጫ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | የመላሾች ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ 4 | | አብዛኛውን ጊዜ 3 | | አንዳንድ ጊዜ 2 | | ጨርሶ 1 | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 6 | በክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት የሚሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች በተማሪዎች የህይወት ገጠመኝ ዙሪያ እንዲለማመዱ አደርጋለሁ? | 1 | 25% | - | - | 3 | 75% | - | - |
| 7 | በራሳቸዉ የቋንቋ እዉቀት ተጠቅመዉ ሀሳባቸዉን የሚገልፁበት መንገድ አመቻቻለሁ? | 1 | 25% | 2 | 50% | 1 | 25% | - | - |
| 8 | አብዛኛዉን ጊዜ ለመናገር የማይደፍሩና ሀሳባቸዉን ለመግልፅ የሚያዳግታቸዉ ተማሪዎች እንዲናገሩ የተለያዩ መንገዶችን አመቻቻለሁ? | - | - | 3 | 75% | 1 | 25% | - | - |
| 9 | የመናገር ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት አስተምራለሁ (አለማምዳለሁ)? | 1 | 25% | 2 | 50% | 1 | 25% | - | - |
| 10 | የተማሪዎች የንግግር ክሂል ለማዳበር የሚታዩ ነገሮችን ስዕል ፧ቅርፃቅርፅ፧ ካርታ ወዘተ በመስጠት እንዲለማመዱና እንዲናገሩ አደርጋለሁ? | 1 | 25% | 2 | 50% | 1 | 25% | - | - |
| 11 | ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል ሀሳብ ለሀሳብ እንዲለዋወጡ አደርጋለሁ? | 1 | 25% | 3 | 75% | - | - | - | - |

በሠንጠረዡ እንደተመለከትነው በመማር ማስተማሩ ሂደት የመምህሩ ሚና ተማሪዎቹ ተግባራቱን ከራሳቸዉ የህይወት ገጠመኝ ዙሪያ ወይም ከአካባቢያቸዉ ነባራዊ ሁኔታ ተነስተዉ ሃሳብ የሚያቀርቡበትን መንገድ ተጠይቀው አንድ መምህር "ሁል ጊዜ" 75%ቱ "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚያመቻቹ መልስ ሰጥተዋል፡፡ እንደሚታወቀዉ ማንኛዉም ተማሪ ሀሳቡን በአግባቡ

ለመግለፅ የሚችለዉ ከሚያዉቀዉና ከገጠመኙ በመነሳትና ከህይወት ልምዱ ጋር በማዛመድ መሆኑ ግልፅ ነዉ፡፡ ከሰንጠረዡም እንደምንረዳዉ ሦስት መምህራን ይህንን ዕድል

እንደማይሰጡ ሲገልፁ አንድ መምህርት ብቻ ይህንን ተግባር እንደምታከናዉን ገልፃለች፡፡ እንደ Harmer (1995-105) በተግባ„ ሄደት ተማሪዎች አስቀድመዉ በተወሰነ ነገር ላይ ተዘጋጅተዉ ወይም ተለማምደዉ እንዲያከናዉኑት በማድረግ እንዲሳተፉ ማድረግ ነዉ፡፡ በዚህ ጊዜ ርዕሱን ተማሪዎች መምረጥ የሚችሉበትን ሆኔታ በማመቻቸት በክርክር ወይም በዉይይት መልክ እንዲያከናዉኑ ማድረግ ይቻላል በማለት ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩል የመናገር ክሂል መለማመዱ ተማሪዎች በራሳቸዉ እዉቀት ተጠቅመዉ ሀሳባቸዉን በነፃ እንዲገልፁ የማያደርጉበትን ሁኔታ ተጠይቀው አንድ መምህር "ሁልጊዜ" 50%ቱ መምህራን "አብዛኛዉን ጊዜ" አንድ መምህር ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" የልምምዱን ሁኔታ እንደሚያመቻቹ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ተማሪዎቹ በቋንቋቸው ተጠቅመዉ ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሀሳባቸዉን በነፃ መግለፅ የሚችሉበት መንገድ ማመቻቸት የፍራሃትን ስሜት እንደሚቀንስ ከማድረግም በላይ በራሳቸዉ እንዲተማመኑ መንገድ እንደሚከፍት Harmer (1995) ይገልፃሉ፡፡

ከሰንጠረዡ እንደሚታየዉ የጽሑፍ መጠይቁን ከሞሉት ተተኳሪ መምህራን መካከል 75%ቱ "አብዛኛዉን ጊዜ" አንድ መምህር "አንዳንድ ጊዜ" ለመናገር የማይደፍሩና ሐሳባቸዉን ለመግለፅ የሚቸገሩ ተማሪዎች በነፃ እንዲናገሩ የተለያዩ መንገዶች እንደሚያመቻቹ ገልፀዋል፡፡ ከላይ እንዳየነዉ አንድም መምህር ይህንን ተግባር "ሁልጊዜ" እንደማያከናዉን መምህራኑ ከሰጡት መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል ፡፡

አብዛኞቹ ሙሁራን የሚስማሙት በክፍል ዉስጥ በመማር ማስተማር ሂደት ብዙ ተማሪዎች በሚኖሩበት ክፍል ዉስጥ በግል ከሚደረገዉ የመማር ማስተማር በጥንቃቄ የሚደረግ የቡድን ስራ በበለጠ መልኩ በክፍል ዉስጥ ለመናገር የማይደፍሩትን የሚያበረታታ ሐሳባቸዉን ለመግለፅ ቃላት የሚያጥራቸዉን እንዲናገሩ የሚያነሳሳና አብዛኛዉን ተማሪ በእኩል ሊያሳትፍ የሚችል በመሆኑ ተመራጭ ነዉ፡፡ በመሆኑም በልምምድ ተግባር ሂደት ወቅት መምህራኑ ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን እንዲናገሩ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ተግባራዊ ማድረግ እንደሚኖርባቸዉ እንረዳለን፡፡

እንደ Beygete (1987፡11) በአራቱ የክሂል ዘርፎች መካከል ጥብቅ ግንኙነት አለ የምንልበት ምክንያት አንዱን ክሂል በምናስተምርበት ጊዜ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ሁሉንም

ክሂሎች ለማስተማር ስለምንገደድ ነዉ፡፡እንዲሁም የንግግር ክሂል ከሌሎች ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ቢኖረዉም የራሱ የሆነ መለያ ባህሪ አለዉ፡፡ በተጨማሪም የመናገርና ማዳመጥ ክሂል የማይነጣጠሉና አንደኛዉ ከሌላኛዉ ጥብቅ ቁርኝት ያላቸዉናቸዉ፡፡ ጥሩ ለመናገር ጥሩ አዳማጭ መሆንን ብዙ ሙሁራን ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም የመናገር ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማስተማርን መምህራን ምን ያህል ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ተጠይቀዉ፤ አንድ መምህር "ሁል ጊዜ" 50%ቱ "አብዛኛዉን ጊዜ" አንድ መምህር "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚተገብሩት ከሰጡት ምላሽ መረዳት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር የሚታዩ ነገሮች ስዕል ፤ ቅርፃቅርፅ፤ ካርታ ወዘተ በመስጠት እንዲለማመዱ የማድረጉ ሁኔታ ተጠይቀዉ አንድ መምህር "ሁልጊዜ" 50%ቱ መምህራን "አብዛኛዉን ጊዜ" አንድ መምህር ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ግን በተደረገዉ ተከታታይ የክፍል ወስጥ ምልከታ መረጃ መረዳት እንደሚቻለዉ ይህ ተግባር አንድም መምህር ተግባራዊ ሲያደርገዉ አልታየም ፡፡

እንደ Harmer (2007:129) የመናገር ክሂል ተግባርን ግልፅ አድርጎ ለማስተማር የስዕሎችን ልዩነት እንዲገልፁ ማድረግ፤ አቅጣጫን ማሳየት በሰንጠረዥ መልክ የቀረቡ መረጃዎችን ማሟላት እንዲችሉ ማድረግ ተግባራቱ ዉስብስብነት ባህሪ እንዳይታይባቸዉ ያደርጋል ይላሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የተማሪዎቹን የመናገር ክሂል ለማዳበር ተማሪዎች በቡድን በቡድን በመከፋፈል ሃሳብ ለሃሳብ እንዲለዋወጡ የማድረጉን ሆኔታ መምህራን ተጠይቀዉ ሲመልሱ 1(25%) መምህር "ሁሉጌዜ " 3(75%)ቱ ደግሞ "አብዛኛዉን ጊዜ" እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን በተደረገዉ ተከታታይ የክፍል ዉስጥ ምልከታ መረጃ መሰረት፤ ይህ ተግባር ከአንድ መምህርት በስተቀር ሌሎቹ መምህራን ሲተገብሩት አልታየም፡፡ የመናገርን ተግባር በማከናዉን ይበልጥ የሚታመነዉ ተማሪዎች ከቢጤዎቻቸዉ ጋር በመመደብ በተወሰነ ርዕሰ ጉዳይ ላይ እነዲወያዩና ሃሳባቸዉን በቡድኑ መሪ አማካኝነት እንዲያቀርቡ ቢደረግ ተመራጭነት አለዉ፡፡

*ሠንጠረዥ 9. የመናገር ክሂል ትምህርት የልምምድ ሂደትን በተመለከተ ከተማሪዎችን ምላሽ የተገኘ መግለጫ*

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | መልሶች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን ያቅተኛል | | አልስማማም | | በፍፅም አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 5 | በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን ውይይት፣ ክፍሉ በአንድነት በመሆን ወዘተ የመናገር ክሂል ተግባርን በክፍል ውስጥ የመከናወኑ ሁኔታ? | 42 | 35 | 23 | 27.5 | 14 | 11.7 | 16 | 13.3 | 15 | 12.5 |
| 6 | በግል፣ በጥንድ፣በሶስትዮሽ፣ በቡድን፣ ወዘተ የመናገር ክሂል ተግባራትን እየተዘዋወሩ በመከታተል ያበረታታሉ? | 33 | 27.4 | 36 | 30 | 18 | 15 | 19 | 15.8 | 14 | 11.7 |
| 7 | በክፍል ውስጥ ንግግርን በሪፖርት፣ በጭውውት፣ በክርክር፣ በውይይት መልክ ተግባራቱን መለማመዱ የንግግር ችሎታን አጉልብቷል? | 46 | 38.3 | 43 | 35.9 | 12 | 10 | 12 | 10 | 7 | 5.8 |
| 8 | በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት የመናገር ክሂል ተግባራት ከተማሪው የህይወት ልምድ ጋር የተቆራኙ ናቸው? | 29 | 24.2 | 34 | 28.3 | 28 | 23.4 | 19 | 15.8 | 10 | 8.3 |

ከላይ ከሰንጠረዡ እንደሚታየው ተማሪዎች የመናገር ክሂል በክፍል ውስጥ ሲቀርብ በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን ውይይት ይለማመዱ ወይም አይልማመዱ እንደሆነና ልምምዱን ሲያከናውኑ መምህራን ክትትል ድጋፍ ያደርጉ ወይም አያደርጉ እንደሆን ለመፈተሽ ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኞቹ ተማሪዎች አውንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል 35% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 27.5% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 11.7% ተማሪዎች ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 13.3% ተማሪዎች አልስማማም፣ 12.5% ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ በተደረገው ተከታታይ ምልከታ መረጃ መሰረት ይህንን ተግባር የተገበሩ መምህራን ሁለት ሲሆኑ፤ ሌሎቹ መምህራኖች ሲተገብሩት አልተስተዋልም፤ ምናልባትም ተማሪዎቹ በሌላ ክሂል የተገበሩትን የመናገር ክሂል ልምምድ አድርገው የወሰዱ ሊሆን ይችላል፡፡

በሌላ በኩል የመናገር ክሂል ተግባራት ሲከናወኑ መምህራኑ እየተዘዋወሩ በመከታተል ተማሪዎችን ያበረታታሉ ለሚለው ሲመልሱ 27.4% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 30% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 15% ተማሪዎች ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 15.8% አልስማማም ፣ 11.7% ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት ወስነዋል፡፡

በተከታታይ በተደረገው ምልከታ መረጃ መሰረት ከአንድ መምህርት በስተቀር ተግባሩን ሲያከናውኑ አልተስተዋለም፡፡ ተማሪዎች በቡንድን፣ በጥንድ ተማሪዎችን ስንመድብ ስብጥሩን በደንብ መገንዘብ ይበጃል፡፡ ለልምምዱ ተማሪዎች ያላቸውን ችሎታ በመገምገም ምድቡ ከሶስቱም የተማሪዎች ደረጃ ቢሆን የተሻለ ይሆናል፡፡

ተማሪዎች የንግግር ትምህርቱን በተለያየ መልኩ መለማመዱ (በሪፖርት፣ ጭውውት ፣ክርክር ፣ውይይት) የመናገር ችሎታን አጎልብቷል ተብለው ሲጠየቁ 38.3% በጣም እስማማለሁ፣ 35.9% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 10% ለመወሰን ይቸግረናል 10% ተማማሪዎች አልስማማም ቡለው ሲመልሱ 5.8% ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያለው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚቀርብላቸው የመናገር ክሂል የልምምድ ተግባራት ከራሳቸው የህይወት ልምድ ጋር የተቆራኘ መሆኑን ተጠይቀው 24.2% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 28.3% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 23.4% ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 15.8% አልስማማም በማለት ሲመለሱ 8.3% ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ የመናገር ክሂል ልምምዱ ሲከናወን የሚመረጠው ርዕስ በተማሪዎች ቢሆን ልምምዱን ቀላልና የማያስቸግር ያደርገዋል፡፡ በመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ መልስ ላይ እንደሚያሳየው ይህንን ተግባር ሁል ጊዜ የሚያከናውኑ አንድም የለም በተጨማሪም በምልከታውም ላይ ሲተገበር የታየው ከመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በወጡ ርዕስ ጉዳይ ላይ ነው ተማሪዎች ሲከራከሩ የነበረው ስለዚህ ይህ አተገባበር በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ የንግግር ክሂልን በልምምድ ተግባር ወቅት ስንመለከት ከሁለቱ የጽሁፍ መጠይቅና በምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየን የውይይትም ሆነ የክርክር ርዕስ የተማሪው የህይወት ገጠመኝን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ የልምምዱ ተግባር የሚጠበቀውን ያህል እነዳለሆነ እንመለከታለን፡፡ በሌላ በኩል የልምምዱን ተግባር በጥንድ፣በቡድንና በግል የማከናወን ሂደት በጽሁፍ መጠይቁም ሆነ በምልከታው ሂደት በጥሩ ሁኔታ እነደተከናወነ ያመለክተናል፡፡

### *4.1.3 የመናገር ክሂል ትምህርት ሲተገበር በአፍልቆት ወቅት የሚታየውን ውጤት መፈተሽ*

*ሠንጠረዥ 10.* ተማሪዎች በአፍልቆት ወቅት ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ መምህሩ ያመቻቸበት ሁኔታ መግለጫ፤

| ተራ ቁ | የማስተማር ዘዴው ትግበራ | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 17 | የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን በማቅረብ የሚያዩትን ነገር በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ይደረግ ነበር? | _____ | _____ | 8 | 100% |
| 18 | የንግግር ተግባራቱ ተማሪዎችን በቀላሉ እና በነፃነት ሊያግባባ የሚችል ዐውድ በመፍጠር የተከናወኑ ናቸው? | _____ | _____ | 8 | 100% |
| 19 | ውይይት እና ክርክር በማዘጋቸት የመናገር ተግባር እንዲከናወን ተደርጓል? | 8 | 100% | _____ | _____ |
| 20 | የተሰጡት ተግባራት የትምህርቱን አላማ ያሳኩ ነበር? | 2 | 25% | 6 | 75% |
| 21 | ተማሪዎች ስህተት ሲፈጽሙ እርማቱ በወቅቱ ይሰጥ ነበር? | _____ | _____ | 8 | 100% |

Harmer(2007:129) ተማሪዎች በቡድን በቡድን ይቀመጣሉ ለእያንዳንዱ ቡድን ተከታታይነት ያላቸው መልዕክት አዘል ስዕሎች ይሰጣል፤ ቡድኖቹ ስዕሎቹ ከተመለከቷቸው በኋላ ይሰበሰባሉ፣ ከዚያም ከመጀመሪያዎቹ ቡድኖች አንዳንድ አባል ያያዙ ስዕሎች አዳዲስ ቡድኖች ይደራጃሉ። አዲሶቹ ቡድኖችም ቀደም ሲል ያዩት ስዕላዊ መግለጫ ምን መልእክት እንደሚያስተላልፍ ይናገራሉ። በመጨረሻም እያንዳንዱ ቡድን የቀረበው ታሪክ ተመሳሳይ ሀሳብ የያዘ መሆኑን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ቡድኖች የየራሳቸውን ታሪክ ለክፍል ያቀርባሉ። ይህም በሚቀርብበት ጊዜ የሚቀርበው ተግባራት ለተገልጋዮች ህይወት ቅርበት ያላቸው መሆኑን እንደሚገባቸው ያስረዳሉ። ከላይ በሙሁሩ እንደተገለፀው የመናገር ልምምድ ተግባርን ለማከናወን አንዱ መንገድ ስዕሎችን፣ ፎቶግራፎችን በማቅረብ በንግግር መልክ ማቅረብ መሆኑን እንረዳለን። ሆኖም ሰሠንጠረዡ እንደሚያሳየው ሁሉም መምህር በዚህ መልኩ

የመናገር ልምምዱን አላካናወኑም ወይም 100%ቱ ተግባራዊ አላደረጉም፡፡ በመሆኑም የመማር ማስተማሩ ክንውን በአግባቡ እንዳልተከናወነ ከሰንጠረዡ መረዳት ይቻላል፡፡
ተማሪዎች በቋንቋቸው ተጠቅመው ስለሚያከናውኑት ተግባር በቀላሉና በነፃነት ሊያግባባ የሚችል አውድ እንዲኖር መምህራን ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንዳለባቸው Harmere (1995፡105) ይገልፃሉ፡፡ ሆኖም ግን በመማር ማተማሩ ሒደት የመናገር ተግባራቱ ተማሪዎችን በቀላሉና በነፃነት ሊያግባባ የሚችል አውድ በመፍጠር የተከናወኑ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡ የክፍል ውስጥ ምልከታው መረጃ እንደሚያመላክተው 100%ቱ ይህንን ተግባር አላከናወኑም፡፤ ስለዚህም ይህ የልምምድ ተግባር የተሰጠው ትኩረት አለመኖሩን ከመረጃው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የመናገር ልምምድ ተግባርን በውይይትና በክርክር ሁሉም መምህር ተግብረዋል፡፡ ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው 100%ቱ የመማር ማስተማሩ ሒደት ተከናውኗል፡፡

የመናገር ክሂል ማስተማር ዓላማን እንደ Harmere (1995፡15) ተማሪዎች በቋንቋው ተጠቅመው ሃሳባቸው መግለጽ እንዲችሉ፣ ዘመናዊ በሆነ የክፍል ውስጥ የማስተማር ዘዴ ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በዚህም በቋንቋው የመጠቀም ችሎታቸውን ያዳብሩ ዘንድ አስፈላጊው ሁሉ ሊደረግ ይገባል፡፡ በመሆኑም የሚከተሉት ፋይዳዎች አሉት፡- ተገቢ ቃላትን በተገቢው ቦታ መጠቀም እንዲችሉ፣ አስተያየታቸውን በስማረጃ አስደግፈው ማቅረብ እንዲችሉ፣ ግላዊ አመለካከቶችን በንግግር ነጻ ሆነው እንዲገልጹ እና ኢ-መደበኛ አነጋገር አስወግደው መደበኛ አነጋገር ስልት እንዲጠቀም ይረዳቸዋል በማለት አስቀምጠዋል፡፡ የተሰጡት የልምምድ ተግባራት ዓላማውን ሙሉ በሙሉ ያሳኩ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡

ከምልከታው እንደተገኘው መረጃ መሰረት 75%ቱ መምህራን የተሰጡት ተግባራት ዓላማውን ያሳኩ አለመሆነቸውን ያሳየናል፡፡ መምህራኖች በልምምድ ወቅት ተማሪዎችን የመርዳትና የማገዝ ስራ መስራት እንዳለባቸው ይታወቃል፡፡ በምልከታው ወቅትም ተማሪዎች ሃሳባቸው በሚገልጹበት ወቅት ብዙ ስህተቶች ይከናወኑ ነበር፡፡ ለምሣሌ፡- በአንድ ክፍል የሚሰጡ የክርክር ሒደት ላይ ተማሪዎች ተራቸው ሳይጠብቁ የመናገር ሁኔታ፣ ከክርክሩ ርዕስ አፈንግጦ የመውጣት፣ የተቃራኒ ተከራካሪ ቡድንን ያለማክበር እና የመሳሰሉት ሁኔታዎች ተከስተው በመምህሯ የተሰጠ እርምት አልነበረም፡፡ ሰንጠረዡ እንደሚያመላክተው ተማሪዎች ስህተት ሲፈጽሙ እርምቱ በወቅቱ አለመሰጠቱንና ሁሉም መምህራን ይህንን ተግባር አለማከናወናቸውን ያሳየናል፡፡

*ሰንጠረዥ11 -ተማሪዎች ሃሳባቸዉን በነፃነት እንዲገልፁ በማድረግ ከመምህሩን ምላሽ የተገኘ መግለጫ*

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | የመላሽ ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 12 | የመናገር ተግባሩ ከቀረበና በዛላይ ከተለማመዱ በኋላ ሀሳባቸዉን በነፃነት እንዲገልፁ የማድረግ ሁኔታ? | 2 | 50% | 1 | 25% | 1 | 25% | - | - |
| 13 | የተማሪዎቹን ቁጥር ባገናዘበ መልኩ በቡድን(በህብረት)ተወያይተዉ ሀሳባቸዉን እንዲገልፁ አበረታታለሁ? | 1 | 25% | 2 | 50% | 1 | 25% | - | - |
| 14 | ተማሪዎች ከክፍል ዉጪ ሰዎችን ጠይቀዉ ወይም ምልከታ አድርገዉ እና የተለያዩ ፅሑፎችን አንብበዉ በክፍል ዉስጥ እንዲናገሩ ማድረግ? | - | - | 2 | 50% | 2 | 50% | - | - |
| 15 | በመናገር ትምህርት ወቅት በተማሪዎቹ ንግግር ጣልቃ በመግባት ስህተታቸዉን እንዲያርሙ አደርጋለሁ? | 1 | 25% | 1 | 25% | - | - | 2 | 50% |
| 16 | የመናገር ትምህርቱ ከመጠናቀቁ በፊት ተማሪዎቹ ጥያቄ እንዲጠይቁ አበረታታለሁ? | 2 | 50% | 2 | 50% | - | - | - | - |
| 17 | ስህተት እንደ አንድ የመማሪያ መንገድ አድርገዉ እንዲቆጥሩ አስገነዝባለሁ? | 1 | 25% | 1 | 25% | 2 | 50% | - | - |
| 18 | ተማሪዎቹ ስህተታቸዉን እርስበርስ እንዲተራረሙ የማመቻቸት ሁኔታ? | 1 | 25% | - | - | 3 | 75% | - | - |
| 19 | በቀረበዉ የንግግር ትምህርት ላይ የማሻሻያ ሀሳብ የመስጠት ሁኔታ? | 2 | 50% | 2 | 50% | - | - | - | - |

በዚህ የመናገር ትምህርት የመጨረሻ ደረጃ ልምምዱን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች በራሳቸው የቋንቋ እውቀት በመጠቀም ሃሳባቸውን አፍልቀው የሚገልፁበትን መንገድ መምህሩ የሚያመቻችበትን ሁኔታ መፍጠር ይኖርበታል፡፡

ከዚህ አንፃር የሰንጠረዡ መረጃ እንደሚያመለክተው 50%ቱ መምህራን “ሁልጊዜ” አንድ መምህርት “አብዛኛውን ጊዜ” በማለት ስትገልፅ አንድ መምህር ደግሞ “አንዳንድ -ጊዜ” በማለት

ተግባሩን እንሚተገብሩ ገልፀዋል፡፡ እንደሚታወቀው ተማሪዎች የልምምድ ተግባሩን ካጠናቀቁ በኋላ ሀሳባቸውን ለመግለፅ ምቹ ሁኔታ እንደሚያስፈልጋቸው የመስኩ ሙሁራን ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም ከሁለቱ መምህራን በስተቀር ሌሎች መምህራን ሁልጊዜ ሲተገብሩት አልታየም፡፡

Byrne(1986-75) በዝርዝር እንደገለፁት ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል በተለማመዱት የመናገር ክሂል ተግባር ላይ ተመስርተው በሚታዩ ነገሮች ላይ ተንተርሰው ውይይቶችን ክርክሮችን በማደራጀት ሃሳባቸውን የሚገልፁበትን መንገድ በማመቻቸት ማከናወን ይቻላል ከሰንጠረዡ እንደምረዳው አንድ መምህር "ሁልጊዜ" ተግባሩን ሲያከናውን 50%ቱ መምህራን "አብዛኛውን ጊዜ" አንድ መምህርት ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" እንደምትተገብረው ገልፃለች በተከታታይ ከተደረገው ምልከታ መረዳት እንደሚቻለው ከሁለት መምህራን በስተቀር ሌሎች መምህራኖች ሲተገብሩ አልተስተዋለም፡፡

በሌላ በኩል ተማሪዎችን ከቀረበላቸው ከመጽሀፍ መልመጃ ውጪ ሰዎችን ጠይቀው ወይም የተለያዩ ትዕይንቶችን ምልከታ አድርገው እና ጽሑፎችን አንብበው በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ የማመቻቸቱ ሁኔታ ከቀረበላቸው የጽሑፍ መጠየቅ አንድም መምህር ተግባሩን "ሁልጊዜ" እንደማያከናውኑ የታየ ሲሆን፤ 50%ቱ መምህራን "አብዛኛውን ጊዜ" ተግባሩን እንደሚያከናውኑ ሲገልጹ፤ 50%ቱ መምህራን ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚተገብሩት ገልፀዋል፡፡

በተጨማሪም በመናገር ትምህርት ወቅት በተማሪዎች ንግግር ጣልቃ በመግባት ስህተታቸውን የማረሙ ሂደተን መምህራኑ ሲገልፁ፣ አንድ መምህርት "ሁልጊዜ" ተግባሩን እደምታከናውን ስትገልፅ አንድ መምህር "አብዛኛውን ጊዜ" ሂደቱን እንደሚያከናውን ገልጿል 50%ቱ መምህራን ደግሞ "በጭራሽ" ተግባሩን እንደማያከናውኑ ገልፀዋል ሆኖም ግን በተከታታይ በተደረገው ምልከታ መረጃ መሰረት አንዳም መምህር ጣልቃ በመገባት ስህተታቸውን የማረሙ ሁኔታ አልታየም፡፡

ተማሪዎች የዕለቱ ትምህርት ከመጠናቀቁ በፊት ያልገባቸውን ጥያቄ እንዲጠይቁ የማበረታቱ ሁኔታ መምህራን ሲገልጹ 50%ቱ መምህራን ሁልጊዜ ተግባሩን እንደሚያከናውኑ 50%ቱ ደግሞ ተግባሩን "አብዛኛው ጊዜ" እንደሚተገብሩ ገልፀዋል በመሆኑም በተከታታይ በተደረገው ምልከታ አንድም መምህር ይህንን ተግባር ሲያከናውን አለመታየቱን ያሳየናል፡፡

እንዲሁም ተማሪዎች የመናገር ክሂል ትምህርቱን ተግባር ሲያከናውኑ ስህተት እንደ አንድ የመማሪያ መንገድ አድርገው እንዲቆጥሩ የሚስገነዝበውን ሁኔታ መምህራን ሲገልፁ አንድ

መምህርት “ሁል ጊዜ” እንደምትፈፅመው ስትገልፅ አንዷ መምህርት “አብዛኛውን ጊዜ” ተግባሩን እንደምታከናውን ገልፃለች፡፡ 50%ቱ መምህራን ደግሞ “አንዳንድ ጊዜ” እንደሚያከናውኑ ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ግን ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ሀሳባቸውን በነፃነት ለማቅረብ ከሚያደርጓቸው አንዱና ዋነኛው ምክንያት በተሰጣቸው ርዕስ ዙሪያ የመሰላቸውን ሀሳብ እንዳይገልፁ እንሳሳታለን የሚል ፍራቻ ይታይባቸዋል፤ ይህንን ችግር ለመቅረፍ መምህሩ ትምህርት መሆኑንና ቢሳሳቱም የመማር ማስተማሩ አንዱ አካል መሆኑን ገልፆ ሚናውን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡

ተማሪዎች ስህተታቸውን እርስ በርስ እንዲተራረሙና ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ የማበረታታት ሁኔታቸው ምን እንደሆነ ተጠይቀው አንድ መምህር “ሁልጊዜ” ተግባሩን እንደሚተገብር ሲገልፁ 75%ቱ መምህራን ደግሞ “አንዳንድ ጊዜ” ተግባሩን እንደሚያከናውኑ ገልፀዋል፡፡ በተከታታይ በተደረገው ምልከታ ላይም መረጃው የሚያመለክተው መምህራኑ ከሰጡት መረጃ ጋር ተመሳሳይነት ይታይበታል፡፡

በመጨረሻም ለቀረበው የመናገር ክሂል ትምህርት የማሻሻያ ሀሳብ የመስጠት ሁኔታ ተጠይቀው 50%ቱ መምህራን “ሁልጊዜ” ተግባሩን እንደሚያከናውኑ ሲገልፁ የተቀሩት 50%ቱ መምህራን ደግሞ “አብዛኛውን ጊዜ ተግባሩን እንደሚያከናውኑ ገልፀዋል”

## ሠንጠረዥ 12. የአፍልቆት ደረጃ የመናገር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ የሚያሳይ መግለጫ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | መልሶች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን ያቅተኛል | | አልስማማም | | በፍፁም አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 9 | በጥንድ፣በቡድን ወዘተ በመሆን የመናገር ክሂል ተግባራትን በመለማመድ እና በመከታተል የንግግር፣ የጭውውት ፣ የክርክር የውይይት ስርአት እንዲዳብር ተደርጓል? | 28 | 23.4 | 39 | 32.5 | 17 | 14.1 | 23 | 19.2 | 13 | 10.8 |
| 10 | የመናገር ተግባራትን ስታከናወኑ ሀሳብችሁን በነፃነት እንድትገልፁ ተደርጓል? | 50 | 41.7 | 35 | 29.1 | 18 | 15 | 9 | 7.5 | 8 | 6.7 |
| 11 | በጥንድ፣ በቡድን በመሆን ቃለመጠየቅ ማድረግ ስዕላዊ መግለጫዎች በሚያስተላልፉት ሀሳብ ላይ መወያየትና መከራከር እንዲሁም ሀሳብን ያለፍርሀት ለመግለፅ ተችሏል? | 29 | 24.1 | 35 | 29.2 | 23 | 19.2 | 20 | 16.6 | 13 | 10.8 |
| 12 | የጭውውት ፣ የክርክር፣ የውይይት ተግባራት በክፍል ውስጥ ከቀረቡ በኋላ በማጠቃለያ ያለምንም ፍርሀት አስተያት እሰጣለሁ? | 34 | 28.3 | 33 | 27.5 | 23 | 19.2 | 19 | 15.8 | 11 | 9.2 |
| 13 | ስህተታችን በቀጥታ ከመናገር ይልቅ እርስበርስ እንድንተራረም ይደረግ ነበር? | 36 | 29.2 | 34 | 28.4 | 17 | 14.2 | 18 | 15 | 15 | 12.5 |
| 14 | ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎች እንዲናገሩ ይበረታታሉ? | 38 | 31.7 | 36 | 30 | 17 | 14.2 | 9 | 7.5 | 20 | 16.6 |
| 15 | የመናገሩ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል ይሰጣሉ? | 57 | 47.4 | 25 | 20.8 | 13 | 10.9 | 10 | 8.4 | 15 | 12.5 |

የመናገር ክሂልን በክፍል ዉስጥ ተማሪዎች እንዲማሩ የሚደረግበት ምክንያት መናገር፣ ክርክር፣ ዉይይት ሲያደርጉ መረጃ አሰባስበዉ፣ አደራጅተዉና ተለማምደዉ ሀሳባቸዉን መግለጽ እዲችሉና የነዚህ ተግባራት ቅድመ ስርአት ማወቅ እንዲችሉ ማድረግ ነዉ፡፡ ስለሆነም ተማሪዎቹ የቀረበላቸዉን ጥያቄ የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ዉስጥ ማቅረባቸዉ እና መከታተላቸዉ የጭዉዉት ፣ የክርክር፣ የዉይይት ወዘተ ስርዐት ለማወቅ የረዳቸዉ መሆንኑና አለመሆኑን የሚመለከት ሲሆን ፣መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ዉስጥ 23.4% በጣም እስማማለሁ ፣ 32.5% እስማማለሁ፣ 14.1% ተማሪዎች ለመወሰን ይቸግረኛል 19.2% አልስማማም በማለት ሲመልሱ 10.8% ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማምም በማለት ተግባራቱን አለመፈጸማቸዉን ገልጸዋል፡፡ ይህ ማለት ለምሳሌ በክርክር ጊዜ ክርክሩ ተራ በተራ አካሄድ ወይስ እያጠናቀቁ የመሄድ ስልትን እንደሚከተል ማወቅ አንዱ የክርክሩ ስርዐት ሲሆን ፣ በክርክሩም ሃሳብ እንደተዘረጋ ከተከራካሪዎቹ ሃሳብ ሲቀርብ ሌሎች የሚያደምጡ መሆኑን ፣ጥያቄና የተቃራኒ ሀሳብን ውድቅ ማድረጊያ ሀሳብ ቀርቦ ፣ ዉሳኔ በድምጽ ወይም በዳኞች የሚሰጥ መሆኑን ማወቅ ከተከራካሪዎች የሚጠበቅ ነዉ፡፡ስለሆነም አብዘሃኛዎቹ ተማሪዎች ክርክር ፣ጭዉዉት በክፍል ዉስጥ ማቅረባቸዉ እነዚህንና ሌሎች መሰል ስርዐቶችን ለማወቅ እንዲረዳቸዉ አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህ ዉጭ የሆኑት ተማሪዎች ግን ግልጽ ግንዛቤ የሌላቸዉና በሃሳቡ የማይስማሙ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የመናገር ተግባራትን ስታከናውኑ ሀሳባችሁን በነጻነት እንትገልጹ ተደርጓል ወይ ተብለዉ ለተጠየቁት ሲመልሱ 41.7% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ ፣29.1% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 15% ተማሪዎች ለመወሰን ይቸግረኛል፣ 7.5% ተማሪዎች አልስማማም፣ 6.7% ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚሁ ጥያቄ ጋር ተያያዥነት ያለዉ ጥያቄ የተለያዩ የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ዉስጥ መለማመዳቸዉ ሀሳባቸዉን ያለፍርሃት ለመግለጽ ያስቻላቸዉ ወይም ያላስቻላቸዉ መሆኑን የገለፀ ነበር? 24.1%እና 29.2% ተማሪዎች ማለትም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሀሳባቸዉን ያለፍርሀት መግለጽ መቻላቸዉን ገልጸዋል፡፡ ሌሎቹ ግን 19.2% መወሰን እንዳቃታቸዉና 16.6% እና 10.8% ተማሪዎች አለመስማማታቸዉን ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ግን በተከታታይ በተደረገዉ ምልከታ መረጃ መሰረት መገንዘብ የተቻለዉ ማንኛዉም መምህር ተማሪዎችን ፍርሃታቸዉን እንዲያስወግዱ ሲያከናዉኑ አልታዩም፡፡ እንዲሁም በመምህራን የጽሁፍ መጠየቅ መረጃ እንደሚያሳየዉ ተግባራቱን ሁልጊዜ እንደማያከናዉኑት ለመረዳት ተችሏል፡፡

ተማሪዎች የጭዉዉት ፣የክርክር ፣የዉይይት ተግባራት በክፍል ዉስጥ ከቀረቡ በኋላ በክፍል ጊዜው ማጠናቀቂያ ላይ አስተያየት መስጠታቸውን ተጠይቀው 28.3% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 27.5% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 19.2% ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 15.8% ተማሪዎች አልስማማም እና 9.2% ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡

በመናገር ክሂል አቀራረብ የሚደረግ ማጠቃለያ ሀሳብ አሰጣጥ ተማሪዎች በሂደቱ እንዲሳተፉ እርስ በእርስ እንዲተራረሙ ከተደረገ በኋላ በመምህራን ቢጠቃለል የተማሪዎች የእርስ በእርስ ተራክቦና በራስ የተማመን ስሜት እየጐለበተ ሊሄድ ይችላል፡፡

እንደ Sesnan (1997:181) ገላፃ ብዙ ሰዎች በቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ሲተራረሙ ስሜታቸው ይጐዳል ብለው ያስባሉ፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች በዕለት ተዕለት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንደሚታየው (ለምሳሌ ሲጫወቱ) እርስ በርስ ይተራረማሉ፤ መተራረሙንም በደስታ ሲቀበሉት ይታያል ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ መሰረተ ሀሳብ በመነሳት ተማሪዎች ስህተታቸውን እርስበርስ እንዲተራረሙ ይደረጋል ወይ ተብለው ከተጠየቁ ማሪዎች መካከል 29.2% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 28.4% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 14.2% ተማሪዎች ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 15% ተማሪዎች አልስማማም፣12.5% ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ሆኖም በተደረገው ተከታታይ ምልከታ እርስ በርሳቸው ሲተራረሙ እንዳልታየ ነው የሚያሳየው፡፡ እንዲሁም የመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ እንደሚያሳየው ከአንድ መምህርት በስተቀር ሌሎቹ አንዳንድ ጊዜ እንደሚተገብሩት ነው የገለፁት፡፡

በመጨረሻም ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎች እንዲናገሩ ይበረታቱ ነበር ተብለው ተጠይቀው 31.7% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 30% ተማሪዎች እስማማለሁ፣14.2% ተማሪዎች ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 7.5% ተማሪዎች አልስማማም ሲሉ 16.6% ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡እንዲሁም የመናገሩ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል ይሰጥ ነበር ለሚለው ተማሪዎች ሲመልሱ 47.4% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ ፣ 20.8% እስማማለሁ ፣ 10.9% ተማሪዎች ለመወሰን ያቅተኛል ፣ 8.4% ተማሪዎች አልስማማም በማለት ሲመልሱ 12.5% ተማሪዎች በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡

በጥቅሉ ሲታይ ከተማሪዎች የፅሑፍ መተይቅ የተገኘው ምላሽ በመጠኑ ከመጋነኑ በስተቀር ከሶስቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎች ውጤት ብዙም የጎላ ልዩነት

አይታዩበትም። ምልከታ በተደረገበት ጊዜ በአፍልቆት ደረጃ በተለይ በአንድ ክፍል ውስጥ የተማሪዎች የርስበርስ መስተጋብር በቀረበው የክርክር ርዕስ ላይ ተከራካሪዎቹ የክርክሩን ደንብ ባለማወቅ ደንብ ሲጥሉ እንደነበር ተመልካቾቹ ስርዓት ያለመያዝ እና ያለማዳመጥ ሁኔታ ይታይ እንደ ነበር ታይቷል። የመከራከር እድል ካገኙ ተማሪዎች መካከል የተወሰኑት ተማሪዎች በቂ ዝግጅት የማድረግ ፣ ሀሳባቸውን አደራጅተው የመናገር ፣ የሀሳብ ማሚያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሀሳብ የማስተላለፍ ችግር ከልምምድ ማነስ የተነሳ ይታይ እንደ ነበር በመገንዘብ ተችሏል።

## 4.2. የመረጃዎቹ ትንተና ማብራሪያ

### 4.2.1 የመናገርን ክሂል ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች ክንውኖች

በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚቀርቡት የተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍ በአስሩ ምዕራፍ ውስጥ የመናገር ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ መልጃዎች ቀርበዋል። ይህ የሚያመለክተው ለመናገር ክሂል ትኩረት መሰጠቱን ነው። የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረቡት ይዘቶችና ክንውኖች ሁሉም ማለተ ይቻላል ማስተማሪያ መሳሪያዎችን መስረት ያደረጉ ናቸው። የመናገርን ክሂል ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ በተማሪዎች ተመርጠው የሚቀርቡና ከራሳቸው የህይወት ገጠመኝ ጋር የተቆራኘ ቢሆን ትምህርቱን አጉልተው እንዲማሩ ይጋብዛቸዋል። በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ይዘቶችና ክንውኖች ብቻቸውን በንግግር ሐሳብን የመግለፅ ችሎታንና ተግባቦትን የመፍጠር ብቃትን ወደ ማዳበር የሚያደርሱ መሆናቸውን ጥናቱ በሰበሰባቸው መረጃዎች አማካኝነት ደርሶበታል።

### 4.2.2 የክፍል ውስጥ የመነጋገር ክሂል ትምህርት ትግበራ

የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ ተማሪዎች በአራቱ የቋንቋ ክሂሎች በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ ማድረግ ነው። ከነዚህ ክሂሎች አንዱ ደግሞ መናገር መሆኑ ቀደም ብሎ ተገልጿል። ይህ በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዳበር ይገባል። ስለዚህ በመናገር ክሂል ትምህርት የአቀራረቡን ፣ የልምምዱን እና የአፍልቆት ሂደቱን በተግባር ላይ ሊውሉ የሚያስችሉ መልመጃዎች በበቂ ሁኔታ መመረጥና መደራጀት አለባቸው።

በመማር - ማስተማሩ ሂደት የትምህርት አቀራረብ መምህሩ ወደ ዋናው ተግባር ከመግባቱ በፊት የተማሪዎችን ትኩረት ለመሳብና ውስጣዊ ፍላጎታቸውን ለማነሳሳት የማነቃቃት ተግባር መፈፀም ይገባዋል። ይህንን በማደርጉም በቋንቋው ተጠቅመው ሀሳባቸውን በመናገር

እንዲገልጹ ከማበረታታቱም ባሻገር የመማር - ማስተማሩ ሂደትም ውጤታማ ይሆናል፡፡ የማነቃቃት ሥራ ትምህርት ለመጀመር ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የመናገር ማስተማር ደረጃዎች እጅግ ጠቃሚ መሆኑን አብዛኞቹ ሙሁራን ይስማሙብታል፡፡ ይሁን እንጂ ከክፍል ውስጥ ምልከታው የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው ለዚሁ ተግባር ብዙም ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን ነው፡፡

ተግባቦታዊ አቀራረብ ተማሪዎች በቋንቋው ተጠቅመው በተለያዩ ማህበራዊ ርዕሰ ጉዳዮች ውስጥ ሀሳባቸውን በመግለጽ በቂ ልምምድ የሚደረግበት ነው፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎች መስተጋብር እንዲጨምር ፍንጭ ሰጪ ሃሳብና የተለያዩ ስዕሎች፣ ፎቶግራፎች ወዘተ በተጨባጭ በክፍል ውስጥ በማምጣት ተነሳሽነታቸውንና ፍላጎታቸውን ባገናዘበ መንገድ ተማሪዎች እንዲናገሩ እና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ መምህራን ያደረጉት ጥረት ደካማ እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ መምህራን አልፎ አልፎ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች መናገርን የሚለማመዱበትን ክንውን የሚሰጡ ቢሆንም ተማሪዎቹ በጥንድ ወይም በቡድን በመሆን እርስ በርሳቸው ሃሳብ ለሃሳብ እንዲለዋወጡ፣ ሌሎች የሚያስተላልፉትን ሀሳብ መረዳት እንዲችሉ፣ እንዲከራከሩ፣ እንዲወያዩ ወዘተ የሚደረግ ሁኔታ በከፊል ደረጉ መሆኑን ታይቷል፡፡

የምልከታው መረጃ በግልጽ እንዲሚያሳየው ተማሪዎች ሀሳባቸውን በመናገር የመግለጽ ችሎታቸውንና ተግባቦታቸውን ለማዳበር የሚያስችላቸውን በተግባር የሚለማመዱበት ሁኔታ ሲታይ በተወሰኑ ተማሪዎች ላይ ብቻ በማተኮር ሌሎች ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን በተገቢው መንገድ እንዳይለማመዱ መደረጋቸውንመረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡ መምህራኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪው ሀሳቡን በንግግር መግለጽ የሚችልበትን በጥንድ ወይም በቡድን መናገርን የሚማሩበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሚና በአብዛኛው እንዳልተጫወቱ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሐሳቦች

በምዕራፍ አንድ እንደተገለጸዉ አጥኚዉ ይህን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሳዉ መሰረታዊ ጉዳይ መንግስታዊ በሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበር በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግና አለማድረጋቸዉን ለመፈተሽ ነዉ፡፡በዚህም መሰረት የክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት ደረጃዎች ፣ በመናገር ትምህርት አቀራረብ ፣ የመምህሩ የልምምድ ተግባር እና የአፍልቆት አተገባበር ምን እንደሚመስል ለመርመር ተሞክሯል፡፡እነዚህን ጉዳዮች ለመርመርም የክፍል ዉስጥ ምልከታ፣ በተተኳሪ መምህራንና ተማሪዎች በሚሞሉት የጽሁፍ መጠይቆች መረጃዎችን ለማሰባበሰብ ተችሏል፡፡ መረጃዎቹን በመተንተን ጥናቱ የሚከተሉትን ዉጤቶች አግኝቷል፡፡

## 5.1 ማጠቃለያ

የመናገር ክሂል የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ትርጉም ባለዉ መንገድ ችሎታቸዉ እንዲዳብር የተለያዩ አይነት መንገዶችን መጠቀም እንዳለበት እያንዳንዱ መምህር ራሱን በማዛጀት ረገድ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ መምህሩ ጥሩ የመማር ማስተማር ሁኔታን በክፍል ዉስጥ ካልፈጠረና ትምህርቱንም በተገቢዉ መንገድ እንዲካሄድ ትኩረት የሚሰጡ ፣ከተማሪዎች የእለት ህይወታቸዉ ጋር የተገናኘ ርዕሰ ጉዳዮችን ፣ የማነቃቂያ ስልቶችን ካላቀረበ ቶሎ የመሰላቸትና ለመሳተፍ ፍላጎት ያለመኖር አዝማሚያ በተማሪዎች ላይ መታየቱ ይበረታል፡፡ የመረጃው ውጤት እንደሚያመለከተው በክፍል ውስጥ የቀረቡት ይዘቶችና ክንውኖች መምህሩ ፈጠራ ላይ እንዲሁም የተማሪዎችን ነባራዊ ሁኔታ በሚያሳይ ርዕስ ላይ ያልተመሰረቱና መማሪያ መጽሐፍን ተመርኩዘው የቀረቡ መሆናቸው ተማሪዎቹን ግድየለሽ አድርጓቸዋል፡፡ እንዱሁም ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን ያለማበረታታት እና መምህር መር አቀራረብ በመኖሩ ክሂሉ በአግባቡ እንዳይተገበር አድርጎታል፡፡

በአጠቃላይ የጥናት ውጤቱ እንደሚያመለክተው የቀረቡት የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ ትግበራ የተማሪዎችን ስሜትና ፍላጎት የማያነሳሳ በመሆኑ ነፃ ሆነው እንዲናገሩ የማያበረታቱ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለማዳበር መምህራን በቂ ጊዜ ወሰደው ግልፅ አላማ ይዘው ሥራውን እንዳላከናወኑት ያሳየናል፡፡

## 5.2 አስተያየት

ለጥናቱ መነሻ ከሆኑ ምክንቶች አንዱ የመናገር ክሂል ትምህርት አተገባበርን በሚመለከት የታዩ ችግሮች ለወደፊቱ ይፈቱ ዘንድ መፍትሄ መጠቆም ነው፡፡ ስለሆነም ትናቱ ያነሳቸውን ጥያቄዎች እና ግኝቶች መሰረት በማድረግ የሚከለቱት አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡

- የመናገር ክሂል ተግባር ከመከናወኑ በፊት የትምህርት አላማ በዝርዝር እነዲቀርብ ቢደረግ፤
- ተማሪዎች ወደ ዋናው የመናገር ክሂል ትምህርት ከመግባታቸው በፊት የማነቃቂያ ትምህርት ቢሰጣቸው ፤
- መምህራን የመናገር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ የተማሪዎን የቅድመ እውቀት መነሻ ቢያደርጉ፤
- የመናገር ክሂልን ለማሳደግ የቀረቡትን ተግባራት ለማለማመድ የሚሰጠው ጊዜ ከመልመጃዎቹ ስፋት ጋር እየታየ ቢሆን፤
- ክርክር፣ ጭውውት፣ ከውይይት በተጨማሪ የግልና የጥንድ ስራን የሚያበረታቱ እንደ ታሪክ መናገር፣ የዱብዳ ንግግር፣ ቃለመጠይቅ መደራረግ የመሳሰሉ ተግባራት በቀጣዩ ዝግጅት እንዲካተቱ ትኩረት ቢደረግ፤
- የተማሪዎቹን የመናገር ክሂል ለማሳደግ መምህራን ከተማሪዎች ህይወት ጋር የተያያዙና ሳቢነት ያላቸው ርእሶች ከተለያዩ ምንጮች(ጋዜጣ ወይም መጻህፍት) ወደ ክፍል ለማምጣት ቢሞከር፤
- መምህራን ተማሪዎቻቸው ያሉባቸውን የንግግር ግብዓት ማጣት ችግር መቅረፍ ይችሉ ዘንድ ጋዜጦችን መጻህፍትን ወዘተ እንዲያነቡ ቢያበረታቱ፤
- ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን መምህራን የተለየ ትኩረት በመስጠት በልምምድ ወቅት ከፍተኛ ክትትል ቢያደርጉላቸው፤
- በአፍልቆት ትምህርት ወቅት የተወሰኑ ተማሪዎችን ብቻ ከማሳተፍ ይልቅ ሁሉም ተማሪዎች ተግባሩን እንዲያከናውኑ ቢደረግ፤

- መናገርን ክሂል ለማሳደግ የሚረዱ ተግባራት (መልመጃዎች የተማሪዎቸን እድሜ፣ ጾታ፣ የእውቀት ደረጃ፣ የመጡበትን አካባቢ ወዘተ) ያገናዘቡ እንዲሆኑ በመጽሃፍት ዝግጅት ወቅት የፍላጎት ዳሰሳ ማድረግ ትኩረት ቢሰጠው፤

- መምህራን አዳዲስ ጸንስ ሀሳቦችና ከማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር ለማስተዋወቅ የትምህርት ቢሮ፣ የወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች ወዘተ ስልጠናዎችን እንደአስፈላጊነቱ ቢዘጋጁ፤

- የመማሪያ ክፍል መጨናነቅ በመናገር ክሂል አቀራረብ አሉታዊ ተጽእኖ ስላለው ተማሪ ክፍል-ጥምርታ መማሪያ ክፍሎች ግንባታ በከተማው ትምህርት ቢሮ ስታንዳርድ መሰረት እንዲሆን የየወረዳው አስተዳደር እና የየወረዳው ትምህርት ጽህፈት ቤቶች፣ ያካባቢው ኅብረተሰብ እና መንግስታዊ ልሆኑ ድርጅቶች ትኩረት ቢሰጡት፤

- አብዛኛውን ጊዜ የሚታየው የመምህሩ ሚና የመጉላት ሁኔታ ቢቀንስ ከችግሩ በመላቀቅ የመማር ማስተማር ሂደቱ በመልካም ሁኔታ ይጓዛል ብሎ አጥኚው ያምናል፡፡

## ዋቢ መጽሐፍት


በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (2001)፡፡ *<u>በስነ ፅሑፍ ቋንቋ ማስተማር፡፡</u>* ፋር ኢስት ትሬንግ ኃላ.የተ.የግ.ማህበር

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡ (1981) *"ስነ ልሳንን እና ቋንቋን ማስተማር "* የቋንቋዎች እና ጥናት ተቋም፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

አያለሰው ይታየው፡፡(2003) *" ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍት ውስጥ በሚገኙ የልበወለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ኪሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተና እና ግምገማ "* የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

እጅጉ ይማም፡፡ (2003) " በደብረ ብርሃን ከተማ በተመረጡ ሶስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሰባተኛ ክፈል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አመቀራረብ ግምገማ"፡፡ የአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የቋንቋዎች ጥናተ ተቋም

ያለው እንዳወቅ፡፡ (2001) *<u>የምርምር መሠረታዊ መርሆዎች አተገባበር፡፡</u>* ሁለተኛ እትም፡፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት

Bygate. M. (1987). *<u>Speaking</u> oxford*; Oxford university press.

Brown & Yule (1983). "*A Holistic approach to Teaching speeking in the language class room.*" (Symposium).

Brum Fate(1984) *<u>Imroving speaking fluency</u>*. Vol.17.No 3 pp.287-295.Printed Great Britain

Byrne, D (1987). *<u>Techniques for class room interaction</u>*. London. Longman Group UK limited.

Byrne, D (1976). *<u>Teaching Oral English</u>, London*: Longman.

Cook,G. (1989). Discourse oxford university press.

Gower, R., Phillips, D, and walters. S. (1995) *Teahcing practice hand book*. Oxford. Heinemann.

Harmer. J. (1995). *The principle of English Language Teaching*. London; Longman.

Harmer. J. (2007). *How to teach English.* London: Longman.

Lewis & Sick (1993). *Teaching English 7-12 NewYourk*; America Book Company.

Mc Donough. J. and shaw. C (1995) *Materials and Methods in ELT: A teachers Guide Oxford*. B. Lack well Publishers Ltd.

Nunan. D. (1991): *Tasks for the communicative Classrrom*. Sydney: Cambridge University Press.

Paul Nation.(1990). *Improving Speaking fluency*. Vol.17.No. 3,pp.377-384,printed Great Britain.

Pressley.M.D & etal.(2007).*Teaching reading journale of education psychologiy*. Vol.pp.m124.pp129

Richards:Jack C.(1994). *The context of language teaching*. Cambridge:Cambridge University press.

Sesnan (1997).*How to teach English*. Oxford: cup

Tricia Hedge (1996): *Teaching and learning in the language class room*. oxford university Press

Ur.P.(1996). *Acourse in language teaching practice and theory* Cambridge University Press.

Widdowson H.G (1992) *Teaching Language as communication*. Oxford University Press

## አባሪ አንድ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የቋንቋ ተቋም ፋካልቲ

## የሂዩማኒቲስ፤የቋንቋ ጥናት፤ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፤ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

**የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ**

ውድ የ ________________ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ይህ መጠይቅ በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂል አተገባበር በክፍል ውስጥ እንዴት እያቀረቡ እንዳለ ለመፈተሽ የተዘጋጀ ነው፡፡ ከመጠይቁ የሚገኘው ምላሽ ለተጀመረው ጥናት መሳካት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ይታሰባል፡፡ ጥናቱ የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ የሙያው ባለቤቶችን ድጋፍ የሚጠይቅ ስለሆነ እርስዎም ይህንን መጠይቅ በመሙላት የበኩልዎን ሙያዊ ድጋፍ ያደርጉልኝ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

በመጨረሻም እጅግ ውድ የሆነ ጊዜዎን ሰጥተው መጠይቁን ለመሙላቱ ለሚያደርጉት ትብብር ምስጋናዬ ይድርስዎ፡፡

**ማሳሰቢያ፡** በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

### ክፍል አንድ

### አጠቃላይ መረጃ

**ከዚህ በታች ላቀረቡት መረጃዎች ትክክለኛውን መረጃ በቀረበው ባዶ ቦታዎች ይሙሉ፡፡**

1. ጾታ ______________________
2. የትምህርት ደረጃ ______________________
3. የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ ______________________
4. የአገልግሎት ዘመን ______________________
5. የንግግር ክሂልን ትምህርት ማስተማር አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ? ለምን?______________________

   ______________________________________________
6. የንግግር ክሂልን በማስተማር ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች አሉ ወይ? ካሉስ ምን? ምን ናቸው?______________________

   ______________________________________________

## ክፍል ሁለት

**ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ ለቀረቡት ዝርዝር መጠይቆች መልስ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡ አራት አማራጮች ተሰጥተዋል። እርስዎም በጥያቄዎቹ ትይዩ የሚሰጡትን መልስ የ"X" ምልክት በማድረግ ያመልክቱ።**

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | ሁልጊዜ | አብዛኛውን ጊዜ | አንዳንድ ጊዜ | ጨርሶ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመናገር ትምህርት ከማቅረቤ በፊት አላማዉን በግልፅ አብራራለሁ? | | | | |
| 2 | ወደ ዋናዉ የመናገር ተግባር ከመግባቴ በፊት የማነቃቂያ ስራ አከናዉናለሁ? | | | | |
| 3 | ከመናገር ትምሁርት በፊት ስለመናገር አቀራረብ ተማሪዎች እንዲያውቁ አደርጋለሁ? | | | | |
| 4 | ለመናገር ትምህርት የሚሆን ግብአቶችን በግል ተዘጋጅቼ በመምጣት አስተምራለሁ(አጋዥ መርጃ መሳሪያዎችን)? | | | | |
| 5 | ተማሪዎቹ በቀረበላቸው ሞዴል የመናገር ተግባር መሰረት የማስመሰልና የመደጋገም ስራዎችን እንዲያከናውኑ አደርጋለሁ? | | | | |
| 6 | **በክፍል ዉስጥ የመናገር ክሂል ትምህርት የሚሆኑ ርዕስ ጉዳዮች በተማሪዎች የህይወት ገተመኝ ዙሪያ እንዲለማመዱ አደርጋለሁ?** | | | | |
| 7 | **በራሳቸዉ የቋንቋ እዉቀት ተጠቅመዉ ሀሳባቸዉን የሚገልፁበት መንገድ አመቻቻለሁ?** | | | | |
| 8 | **አብዛኛዉን ጊዜ ለመናገር የማይደፍሩና ሀሳባቸዉን ለመግልፅ የሚያዳግታቸዉ ተማሪዎች እንዲናገሩ የተለያዩ መንገዶችን አመቻቻለሁ?** | | | | |
| 9 | **የመናገር ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት አስተምራለሁ (አለማምዳለሁ)?** | | | | |
| 10 | **የተማሪዎች የንግግር ክሂል ለማዳበር የሚታዩ ነገሮችን ስዕል ፤ቅርፃቅርፅ፤ ካርታ ወዘተ በመስጠት እንዲለማመዱና እንዲናገሩ አደርጋለሁ?** | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 11 | **ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል ሀሳብ ለሀሳብ እንዲለዋወጡ አደርጋለሁ?** | | | | |
| 12 | የመናገር ተግባሩ ከቀረበና በዛላይ ከተለማመዱ በኋላ ሀሳባቸዉን በነፃነት እንዲገልፁ የማድረግ ሁኔታ? | | | | |
| 13 | የተማሪዎቹን ቁጥር ባገናዘበ መልኩ በቡድን(በህብረት)ተወያይተዉ ሀሳባቸዉን እንዲገልፁ አበረታታለሁ? | | | | |
| 14 | ተማሪዎች ከክፍል ዉጪ ሰዎችን ጠይቀዉ ወይም ምልከታ አድርገዉ እና የተለያዩ ፅሑፎችን አንብበዉ በክፍል ዉስጥ እንዲናገሩ ማድረግ? | | | | |
| 15 | በመናገር ትምህርት ወቅት በተማሪዎቹ ንግግር ጣልቃ በመግባት ስህተታቸዉን እንዲያርሙ አደርጋለሁ? | | | | |
| 16 | የመናገር ትምህርቱ ከመጠናቀቁ በፊት ተማሪዎቹ ጥያቄ እንዲጠይቁ አበረታታለሁ? | | | | |
| 17 | ስህተት እንደ አንድ የመማሪያ መንገድ አድርገዉ እንዲቆጥሩ አስገነዝባለሁ? | | | | |
| 18 | ተማሪዎቹ ስህተታቸዉን እርስበርስ እንዲተራረሙ የማመቻቸት ሁኔታ? | | | | |
| 19 | በቀረበዉ የንግግር ትምህርት ላይ የማሻሻያ ሀሳብ የመስጠት ሁኔታ? | | | | |

# አባሪ ሁለት

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የቋንቋ ተቋም ፋካልቲ

## የሂዩማኒቲስ፤የቋንቋ ጥናት፤ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፤ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

**የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመናገር ክሂል በክፍል ውስጥ አተገባበር ለመፈተሽ የተዘጋጀ የጽሁፍ መጠይቅ**

**ውድ ተማሪዎች**

ይህ መጠይቅ በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመናገር ክሂል አተገባበር በክፍል ውስጥ እንዴት እየቀረበ እንደሆነ ለመፈተሽ የተዘጋጀ ነው፡፡

ስለሆነም የምትሰጡት ምላሽ ለጥናቱ የላቀ ድርሻ ስላለው ትክክለኛውን መልስ በመስጠት ትተባበሩኝ ዘንድ እየጠየቅኩ ለምታደርጉልኝ መልካም ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

**ክፍል አንድ**

**አጠቃላይ መረጃ**

- የትምህርት ቤቱ ስም ____________________
- ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ክ/ከተማ _________
- የተማሪው ክፍል ደረጃ _____________
- ፆታ ወንድ ☐ ሴት ☐

**ክፍል ሁለት**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ያለህን/ሽን አመለካከት በትክክል ያመለክታል የምትለውን/ይውን ሀሳብ በቀኝ በኩል ከተሰጡት አማራጮች መካከል አንዱን በመምረጥ የ “X” ምልክት በማድረግ አመልክት/ች፡

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | መወሰን ያቅተኛል | አልስማማም | በፍፁም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመናገር ትምህርት ክሂልን ተግባር ከማከናወናቸው በፊት አለማው ይገለፅላችኋል? | | | | | |
| 2 | የመናገር ክሂል ተግባር በክፍል ውስጥ ከመቅረቡ በፊት በተለያዩ መንገዶች ያነቃቃሉ? | | | | | |
| 3 | የመናገር ክሂል ተግባር ከመጀመራቸው በፊት አጭርና ግልፅ መመሪያ ይሰጡ ነበር? | | | | | |
| 4 | ዋናውን የመናገር ተግባር ተማሪዎች ከማከናወናቸው በፊተ ሞዴል (ምሳሌ የሚሆኑ) ተግባሮች ይቀርቡ ነበር? | | | | | |
| 5 | በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን ውይይት፣ ክፍሉ በአንድነት በመሆን ወዘተ የመናገር ክሂል ተግባርን በክፍል ውስጥ የመከናወኑ ሁኔታ? | | | | | |
| 6 | በግል፣ በጥንድ፣በሶስትዮሽ፣ በቡድን፣ ወዘተ የመናገር ክሂል ተግባራትን እየተዘዋወሩ በመከታተል ያበረታታሉ? | | | | | |
| 7 | በክፍል ውስጥ ንግግርን በሪፖርት፣ በጭውውት፣ በክርክር፣ በውይይት መልክ ተግባራቱን መለማመዱ የንግግር ችሎታን አጉልብቷል? | | | | | |
| 8 | በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት የመናገር ክሂል ተግባራት ከተማሪው የህይወት ልምድ ጋር የተቆራኙ ናቸው? | | | | | |
| 9 | በጥንድ፣በቡድን ወዘተ በመሆን የመናገር ክሂል ተግባራትን በመለማመድ እና በመከታተል የንግግር፣ የጭውውት ፣ የክርክር የውይይት ስርአት እንዲዳብር ተደርጓል? | | | | | |
| 10 | የመናገር ተግባራትን ስታከናወኑ ሀሳብችሁን በነፃነት እንድትገልፁ ተደርጓል? | | | | | |
| 11 | በጥንድ፣ በቡድን በመሆን ቃለመጠየቅ ማድረግ ስዕላዊ መግለጫዎች በሚያስተላልፉት ሀሳብ ላይ መወያየትና መከራከር እንዲሁም ሀሳብን ያለፍርሀት ለመግለፅ ተችላል? | | | | | |
| 12 | የጭውውት ፣ የክርክር፣ የውይይት ተግባራት በክፍል ውስጥ ከቀረቡ በኋላ በማጠቃለያ ያለምንም ፍርሀት አስተያት እሰጣለሁ? | | | | | |
| 13 | ስህተታችን በቀጥታ ከመናገር ይልቅ እርስበርስ እንድንተራረም ይደረግ ነበር? | | | | | |
| 14 | ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎች እንዲናገሩ ይበረታታሉ? | | | | | |
| 15 | የመናገሩ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል ይሰጣሉ? | | | | | |

# አባሪ ሶስት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የቋንቋ ተቋም ፋካልቲ

## የሂዩማኒቲስ፤የቋንቋ ጥናት፤ ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፤ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

### የክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርት ክንውን ምልከታ መከታተያ ቅፅ

የትምህርት ቤቱ ስም ____________________

ምልከታ የተካሄደበት የክፍል ደረጃ ____________________

ምልከታ የተደረገበት ቀን ____________________

ምልከታ የተደረገበት ክ/ጊዜ ____________________

ምልከታ የተደረገበት ሰዓት ____________________

በምልከታው ወቅት ይሰጥ የነበረው የትምህርት ርዕሰ____________________

ይህ የምልከታ ቅጽ የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል ተግባራትን የክፍል ውስጥ አቀራረብን በ10ኛ ክፍል ለመከታተል ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ በክፍል ምልከታ ወቅት ተግባራቱ ተከናውነው ከሆነ / √/ ምልክት "አዎ "ከሚለው ላይ ደረጋል፡፡ተግባራቱ ያልተከነናወኑ ከሆነ ደግሞ / ×/ ምልክት "አይ "ታከሚለው ላይ ይመለከታል፡፡

| ተ.ቁ | የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ | አዎ | አይ |
|---|---|---|---|
| 1 | የተወሰነ ግልፅ ዓላማ ለተማሪዎች ቀርቦ ነበር? | | |
| 2 | የትምህርቱ አቀራረብ የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ መሰረት ያደረገ ነበር? | | |
| 3 | በትምህርቱ አቀራረብ የፈጠራ ስራ እና የማስተማሪያ መሳሪያ ቀርቦ ነበር? | | |
| 4 | የትምህርቱ ይዘት የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ ነበር? | | |
| 5 | የመናገር ትምህርቱን በበቂ ሁኔታ ይለማመዱ ዘንድ ተማሪዎችን የማነቃቃት ተግባር ተከናውኗል? | | |
| 6 | የቀረቡት መመሪያዎች ለተማሪዎቹ ግልፅ ነበሩ? | | |
| 7 | በልምምድ ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ ጐልቶ ይታይ ነበር? | | |
| 8 | ተግባሩን ለማለማመድ የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ ተጠቅመዋል? | | |
| 9 | የመናገር ክሂልን ማለማመድ የሚያስችሉ ተግባራትን (በክርክር፣ በጭውውትና በውይይት መልክ) ተከናውኗል? | | |
| 10 | የመናገር ክሂል ልምምዱን ለማድረግ በግል፣ በጥንድ ወይም በ1 ለ5 የማስተማር ስነ-ዘዴ ተጠቅመው ነበር? | | |
| 11 | በልምድ ጊዜ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሣተፉ ይደረግ ነበር? | | |
| 12 | ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎች እንዲለማመዱ ይበረታቱ ነበር? | | |
| 13 | ልምምድ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዙ የተለያዩ ዘዴዎች ይጠቀሙ ነበር? | | |
| 14 | በልምምድ ወቅት ተማሪዎች እርስ በርስ በመወያየት ልምምድ እንዲያደርጉ ይበረታቱ ነበር? | | |
| 15 | ተማሪዎቹ ያልገባቸውን ጥያቄዎች እንዲያቀርቡ ሰፋ ያለ ዕድል ተሰቷቸዋል? | | |
| 16 | በልምምድ ወቅት ተማሪዎች ሲሳሳቱ ለመርዳት ጥረት ተደርጎ ነበር? | | |
| 17 | የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን በማቅረብ የሚያዩትን ነገር በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ይደረግ ነበር? | | |
| 18 | የንግግር ተግባራቱ ተማሪዎችን በቀላሉ እና በነፃነት ሊያግባባ የሚችል ዐውድ በመፍጠር የተከናወኑ ናቸው? | | |
| 19 | ውይይት እና ክርክር በማዘጋቸት የመናገር ተግባር እንዲከናወን ተደርጓል? | | |
| 20 | የተሰጡት ተግባራት የትምህርቱን አላማ ያሳኩ ነበር? | | |
| 21 | ተማሪዎች ስህተት ሲፈጽሙ እርማቱ በወቅቱ ይሰጥ ነበር? | | |